## ሁለተኛው ስደት

የይሖዋ ምስክሮች ይጋጠማቸው ሌላው ስደት ከማርኪሲስታዊው መንግሥት ነው። በመስከረም 1974 ዓ.ም. በመፈንቅለ መንግሥት ደርግ ሥልጣን ጨበጠ። አገሪቱም በማርኪሲዝም – ሌኒኒዝም ሪእት – ዓለም መተዳደር ጀመረች። በ1970ዎቹ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያናት፥ የይሖዋ ምስክሮችን ጨምሮ ታላቅ የሆነ ስደት ደረሰባቸው። እንደ 1960ዎቹ ከ1980 ዓ.ም. እስከ 1980 ዓ.ም. በዓመታዊ መጽሐፉም ሆነ "መጠበቂያ ግንብ" መጽሔት ምንም ዓይነት ስታቲስቲካዊ ዘገባ ያለመቅረቡ የዚህ ውጤት ነው[48]። እንደ 1992 ዓ.ም. ዓመታዊ መጽሐፍ ብዙ የይሖዋ ምስክሮች በእምነታቸው የተነሣ ተገድለዋል[49]።

## ማጠቃለያ

የክሪኮር ኢታዛኮርታዚያን ወራሾች ከ1991 ዓ.ም. ወዲህ ባሉት ዓመታት የየዓመቱ የእድገት መጠናቸው በአማካይ 15 በመቶ መሆኑ የሚያመለክተን እጅግ ስኬታማ መሆናቸውን ነው። በየዓመቱም አዲስ አበባ በሚገኘው የስፖርት መጫወቻ ሜዳ [ስታዲየም] አገር አቀፍ ስብሰባቸውን ያደርጋሉ። በ1997 ዓ.ም. ስታቲስቲክ መሠረት፡- 5,649 ንቁ ተሳታፊ አባላት፥ 5,292 ለመስክ 916 አቅኚዎች፥ 97 ጉባዔዎች፥ ለመስክ አገልግሎት 1,570 141 ሰዓት፥ 3,674 በቤት ውስጥ የተደረጉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች አሉአቸው።

ለይሖዋ ምስክሮች እድገት እንደ ምክንያት ከሚቆጠሩት መካከል በስደት ጊዜ ጸንተው መቆማቸው፥ ሊስብ የሚችሉና ወቅታዊ ርዕሶች ላይ የሚዘጋጁት ጽሑፎቻቸው፥ እያንዳንዱ የይሖዋ ምስክር መሠረት እምነቱን ማወቁ፥ አባላቱ እምነታቸውን ለሌላ ሰው ለማስተማር ያላቸው ከፍተኛ ፍላጎት እንደ ምክንያት ከሚቆጠሩት ውስጥ ዋንኞቹ ናቸው[50]።

---

48. የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክ የሚለውን ርዕስ ይመለከቷል። የተገደሉትን ሰዎች ስምና
49. 1992 ዓመታዊ መጽሐፍ በደርግ ዘመን ስለ እምነታቸው ፎቶግራፍ አውጥቶአል።
50. አባላቱ የመጠበቂያ ግንብን አስተምህሮ የሚያስተምሩት እንዲሁም የድርጅቱን ጽሑፎች የሚያሠራጩት "የመስክ አገልግሎት" ለደኅንነታቸው አስፈላጊ (አንገብጋቢ) ስለሆነም ጭምር ነው።

# ምዕራፍ ሦስት

# የይሖዋ ምስክሮች አስተምህ[...]
# በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘ[...]


3.1 የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር የአምላክ ድርጅት ነውን? ... 5[...]
3.2 የይሖዋ ምስክሮችና የአምላክ ስም ........ 6[...]
3.3 የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮተ ሥላሴ ........ 7[...]
3.4 የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ..... 9[...]
3.5 ደኅንነት በይሖዋ ምስክሮች መንገድ ........ 10[...]
3.6 የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ በሞት፥ በነፍስና በሲኦል ላይ ........ 123
3.7 የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ምጽአት ........ 132

## ሁለተኛው ስደት

የይሖዋ ምስክሮች ይጋጠማቸው ሌላው ስደት ከማርኪሲስታዊው መንግሥት ነው። በመስከረም 1974 ዓ.ም. በመፈንቅለ መንግሥት ደርግ ሥልጣን ጨበጠ። አገሪቱም በማርኪሲዝም – ሌኒኒዝም ሪኦተ – ዓለም መተዳደር ጀመረች። በ1970ዎቹ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያናት፥ የይሖዋ ምስክሮችን ጨምሮ ታላቅ የሆነ ስደት ደረሰባቸው። እንደ 1960ዎቹ ከ1980 ዓ.ም. እስከ 1980 ዓ.ም. በዓመታዊ መጽሐፉም ሆነ "መጠበቂያ ግንብ" መጽሔት ምንም ዓይነት ስታቲስቲካዊ ዘገባ ያለመቅረቡ የዚህ ውጤት ነው[48]። እንደ 1992 ዓ.ም. ዓመታዊ መጽሐፍ ብዙ የይሖዋ ምስክሮች በእምነታቸው የተነሣ ተገድለዋል[49]።

## ማጠቃለያ

የክርክር ኢታዛኮርታዚያን ወራሾች ከ1991 ዓ.ም. ወዲህ ባሉት ዓመታት የየዓመቱ የእድገት መጠናቸው በአማካይ 15 በመቶ መሆኑ የሚያመለክተን እጅግ ስኬታማ መሆናቸውን ነው። በየዓመቱም አዲስ አበባ በሚገኘው የስፖርት መጫወቻ ሜዳ [ስታዲየም] አገር አቀፍ ስብሰባቸውን ያደርጋሉ። በ1997 ዓ.ም. ስታቲስቲክ መሠረት፦ 5,649 ንቁ ተሳታፊ አባላት፥ 5,292 ለመስከ 916 አቅኚዎች፥ 97 ጉባዔዎች፥ ለመስከ አገልግሎት 1,570 141 ሰዓት፥ 3,674 በቤት ውስጥ የተደረጉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች አሉአቸው።

ለይሖዋ ምስክሮች እድገት እንደ ምክንያት ከሚቆጠሩት መካከል በስደት ጊዜ ጸንተው መቆማቸው፥ ሊስብ የሚችሉና ወቅታዊ ርዕሶች ላይ የሚዘጋጁት ጽሑፎቻቸው፥ እያንዳንዱ የይሖዋ ምስክር መሠረት እምነቱን ማወቁ፥ አባላቱ እምነታቸውን ለሌላ ሰው ለማስተማር ያላቸው ከፍተኛ ፍላጎት እንደ ምክንያት ከሚቆጠሩት ውስጥ ዋንኞቹ ናቸው[50]።

48. የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክ የሚለውን ርዕስ ይመለከቷል።
49. 1992 ዓመታዊ መጽሐፍ በደርግ ዘመን ስለ እምነታቸው የተገደሉትን ሰዎች ስምና ፎቶግራፍ አውጥቶአል።
50. አባላቱ የመጠበቂያ ግንብን አስተምህሮ የሚያስተምሩት እንዲሁም የድርጅቱን ጽሑፎች የሚያሠራጩት "የመስክ አገልግሎት" ለደኅንነታቸው አስፈላጊ (አንገብጋቢ) ስለሆነም ጭምር ነው።

# ምዕራፍ ሦስት

# የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን

3.1 የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር የአምላክ ድርጅት ነውን?...50
3.2 የይሖዋ ምስክሮችና የአምላክ ስም...60
3.3 የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮተ ሥላሴ...74
3.4 የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ...92
3.5 ደኅንነት በይሖዋ ምስክሮች መንገድ...104
3.6 የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ በሞት፥ በነፍስና በሲኦል ላይ...123
3.7 የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ምጽአት...132

## ሁለተኛው ስደት

የይሖዋ ምስክሮች ይጋጠማቸው ሌላው ስደት ከማርኪሲስታዊው መንግሥት ነው። በመስከረም 1974 ዓ.ም. በመፈንቅለ መንግሥት ደርግ ሥልጣን ጨበጠ። አገሪቱም በማርኪሲዝም – ሌኒኒዝም ሪአተ – ዓለም መተዳደር ጀመረች። በ1970ዎቹ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያናት፥ የይሖዋ ምስክሮችን ጨምሮ ታላቅ የሆነ ስደት ደረሰባቸው። እንደ 1960ዎቹ ከ1980 ዓ.ም. እስከ 1980 ዓ.ም. በዓመታዊ መጽሐፋም ሆነ "መጠበቂያ ግንብ" መጽሔት ምንም ዓይነት ስታቲስቲካዊ ዘገባ ያለመቅረቡ የዚህ ውጤት ነው[48]። እንደ 1992 ዓ.ም. ዓመታዊ መጽሐፍ ብዙ የይሖዋ ምስክሮች በእምነታቸው የተነሣ ተገድለዋል[49]።

## ማጠቃለያ

የክሪኮር ኢታዛኮርታዚያን ወራሾች ከ1991 ዓ.ም. ወዲህ ባሉት ዓመታት የየዓመቱ የእድገት መጠናቸው በአማካይ 15 በመቶ መሆኑ የሚያመለክተን እጅግ ስኬታማ መሆናቸውን ነው። በየዓመቱም አዲስ አበባ በሚገኘው የስፖርት መጫወቻ ሜዳ [ስታዲየም] አገር አቀፍ ስብሰባቸውን ያደርጋሉ። በ1997 ዓ.ም. ስታቲስቲክ መሠረት፡– 5,649 ንቁ ተሳታፊ አባላት፥ 5,292 ለመስከ 916 አቅኚዎች፥ 97 ጉባዔዎች፥ ለመስከ አገልግሎት 1,570 141 ሰዓት፥ 3,674 በቤት ውስጥ የተደረጉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች አሉአቸው።

ለይሖዋ ምስክሮች እድገት እንደ ምክንያት ከሚቆጠሩት መካከል በስደት ጊዜ ጸንተው መቆማቸው፥ ሊስብ የሚችሉና ወቅታዊ ርዕሶች ላይ የሚዘጋጁት ጽሑፎቻቸው፥ እያንዳንዱ የይሖዋ ምስክር መሠረት እምነቱን ማወቁ፥ አባላቱ እምነታቸውን ለሌላ ሰው ለማስተማር ያላቸው ከፍተኛ ፍላጎት እንደ ምክንያት ከሚቆጠሩት ውስጥ ዋንኞቹ ናቸው[50]።

48. የይሖዋ ምስክሮች ስታቲስቲክ የሚለውን ርዕስ ይመለከቷል።
49. 1992 ዓመታዊ መጽሐፍ በደርግ ዘመን ስለ እምነታቸው የተገደሉትን ሰዎች ስምና ፎቶግራፍ አውጥቶአል።
50. አባላቱ የመጠበቂያ ግንብን አስተምህሮ የሚያስተምሩት እንዲሁም የድርጅቱን ጽሑፎች የሚያሠራጩት "የመስክ አገልግሎት" ለደኅንነታቸው አስፈላጊ (አንገብጋቢ) ስለሆነም ጭምር ነው።

# ምዕራፍ ሦስት

# የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን

3.1 የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር የአምላክ ድርጅት ነውን? ... 50
3.2 የይሖዋ ምስክሮችና የአምላክ ስም ... 60
3.3 የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮተ ሥላሴ ... 74
3.4 የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ... 92
3.5 ደኅንነት በይሖዋ ምስክሮች መንገድ ... 104
3.6 የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ በሞት፥ በነፍስና በሲኦል ላይ ... 123
3.7 የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ምጽአት ... 132

## 3.1 የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር የአምላክ ድርጅት ነውን?

እንደ ይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ አንድ እውነተኛ የሆነ ሃይማኖታዊ ድርጅት ብቻ አለ[1]። ይህም ድርጅት "የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር" ነው። ይህ የሃይማኖት ድርጅት "የክርስቲያኖች ዓለማቀፋዊ ማኅበር ሲሆን የይሖዋ አምላክንና ለሰዎች ያለውን የእርሱን ዓላማ በንቁነት የሚመሰክር"[2] ነው።

እንደ ይሖዋ ምስክሮች እምነት የመጠበቂያ ግንብ እግዚአብሔር ራሱ የእርሱ ወኪል እንዲሆን የመሠረተው ድርጅት ነው። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ቃሉን የሚያስተምረው በዚህ ብቸኛ ድርጅት በኩል ብቻ ነው። ካለ ድርጅቱና በድርጅቱ እየታተሙ ከሚወጡ ጽሑፎች በስተቀር ሰዎች ቃለ እግዚአብሔርን አንብበው እውነተኛ ትርጉሙን ሊያገኙ በፍጹም አይችሉም። "መጠበቂያ ግንብ" በሚል ርዕስ ከድርጅቱ እየታተሙ የሚወጡ መጽሔቶች እንዲህ ይላሉ፦

- "የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር የዓለማችን ትልቁ ኩባንያ [Corporation] ነው፤ ምክንያቱም ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ጌታ ምሥራቹን ያስታወቀው በድርጅቱ አማካኝነት ነውና"።[3]
- "ከመከር ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በተከታታይ እግዚአብሔር እውነቱን ለማሠራጨት የተጠቀመው አንዱና ብቸኛው ድልድይ በሆነው በመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር በኩል አይደለምን?"[4]
- "የጆሆቫ [የይሖዋ] የሚታይ ምድራዊ ድርጅት በእርሱ የሚመራና እርሱን የሚወክል ነው"[5]

1. የድርጅቱን አስተምህሮ በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ። (1991) ገጽ 191–195። ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር። (1994) ገጽ 280–284 ይመለከቷል።
2. Reasoning from the scriptures (1989) ገጽ. 199
3. The Watchtower, 15 January 1917, ገጽ. 6033
4. The Watchtower, 1 April 1919, ገጽ. 6414



- "እግዚአብሔር የራሱን ድርጅት እየመራ እንዳለ ልብ ልናደርግ ይገባናል"[6]
- "በምድር ሁሉ ላይ የጆሆቫ ድርጅት በእግዚአብሔር መንፈስ ወይም ንቁ ኃይል የሚመራ ብቸኛ ድርጅት ነው"[7]

እንደ ይሖዋ ምስክሮች ዐዋጅ ከላይ ያየናቸው ዐረፍተ ነገሮች ሁሉ እውነት ከሆኑ ከእነርሱ በስተቀር ሌላ ክርስቲያናዊ ድርጅት በእግዚአብሔር የማይመራ ሰይጣናዊ ድርጅት ነው ማለት ነው።

የይሖዋ ምስክሮች ሁሉ ለዚህ እውነተኛ ለሆነ ብቸኛ ድርጅት መገዛት አለባቸው። ምክንያቱም ድርጅቱ የእግዚአብሔር እውነት መገለጫ ብቸኛው ምድራዊ ድርጅት ነውና። ስለዚህ የይሖዋ ምስክሮች ድርጅቱን እንደ እግዚአብሔር ድምፅ እንዲታዘዙት ይጠበቅባቸዋል[8]። ይህ ብቻ አይደለም ድርጅቱ ስለ ራሱ እንዲህ ይላል፦ "ጆሆቫ አምላክን ብቻ አይደለም እንደ አባትነት ልናውቀው የሚገባን ነገር ግን የእርሱን ድርጅት እንደ እናትም ጭምር እንጂ"[9]።

የእግዚአብሔርን ነገር ለማወቅ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ በቂ ላለመሆኑ ድርጅቱ እንዲህም የሚል ትምህርት አለው፦ "እግዚአብሔር ከሚጠቀምበት ከዚህ [የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር] ድልድይ ጋር ግንኙነት ከሌለን፥ ምንም እንኳን ብዙ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ብናነብም በሕይወት ጎዳና እርምጃ ልናሳይ አንችልም"[10]።

"በመጠበቂያ ግንብ [መጽሔት] አምድ ጆሆቫ በቀጣይነት ለሕዝቡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክር አዘጋጅቶአል"[11] ስለዚህ የይሖዋ ምስክሮች "ለልባምና ታማኝ ባሪያዎች" [መንፈሳዊ ምግብ የሚያወርዱ ይህንንም ድርጅቱ በሚያሳትማቸው ጽሑፎች በኩል የሚያስተላልፍ "ቅቡዓን"፥ "ልባምና ታማኝ ባሪያ" በመባል ይታወቃሉ] እንዲሁም ለጽሑፎቻቸው መገዛት አለባቸው። በመጠበቂያ ግንብ ውስጥ ያሉ ቅቡዓ አማኞች የሚወክሉት "መንፈሳዊ ምክሮች ሁሉ የሚመጡበት

5. The Watchtower, 1 May 1938, ገጽ. 169 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።
6. ዝኒ ከማሁ
7. The Watchtower, 1 June 1985, ገጽ. 19
8. The Watchtower, 15 June 1957, ገጽ. 370
9. The Watchtower, 1 May 1957, ገጽ. 274
10. The Watchtower, 1 December 1981, ገጽ. 27 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።
11. The Watchtower, 1 May 1964, ገጽ. 277 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።

ብቸኛ የሆነ የሚታይ [የአምላክ] ድልድይ"[12] ስለሆነ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እያንዳንዱ የይሖዋ ምስክር ለድርጅቱ፥ ለድርጅቱ ጽሑፍና ለጽሑፍ ጸሐፊያን መገዛት አለበት። የይሖዋ ምስክሮች ደግሞ "የልባምና ታማኝ ባሪያዎችን ሹመት ስለሚያውቁና ስለሚቀበሉ ይገዛሉ"[13]።

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች

ከላይ የተመለከትናቸውን የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለማስደገፍ ድርጅቱ የሚጠቅሳቸው ጥቅሶች የሚከተሉት ናቸው፡—

አንድ እውነተኛ ድርጅት ብቻ አለ። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ "አንድ እምነት ብቻ" እንዳለ ያስተምረናል (ኤፌ. 4፥5)። ይህም አንድ የእግዚአብሔር ሕዝብ በኢየሱስ ክርስቶስ "አንድ መንጋ" የተባለው ነው (ዮሐ. 10፥16)።

ዛሬ በተለያዩ የሃይማኖት ድርጅቶች ውስጥ ያለው መከፋፈል የሚያሳየ እነዚህ መንፈሳዊ ድርጅቶች ከእግዚአብሔር ድርጅት ጋር ኅብረ ያለመፍጠራቸውን ነው (1ቆሮ. 1፥10)።

አማኞች ለዚህ ብቸኛ የአምላክ ድርጅት መገዛት አለባቸው። አማኞ መንፈሳዊ ምግብ የሚያወርዱላቸው "ልባምና ታማኝ ባሪያ ያስፈልጋቸዋል (ማቴ. 24፥45–47)። በዚህ ክፍል በእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "ባሪያ" ከሚለው ቃል ፊት ያለው የተወሰ መስተፃምር [The] የሚያመለክተው ሁሉንም "ባሪያዎች" ሳይሆ የተወሰኑትን ብቻ ነው። ይህም "ባሪያ" የተወሰነ የክርስቲያን ስብሰ ነው። ይህም ባሪያ የሚያሳየው የይሖዋ ምስክሮችን "የቅቡዓን" ክፍ ነው። እነዚህ ባሪያዎች አስተማሪ እንደመሆናቸውም መጠን ዋና

12. Marina Bodine. Christian Research Newsletter, "Bible Answer Man" Column, May 1 J 1992, ገጽ.3 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።
13. Robert M. Bowman, Understanding Jehovah's Witnesses (Grand Rapids: Baker Ho 1991), ገጽ. 119



ሥራቸው መንፈሳዊ ምግብንና አስተምህሮአዊ መረጃዎችን ለተቀሩት የይሖዋ ምስክሮች ማውረድ ነው። ሁሉም የይሖዋ ምስክሮች "ለባሪያዎቹ" ትምህርት በየሳምንቱ ሊገዙና ከአምላክም የሚመጣውን ማንኛውም ትምህርት በሙሉ ልብ መቀበል አለባቸው።

በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 ላይ ያለው የኢየሩሳሌም ስብሰባ ይህን አቀራረብ እንድንከተል ያስተምረናል። እያንዳንዱ ጉባዔ ብቻውን ምንም ዓይነት ሥራ ሊሠራ አይችልም። ነገር ግን በኢየሩሳሌም ለሚገኙት "የሽማግሌ" አካላት ብቻ ሌሎች ይገዛሉ። በአሜሪካን አገር ብሮክሊን በሚባለው ስፍራ የሚገኙት የድርጅቱ የአመራር አካላት እንደ ኢየሩሳሌሙ ጉባዔ የሽማግሌዎች ስብሰብ ናቸው። የድርጅቱን ሥራ የሚያከናውኑት እነዚህ "ልባምና ታማኝ ባሪያዎች" ናቸው።

ስለዚህ ሁሉም የይሖዋ ምስክሮች ከአመራር አካላት የሚመጣውን ማንኛውም ዓይነት አዲስ ትምህርት፥ ከበፊቱ አስተምህሮት ጋር እንኳ ቢጋጭ ያለምንም ጥያቄ መቀበል አለባቸው።

በተጨማሪም የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የሐዋ. 8፥30–31 እና 2ጴጥ. 1፥20–21 መደገፊያ በማድረግ ማንኛውም የይሖዋ ምስክር መጽሐፍ ቅዱስን በግል አጥንቶ ያጠናውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ማብራራት እንደሌለበት፤ እንዲያውም ሊሞክረው እንኳን እንደማይገባ፤ ነገር ግን በመጠበቂያ ግንብ ማኅበር የመጽሐፍ ቅዱስ ትንተና ሊደገፍ እንደሚያስፈልገው የሚያስተምሩት የድርጅቱ ጽሑፎች እንዲህ ይላሉ፡—

- "እግዚአብሔር ቃሉን ያዘጋጀው በነጠላ ሰዎችን ለመናገር አይደለም ወይም የሕይወትን እውነታ በራሱ እንዲያንፀባርቅ ብሎ አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔር ብርሃንን ያዘጋጀው በድርጅቱ በኩል ነው"[14]
- "የነጠላ አስተሳሰብን ሆነ . . . እግዚአብሔር በሚታየው ድርጅት ያዘጋጀውን ምክር ያለመቀበል አስወግዱ"[15]
- "የነጠላ ሐሳቦትን ተዋጉ"[16]
- "ጥገኛ ያልሆነን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሳይሆን ጥገኛ የሆነን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን ፈልጉ"[17]

14. The Watchtower, 1 May 1957, ገጽ. 274
15. The Watchtower, 15 January 1983, ገጽ. 22
16. ዚኢ ከማሁ ገጽ 27
17. The Watchtower, 15 September 1911, ገጽ. 4885

- "ከጆሆቫ የማይታይ ላይ ልባችንን ካላደረግን በስተቀር መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል መረዳት አንችልም"[18]
- "ጆሆቫንም ሆነ የድርጅቱን ሰዎች የምናፈቅር ከሆነ ተጠራጣሪዎች አንሆንም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው የመጠበቂያ ድርጅት የሚያመጣውን 'ሁሉ ነገር ማመን ነው' "[19]
- "[እግዚአብሔር] ከሚታየው ድርጅቱ በስተቀር መንፈስ ቅዱስን ሆነ ቃሉን መረዳትንና ማድነቅን አይሰጥም"[20]



## የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን የአምላክ ድርጅት ነውን?



የይሖዋ ምስክሮች ከኤፌ. 4፥5 "አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት" በሚለው ጥቅስ ላይ በመደገፍ "አንድ እውነተኛ የሃይማኖት ድርጅት ብቻ አለ" የሚለው ትምህርት ፍጹም ትክክል አይደለም። ምክንያቱም ክፍሉ "አንድ ሃይማኖት" አለ እንጂ "አንድ ድርጅት ብቻ አለ" አላለም። ሰዎች በጥቃቅን አስተምህሮዎች ላይ የተለያየ አመለካከት ስላላቸው በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ አሉ (ሮሜ 14)። ነገር ግን በመሠረታዊው የቃለ እግዚአብሔር አስተምህሮት ላይ ተመሳሳይ የእምነት አቋም አላቸው።

እርግጥ ነው ዮሐ. 10፥16 "አንድ መንጋ" አለ ይላል። ነገር ግን "አንድ መንጋ" አለ ማለት አንድ "የሃይማኖት ድርጅት ብቻ አለ" ማለት በፍጹም አይደለም። ከክፍሉ ዐውደ ንባብ የምንማረው ነገር ይህ "መንጋ" የእረኛውን፥ የክርስቶስን ድምፅ የሚሰማ፥ እርሱ የሚያውቃቸው፥ እነርሱም የሚያውቁት ማለት ነው (ቁ. 7–9, 11, 14–15, 26–27) እንጂ "አንድ መንጋ" ማለት በአንድ የሰበአዊያን ድርጅት የታቀፈ ማለት አይደለም።

18. The Watchtower, 1 October 1967, ገጽ. 587
19. Qualified to the Ministers, (1955), ገጽ. 156
20. The Watchtower, 1 July 1965, ገጽ. 391 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም



በአንደኛ ቆሮ. 1፥10 በመመሥረት የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት "ዛሬ የሚታየው የሃይማኖት መከፋፈል ድርጅቶቹ ሐሰተኛነታቸውን የሚያሳይ ነው" የሚለው ትምህርቱን ለማስደገፍ ብቻ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰ ጥቅስ እንጂ የክፍሉን ትምህርት የሚያንጸባርቅ አይደለም። ጳውሎስ በዚህ ክፍል ክርስቲያኖች ጠንካራ ኅብረት መፍጠር እንዳለባቸው ያስተምራል እንጂ ያለመግባባታቸው ወይም መለያየታቸው ከትክክለኛው መሠረተ እምነት መውጣታቸውን ወይም ሐሰተኛ ሃይማኖት መከተላቸውን ለማሳየት በፍጹም አይደለም። ምንም እንኳ በመካከላቸው "እኔ የጳውሎስ ነኝ፥ እኔስ የአጵሎስ ነኝ፥ እኔ ግን የኬፋ ነኝ፥ እኔስ የክርስቶስ ነኝ" የሚል መለያየት ቢኖራቸውም ጳውሎስ ግን እነዚህን ሰዎች "ወንድሞች" (1ቆሮ. 1፥2) ነበር የሚላቸው እንጂ "በልባምና ታማኝ ባሪያ" የሚመራ ሃይማኖታዊ ድርጅት ይኑራችሁ በፍጹም አላለም።

ከላይ እንደተመለከትነው የይሖዋ ምስክሮች በማቴ. 24፥45–47 "ልባምና ታማኝ ባሪያ" የሚለው አገላለጽ ክርስቲያንን በአጠቃላይ የሚያሳይ ሳይሆን ድርጅቱ የክርስቶስ ቅቡዓ ተከታዮች [ የ144 ሺው] በድርጅት ደረጃ የተሰበሰቡትን ብቻ የሚያሳይ ነው። እነዚህም የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር ዋና መሥሪያ ቤት የአመራር አካላት ናቸው የሚል የእምነት አቋም አላቸው።

ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ክፍል ላይ የሚናገረው ለተለዩ ወይም ለተወሰኑ "ባሮች" ሳይሆን በአጠቃላይ ለታማኝ ባሮችና ታማኝ ላልሆኑ ባሮች ጭምር ነው። "ባሪያ" ከሚለው ቃል ፊት ያለው የተወሰነ መስተፃምር ለተወሰነ ወይም ለተለየ ባሪያ የተጠቀሰ ነው የሚለው የድርጅቱ ትንታኔ ከእንግሊዝኛም ሆነ ከግሪክ ሰዋስው እውነት እጅግ የራቀ ነው። በእንግሊዝኛም ሆነ በግሪክ ሰዋስው ነጠላ ቁጥር በሚያሳይ ስም ፊት የተወሰነ መስተፃምር መኖር አጠቃላይ የሆነ ነገር ሊያመለክት ይችላል [ለአብነት ያህል አንድ የእንግሊዝኛ ዐረፍተ ነገር እንመልከት፦ The Wise person plans ahead. በዚህ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ብልኅ [Wise] የሚለው ቃል የዐረፍተ ነገሩ ባለቤት ነው። ከእርሱ ፊት ያለው የተወሰነ መስተፃምር [the] ብልኅ [Wise] የሚለውን ቃል የተወሰነ ብልኅ ብቻ እንዲያመለክት አላደረገውም፤ ነገር ግን ብልኅ የሚለው ነጠላ ስም አስቀድሞ የሚያቅድን ማንኛውንም ብልኅ ሰው የሚያመለክት ነው።]

የክፍሉም ዐውድ የሚያመለክተው በአጠቃላይ ታማኝ ስለሆኑና ታማኝነት ስለጎደላቸው ባሮች ነው። ጌታ እየተናገረ ያለው እርሱ

የሚናገረውን ሁሉ ስለሚያደርግ ወይም ስለሚጠብቅ ባሪያ አይደለም፤ ራሱን "ልባምና ታማኝ ባሪያ" ብሎ ስለሰየመ ለአንድ የሃይማኖት ድርጅት የአመራር አካላት አይደለም።

በየሐዋ. 15 ላይ የምናነበው የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ስብሰባ የማንኛውንም የሃይማኖት ድርጅት የሚወክል አይደለም። እንደ ይሖዋ ምስክሮች ትምህርት የኢየሩሳሌሙ ጉባዔ በአሜሪካን አገር የሚገኘውን የድርጅቱን የአመራር አካላት በፍጹም ሊወክል አይችልም። ምክንያቱም የኢየሩሳሌሙ ስብሰባ በበጉ (በኢየሱስ) ሐዋርያት ብቻ የተካሄደ ነበር። የይሖዋ ምስክሮች ደግሞ በመካከላቸው ሐዋርያት እንደሌሉ በበርካታ ጽሑፎቻቸው ገልጸዋል። አሥራ ሁለቱ የበጉ ሐዋርያት እስከሌሉ ድረስ የትኛውም ሃይማኖታዊ ስብሰባ ይህን የኢየሩሳሌሙን ስብሰባ ሊወክል ወይም በእርሱ ሊመሰል አይችልም።

"ቃለ እግዚአብሔርን ለመረዳት የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት አስፈላጊ ነው" ለሚለው የይሖዋ ምስክሮች ትምህርት የተጠቀሰው ከየሐዋ. 8፥30–31 ላይ ነው። ፊሊጶስ የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ የነበረውን ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ". . . በእውኑ የምታነበውን ታስተውለዋለህን? " አለው። ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም፡– ". . . የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል?" አለው። ፊሊጶስም ጃንደረባውን ያስተምረው ዘንድ ተቀመጠ። "ዩር ዊል ቢ ዳን ኦን ኧርዝ" ["ፈቃድህ በምድር ይሁን"] በሚል ርዕስ የታተመው የመጠበቂያ ድርጅት መጽሐፍ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ እንዲህ ይላል፡– "የእግዚአብሔርን ቃል ለመረዳትም ሆነ ፈቃዱን ለማወቅ የተቀናጁና ራሳቸውን ለእርሱ [ለእግዚአብሔር] የሰጡ ሰዎች ያስፈልጋሉ። ኢትዮጵያዊው ጃንደረባም የተገነዘበው ይህንኑ ነው"[21]።

በእርግጥ የይሖዋ ምስክሮች ቃለ እግዚአብሔርን የሚያነቡት በክፍሉ ውስጥ የሌለውን ነገር እየጨመሩ ነው የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት አነጋገር ትክክል ነው። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን እንዲረዱ ሰዎች ሊመሯቸው እንደሚያስፈልግ ክፍሉ ማስተማሩ እሙን ነው። ሐዋርያው ጴጥሮስ እንኳን አንዳንድ የጳውሎስ መልእክቶች ለመረዳት አስቸጋሪ እንደሆኑ ተናግሮአል (2ጴጥ. 3፥16)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለመረዳት አስቸጋሪ የሆኑ ነገሮች ስላሉ ነው እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን አስተማሪዎችን የሰጠው (ኤፌ. 4፥11)።

21. Your Will Be Done On Earth. (1958) ገጽ. 362 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።



ክፍሉ የእግዚአብሔር እውነተኛ ተከታዮች ሁሉ ሊቀበሉት የሚገባ ሥልጣናዊ ቃል ስለሚያስተላልፍ ድርጅት አይናገርም። ፊሊጶስ ደግሞ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ከመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ እየጠቀሰ አስተማረው እንጂ በድርጅት በተጻፉ ተጨማሪ ጽሑፎች ረዳትነት አልነበረም። ይህም ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ ተጠመቀ (የሐዋ. 8፥34–48)።

"ከውኃውም ከወጡ በኋላ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ነጠቀው ጃንደረባውም ሁለተኛ አላየውም፥ ደስ ብሎት መንገዱን ይሄድ ነበርና።" (የሐዋ. 8፥39) ይህ ክፍል ፊሊጶስና ጃንደረባው ዳግም እንዳልተገናኙ ነገር ግን ጃንደረባው በአዳኙ እየተደሰተ መንገዱን እንደቀጠለ ነው የሚናገረው እንጂ ራሱን ለአንድ ድርጅት እንዳስገዛ የድርጅቱንም ጽሑፍ መጽሐፍ ቅዱስንም ለመረዳት ተጠቀመበት አይለንም።

የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር መጽሐፍ ቅዱስ በግል ተጠንቶ መብራራት እንደሌለበት ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን ማብራራት የድርጅቱ ሥራ ብቻ እንደሆነ ለሚያስተምረው ትምህርት ከቃለ እግዚአብሔር ከሚጠቅሰው ጥቅስ መካከል አንዱ (2ጴጥ. 1፥20–21) ነው። ክፍሉ ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዴት መተርጎም እንዳለብን ሳይሆን የሚያስተምረው ቅዱሳት መጻሕፍት እንዴት እንደተጻፉ ነው። ቁ. 20–21 "ይህን በመጀመሪያ ዕወቁ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ"። "ሊተረጉም" የሚለው ቃል ትንቢት የመጣው በነቢያቶቹ ፍላጎት ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን የሚያሳይ ነው። "ተነድተው" የሚለው ቃል ከድሮ መርከብ አንዳድ የተወሰደ ሥዕላዊ አገላለጽ ነው። የጥንት መርከቦች ሞተር ስላልነበራቸው የሚሄዱት በነፋስ ኃይል ነበር። ነፋሱ በበረታ ጊዜ የመርከቧ ሾፌር መቆጣጠር ስለማይችል ነፋሱ ወደፈለገበት ቦታ ነድቶ መርከቡን ይወስዳል። ሉቃስ ይህን ቃል በሐዋርያት ሥራ ላይ ተጠቅሞበታል (የሐዋ. 27፥15, 17)። እንደዚሁም ሁሉ መንፈስ ቅዱስ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊያንን መርቶአቸዋል፥ የጽሑፋቸውም የበላይ ተቆጣጣሪ እርሱ ነበር።

ይህ የሚያሳየን 2ጴጥ. 1፥20–21 መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደተገኘ ያስተምራል እንጂ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት አተረጓጎም አይደለም። ከመጠበቂያ ግንብ ጋር በተቃረነ መልኩ ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቲያኖች ማንኛውንም ዓይነት ትምህርት፥ የግለሰቦችንም ሆነ

የሃይማኖት ድርጅቶችን መመርመር እንዳለባቸው አስተምሮአል (1ተሰ. 5፥21) የቤርያ ክርስቲያኖች ማንኛውንም ዓይነት ትምህርት፥ የጳውሎስን ትምህርት እንኳ ጨምረው ይመረምሩ ነበር (የሐዋ. 17፥11)። እግዚአብሔር እምነታችንን እንድንመረምር ይፈልጋል።

የተለያዩ ትምህርቶችን የምንመረምረው ቃለ እግዚአብሔር ምን እንደሚል አጥንተንና ተረድተን ነው። እግዚአብሔር ያለምንም ጥያቄ የመጠበቂያ ግንብ ጽሐፍን እንድንቀበል አይፈቅድም "በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ ራሳችሁን ፈትኑ. . ." (2ቆሮ. 13፥5)።

በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው ቀኖናዊና እንከን አልባ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል (ማቴ. 5፥17-18፤ ዮሐ. 10፥34-35)። መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፈው፤ አስተምህሮዎችና የእምነት አንቀጾች የሚመዘኑበት፥ የለበአዊያን ልምምዶችና አካሄዶች የሚገሩበት የእግዚአብሔር እስትንፋሳዊ ቃል ነው (2ጢሞ. 3፥16፤ 2ጴጥ. 1፥20-21)። እንደዚሁም ማንኛውም ዓይነት ትምህርቶች ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ በትክክል ሊመዘኑ ይገባቸዋል፤ ምክንያቱም እንከን የሌለበት የእግዚአብሔር እስትንፋሳዊ ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው። ይህም የሐዋርያትንም ሆነ (የሐዋ. 17፥11) የነቢያትን (2ጴጥ. 2፥1) ትምህርት ጨምሮ ማለት ነው። ጳውሎስ ለገላቲያ ቤተ ክርስቲያን አማኞች አዲስ ወንጌልን መቀበል በፍጹም እንደሌለባቸው ይመክራል (ገላ. 1፥8)።

## የመጠበቂያ ግንብ ማኅበርን አስመልክቶ ጥይቄ ለይሖዋ ምስክሮች


1. ቅቡዓ አማኞች በድርጅት መልክ ተዋቅረው "ልባምና ታማኝ ባሪያ" የተባሉት በአሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከሆነ፥ እነዚህም ሰዎች ቃለ እግዚአብሔርን ለመረዳት ብቸኛ መንገድ ከሆኑ ለአንድ ሺ ዘጠኝ መቶ ዓመታት እግዚአብሔር በምድር ላይ እውነተኛ ወኪል የለውም ነበር ማለት ነው? በዚያን ዘመን የነበሩ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት ይረዱ ነበር?
2. እግዚአብሔር በነዚህ ዘመናት የነበሩ ሰዎች ቅዱስ ቃሉን እንዲረዱ አይፈልግም ነበር ማለት ነው?
3. የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ከመቋቋሙ በፊት ሰዎች ቃለ እግዚአብሔርን እንዴት ይረዱ ነበር?



4. መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት የመጠበቂያ ግንብ ጽሑፎች አንገብጋቢ ከሆኑ፤ መጽሐፍ ቅዱስን ሰጥቶ የመረጃውን መንገድ የከለከለው እግዚአብሔር ምን ዓይነት ነው?
5. ሰዎች በሃይማኖት ድርጅት ሥር መጠለል እንዳለባቸውና ለድርጅቱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንተና መገዛት እንደሚገባቸው የሚያስተምረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የት ጋ ነው የሚገኘው? [የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር የሚጠቅሰው ጥቅስ የፊሊጶስንና የኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ታሪክ ነው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ፊሊጶስና ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ዳግም እንዳልተገናኙ ይናገራል]።
6. ፊሊጶስ ከኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ጋር የተወያየው በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነበር ወይስ ተጨማሪ መጻሕፍትንና መጽሔቶችን ተጠቅሞ ነበር?
7. ለኢትዮጵያዊው ጃንደረባና ለፊሊጶስ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ በቂ ከሆነ ለእኛስ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ፥ ያለተጨማሪ ጽሑፎች በቂ መሆን አይችልም?
8. ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ "ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል"። (2ጢሞ. 3፥15) ይለዋል። ለጢሞቴዎስ መጽሐፍ ቅዱስን *ብቻ* ማወቁ ለደኅንነት በቂ ከሆነ ለእኛ በቂ የማይሆንበት ምክንያት ምንድን ነው?
9. የቤርያ ሰዎች የጳውሎስን ትምህርት የመፈተን መብት ነበራቸው (የሐዋ. 17፥11)። ጳውሎስ ራሱ ሁሉን ነገር መመርመር እንዳለብን ይናገራል (1ተሰ. 5፥21)። የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ይህንን ትዕዛዝ መከተል የለባቸውምን? እግዚአብሔር ሁሉን ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ መመዘን እንዳለብን ካዘዘን፥ የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር ጽሑፎች ሁሉ በቃለ እግዚአብሔር ልንመዝናቸው ይገባል ማለት ነው። እርሶ የመጠበቂያ ግንብ ማኅበርን ጽሑፎች በመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ለመመዘን ፈቃደኛ ነዎት?
10. በርካታ የመጠበቂያ ግንብ ጽሑፎች ከአምላክ ቃል ጋር በቀጥታ የሚቃረኑ ከሆነ ምን ያደርጋሉ?
11. በቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ዘንድ የነበረው መለያየት የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ክርስቲያን አይደሉም እንድንል ያደርገናልን? (1ቆሮ. 1፥2 ይመለከቷል)
12. 1ቆሮ. 1፥10 በሃይማኖት ድርጅቶች መካከል ስላለው መለያየት ይናገራልን?
13. 1ቆሮ. 1፥10 የክርስቲያኖች ኅብረት የሚታየው በአንድ የሃይማኖት ድርጅት ጥላ ሥር መጠለላቸው ነው ይላል?

14. "ሁሉን ይበላ ዘንድ እንደ ተፈቀደለት የሚያምን አለ፥ ደካማው ግን አትክልት ይበላል። የሚበላ የማይበላውን አይናቀው የማይበላውም በሚበላው አይፍረድ፥ እግዚአብሔር ተቀብሎታልና። አንተ በሌላው ሎሌ የምትፈርድ ማን ነህ? እርሱ ቢቆም ወይም ቢወድቅ ለገዛ ጌታው ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ሊያቆመው ይችላልና ይቆማል"። (ሮሜ 14፥2–5) በዚህ ክፍል መሠረት ክርስቲያኖች በአንዳንድ ሃይማኖታዊ ትምህርቶች ላይ የተለያየ አቋም መያዛቸው ተቀባይነት ያለው አይመስልዎትም?

## 3.2 የይሖዋ ምስክሮችና የአምላክ ስም



ሐምሌ 26 ቀን 1931 ዓ.ም. በኮሎንበስ ኦሀዮ በተደገው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የአባላት ስብሰባ ላይ የድርጅቱ ሁለተኛ ፕሬዚዴንት፥ ጆሴፍ ፍራንክሊን ሮዘርፎርድ ለድርጅቱ ተከታዮች "የይሖዋ ምስክሮች" የሚል ስያሜ አወጣ[1]። በዚህ አዲስ ስያሜ ብዙ የድርጅቱ አባላት ደስ ከመሰኘታቸውም በላይ አዲሱን ስያሜ ተቀብለውታል። ምክንያቱም አዲሱ ስያሜ የድርጅቱ ተከታዮች ቀድሞ ይጠሩባቸው የነበሩትን የተለያዩ ቅጽል ስሞች ስለሚያስቀር ነው። እነዚህ ቅጽል ስሞች፥ " 'ራስላውያን፥ ሮዘርፎርድውያን'፥ 'የመጠበቂያ ግንብ ስሞች'፥ 'የሺ ዓመት ንጋቶች' "[2] የሚባሉት ነበሩ።

ይህ ለድርጅቱ ተከታዮች መጠሪያ እንዲሆን የተሰጠው አዲስ ስም የተወሰደው ከኢሳይያስ 43፥10–12 ሲሆን፤ እንደ ድርጅቱም እምነት የአምላክ ብቸኛ መጠሪያ ስም ጆሆቫ ነው[3]። ይህንንም ስም የግድ ልንጠቀምበት ያስፈልገናል ባዮች ናቸው[4]።

እንደ ይሖዋ ምስክሮች ትምህርት ይህን የተቀደሰ የአምላክ ስም ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያስወገዱት የዕብራውያን ጣኦት አምላኪ ጸሐፍት ናቸው። ነገር ግን ልንጨነቅ አይገባንም! ምክንያቱም የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት "የአዲሲቱ ዓለም የቅዱሳን ጽሑፎች ትርጉም" ["አው ወርልድ ትራንስሌሽን ኦፍ ዘ ሆሊ ስክሪብቸርስ"] በሚል ስያሜ ያሳተመው መጽሐፍ ቅዱስ የአምላክን ስም "በታማኝነት" በማደስ YHWH [YHWH - ቴትራግራማቶን በመባል ይታወቃል] በመባል

1. The 1975 Year book of Jehovah's Witnesses, ገጽ. 149
2. The Watchtower, Feb. 15,1962. ገጽ. 119
3. Make sure of All Things Hold Fast to What Is Fine. ገጽ. 264
4. ዝኒ ከማሁ



የሚታወቀው የእግዚአብሔር ስም በሚገኝበት የብሉይ ኪዳን ክፍሎች ሁሉ ላይ ጆሆቫ የሚለውን ቃል መልሶአል። ይህም ብቻ አይደለም፤ ጆሆቫ የሚለው የአምላክ ስም ድርጅቱ ባሳተመው መጽሐፍ ቅዱስ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ሁሉ ላይ ይገኛል። የአዲሲቱ ዓለም ትርጉም [NWT] የተርጓሚዎች ኮሚቴ የአብን ስም ያሳያሉ በሚባሉ ቦታዎች ሁሉ ላይ ስሙን አስገብቶአል።

በየቤታችን በር ላይም ሆነ በየመንገድ ዳር የምናገኛቸው የይሖዋ ምስክሮች ጆሆቫ የሚለውን የአምላክ ስም መጠቀም እጅግ አንገብጋቢ፥ እንደሆነም የሞትና የሕይወት ጉዳይ እንደሆነ ከአዲሲቱ ዓለም ትርጉም [NWT] ሮሜ 10፥33 "የጆሆቫን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና" እና ሕዝቅኤል 39፥6 "እኔም ጆሆቫ እንደሆንኩ ሕዝቦች ማወቅ አለባቸው" የሚለውን በመጥቀስ ይሞግቱናል።

እንደ ይሖዋ ምስክሮች የሥነ-መለኮት አቋም ኢየሱስ ክርስቶስ ጆሆቫ ሳይሆን ሊቀ መልአክ ሚካኤል ነው። ይህን ትምህርት አስመልክቶ ከድርጅቱ የሚወጡ ጽሑፎች እንዲህ ይላሉ:– "ኢየሱስ ክርስቶስ ሰማይን ከመተው በፊትና ወደ ሰማይ ከተመለሰ በኋላ ሚካኤል የሚለው ስም የኢየሱስ ክርስቶስ ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ አለ"[5]። "ሚካኤል ታላቅ መልአክ ነው፤ ይህም ከኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ አይደለም"[6]። እንደ መጠበቂያግንብ አስተምህሮ ኢየሱስ ኃያል አምላክ ነው። ነገር ግን እንደ ጆሆቫ ሁሉን ቻይ አምላክ አይደለም[7]።

አብ ብቻ ጆሆቫ ለመሆኑ የይሖዋ ምስክሮች አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቅሱት ጥቅስ ሉቃ. 4፥8 ነው። ክፍሉ በአዲሲቱ ዓለም ትርጉም [NWT] እንዲህ ይነበባል "ልታመልኩት የሚገባችሁ አምላካችሁ ጆሆቫ ነው፤ ለእርሱም ብቻ ነው የተቀደሰ አገልግሎት መስጠት የሚገባችሁ"። ይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ ክርስቶስ ጆሆቫ ከሆነ ኢየሱስ ጆሆቫ አይደለም ማለት ነው ይሉናል።

የይሖዋ ምስክሮች ጆሆቫ ስለሚለው የአምላክ ስም ያላቸውን አስተምህሮ በቃል እግዚአብሔር ላይ ለማስደገፍ ከሚጠቅሱአቸው ጥቅሶች መካከል:– ዘጸ. 3፥15 እና ማቴ. 6፥9 ዋንኞቹ ናቸው። ጥቅሶቹን አስመልክቶ ከድርጅቱ የሚወጡ የድርጅቱ እንድምታዎች

5. The Watchtower, 15, May 1969, ገጽ. 307
6. The watchtower, 15, December 1984, ገጽ.29
7. ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር (1994) ገጽ. 150

እንዲህ ይላሉ፦ ዘጸ. 3፥15 – ጆሆቫ የሚለው ስም የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ስም ነው። ሙሴ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ በጠየቀው ጊዜ እግዚአብሔር የመለሰለት፦ "ለእስራኤል ልጆች እንዲህ በላቸው፤ ጆሆቫ እግዚአብሔር የአባታችሁ አምላክ፥ የአብርሃም አምላክ፥ የይስሐቅ አምላክ እና የያዕቆብ አምላክ ወደ እናንተ ላከኝ፤ ይህም ከትውልድ ትውልድ የመታሰቢያ ስሜ ነው" [የአዲሲቱ ዓለም ትርጉም NWT]።

አምላክ ለዘላለም ሊጠራበት የሚገባው ስም ጆሆቫ ነው። "በሃያኛው ክፍለ ዘመን ላለው ትውልድም ሆነ ለኛ ከ1914 ጀምሮ ላለው ትውልድ የዘላለሙ አምላክ መጠሪያ ስም ጆሆቫ ነው። ይህ ለዘላለም ለእርሱ መታሰቢያ መጠሪያ ስም ነው። ለዘላለምም እኛ እርሱን የምናስበው በዚህ ስም ነው። ይህ የእርሱ የማይለወጥ ስም ነው። ከሰው ፍጥረት ጀምሮ እስከ ሙሴ ዘመን ይህ [ስም] አልተለወጠም ከሙሴ ጀምሮ 1914 እንዲሁም እስከ አሁን ይህ ስም [ጆሆቫ] አልተለወጠም። በእነዚህ ሺ ዓመታት ውስጥ ያልተለወጠውን ስም በአግባቡ መጠቀም ይገባናል"[8]።

በማቴ. 6፥9 የተባልነው "ስለዚህ በዚህ መልኩ ልትጸልዩ ይገባችኋል፦ በሰማይ የምትኖር አባታችን፥ ስምህ ይቀደስ" [NWT]። እንደ ድርጅቱ አስተምህሮ የእግዚአብሔር ስም የሚቀደስበት ብቸኛው መንገድ አምላክን በእውነተኛ ስሙ[ጆሆቫ] ስንጠራው ነው[9]። ጸሎታችን በእርግጥ እንዲሰማልን ከፈለግን እግዚአብሔርን በዚህ ስም እየጠራ ነው ልንጸልይ ይገባል። እግዚአብሔርን በሌላ ስም መጥራት አምላክን ያለማክበር ነው[10]።

እንደ መጠበቂያ ግንብ ማኅበር አስተምህሮ የተቀደሰውን የአምላክ ስም ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያስወገዱት ጣኦት ያመልኩ የነበሩት ዕብራውያን ጸሐፍት ናቸው። እንደዚሁም በዚህ ዘመን ያሉ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች ጆሆቫ የሚለውን የእግዚአብሔር ስም በመተው ሰውን እያሳሳቱ ናቸው። በ1961 ዓ.ም. የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር ከማቴ. 6፥9 በመዋስ "ስምህ ይቀደስ" ["ሊት ዮር ኔም ቢ ሳንቲፋይድ"] በሚለው ርዕስ ያሳተመው መጽሐፍ እንዲህ ይላል፦

8. "Let your Name Be Sanctified" ገጽ. 88። በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።
9. Let God Be True ገጽ. 28
10. Let Your Name Be Sanctified



"መጽሐፍን [መጽሐፍ ቅዱስን] በተለያዩ ቋንቋዎችና የአነጋገር ዘዬዎች የመተርጎሙ ሂደት ቀጥሎአል። ይህ መጽሐፍ ለብዙ ሰዎች መዳረሱ የዘላለም ሕይወታቸውን በአደጋ ላይ ይጥለዋል። ምክንያቱም ከነዚህ ትርጉሞች የፈጣሪያችንን ስም መማር ስለማንችል ነው። ከስሙ ይልቅ ሌላ ቃል ወይም ስም ነው የሚጠቀሙት። በነዚህ ትርጉሞች ስሙ [የአምላክ ስም] አልተከበረም ወይም አልተቀደሰም፤ ከአንባቢዎቹ ለደኅንነታቸው የሚሆናቸውን ስም እንዳያውቁት ተደብቆባቸዋል"[11]።

ለደኅንነት ይጠቅማል የተባለው "ስም" እንዴት ሊታወቅ እንደቻለ ይኸው የመጠበቂያ ግንብ መጽሐፍ እንዲህ በማለት ያብራራል፦ "በልባችን የራሳችን የሆነ ዘላለማዊ ፍላጎት ካለን፥ ራሳችንን ከእግዚአብሔር ጋር ለማስተዋወቅ የምንጓጓ ከሆነ፥ ብዙ የክርስቲያን ድርጅቶች በተሳሳተ መልኩ እንዳቀረቡት ሳይሆን እርሱን እንደ እርሱነቱ ለማወቅ የስሙን መጽሐፍ፥ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብና በማጥናት ወደ ትክክለኛው መረዳት መድረስ እንችላለን፤ እንዲሁም ራሳችንን ከተፈተነው ከእርሱ የሚታይ ድርጅት፥ 'ለእርሱ ስም በሆኑ ሰዎች'፥ ቅሬታ ከሆኑ ቅቡዓ ምስክሮች፥ ልባምና ታማኝ ባሪያዎች ጋር ፍጹም መተባበር ነው"[12]።

በአጠቃላይ የይሖዋ ምስክሮች እንደሚያምኑት እኛ ብቻ የእግዚአብሔርን እውነተኛ ስም በትክክል ስለምንጠራ የአምላክ እውነተኛ ተከታዮች እኛ ነን። በእኛ የሃይማኖታዊ ድርጅት ጥላ ሥር ያልተጠለለ ሁሉ የሰይጣን እንደራሴ ነው ባዮች ናቸው።



## የይሖዋ ምስክሮችና የአምላክ ስም በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን



ሃያ ሰባቱም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በመጀመሪያ የተጻፉት በግሪክ ቋንቋ ነው። የመጀመሪያ ቅጂ ጸሐፊያን ጌታ፥ አምላክ ወይም እግዚአብሔር ለሚሉት ስሞች የተጠቀሙበት ቃል፦ ጌታ [በግሪክ፦ "ኩሩዮስ"]፥ እግዚአብሔር ወይም አምላክ [በግሪክ፦ ቴዎስ] የሚለውን ስም ነው። እነዚህ የአዲስ ኪዳን ጸሐፊያን ጆሆቫ ወይም ያህዌ የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል አንድም ጊዜ በጽሑፎቻቸው

11. ዝኒ ከማሁ ገጽ 12። በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።
12. ዝኒ ከማሁ ገጽ 374–375

አልተጠቀሙም። የአዲስ ኪዳን ጸሐፊያን ብዙ የብሉይ ኪዳን ክፍሎችን ጠቅሰው ጽፈዋል። ነገር ግን ይህን ስም ቴዎስ [አምላክ] ወይም ኩሩዮስ [ጌታ] በሚሉት የግሪክ ቃላት ነበር የተኩት።

የጥንት ዕብራውያን ያህዌ [YHWH] የሚለውን የእግዚአብሔር ስም መጥራት ስለሚፈሩ በዚህ ስም ፈንታ አዶናይ [Adonai] የሚለውን የአምላክ ስም ይጠቀሙ ነበር። ይህን የአምላክ ስም መጥራት እንዲፈሩ ያደረጋቸው የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ የሚለውን፥ ከአሥርቱ ትዕዛዛት ሦስተኛውን ሕግ እንዳያፈርሱ በመጠንቀቅ ያህዌ [YHWH] ከሚለው ስም ይልቅ አዶናይ [Adonai] የሚለውን የእግዚአብሔር ስም ይጠቀሙ ነበር።

የጥንት ዕብራውያን ድምፅ ተቀባይ ፊደላትን [Consonants] ብቻ በመጻፍ በሚያነቡበት ጊዜ ብቻ ድምፅ ሰጪ ፊደላትን [Vowels] እያስገቡ ጽሑፋቸውን ያነቡ ነበር። በኋላ የዕብራይስጥ ቋንቋ እያደገ ስለመጣ ድምፅ ተቀባይ ፊደላትን [Consonants] ከድምፅ ሰጪ ፊደላት [Vowels] ጋር አብሮ መጻፍ ተጀመረ። ነገር ግን ዕብራውያን ያህዌ [YHWH] የሚለውን ስም እግዚአብሔርን ከመፍራትና ስሙን ከማክበር የተነሣ ስለማይጠሩት ቋንቋው ሲያድግ የቀድሞው ትክክለኛ አነባበብ [Pronunciation] አዲሱ ትውልድ ሳያውቀው ቀረ። ይህን ችግር ለመቅረፍ ዕብራውያን አጅናይ በሚለው ስም ላይ የሚገኙትን ድምፅ ሰጪ ፊደላት ማለትም፦ " 'A'፥ 'O'፥ 'A' "ን YHWH በሚለው ድምፅ ተቀባይ ፊደላት ውስጥ በመጨመር Yahowah ተብሎ እንዲነበብ አደረጉ [YHWH የሚለውን ቃል ምንም ብለን ማንበብ አንችልም። ምክንያቱም ድምፅ ተቀባይ ብቻ ስለሆነ። ለማንበብ የግድ ድምፅ ሰጪ ፊደል ያስፈልጋል]። ለዚህም ነው ያህዌ የሚለው ስም ሰው ሠራሽ ስም ነው የሚባለው። ይህን እውነት የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ይቀበለዋል[13]። በአጠቃላይ ያህዌ የሚለው ስም ቴትራግራማቶን [YHWH] ሊነበብበት ከሚችለው ከብዙ አማራጮች አንደኛው ነው። ነገር ግን ጆሆቫ የሚለው አነባበብ ሊሆኑ ከሚችሉ የተለያዩ የአነባበብ አማራጮች እጅግ የራቀ ነው። ለዚህም ነው የተለያዩ መድበለ ዕውቀቶች [Encyclopedias] ጆሆቫ የሚለው አጠራር እጅግ የተሳሳተ ነው የሚሉት። አንዳንዶቹን ለአብነት ያህል ከዚህ እንደሚከተለው አቅርበናቸዋል[14]፦

13. ክቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር፣ ገጽ 195

14.. Personal Freedom Outreach – Why the Name Jehovah's Witnesses? በሚል ስያሜ ካሳተመው ትራክት ላይ የተወሰደ ነው



- ጆሆቫ፦ "ለብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ስም ትክክል ያልሆነ ቅምር ነው።"[15]
- ጆሆቫ፦ "ለእስራኤል አምላክ የተሳሳተ ስም"[16]
- ጆሆቫ፦ "ለእግዚአብሔር መጠሪያ YHWH ለሚለው የዕብራይስጥ ስም የተሳሳተ አነባበብ ነው። በሰዋስው ሕግ ይህ ንበት ፍጹም የማያስኬድ ነው።"[17]
- ጆሆቫ፦ "ባዕድ ከሆነ ድምፅ ሰጪ ፊደላት ተዋቅሮ ጆሆቫ በመባል በስህተት የተነበበ"[18]
- ጆሆቫ፦ "ሰው ሠራሽ"[19]
- ጆሆቫ፦ "ለእስራኤል የቃል ኪዳን አምላክ የተሳሳተ መለኮታዊ ስም"[20]
- ጆሆቫ፦ "ያህዌ ለሚለው መለኮታዊ ስም የተሳሳተ መጠሪያ"[21]
- ጆሆቫ፦ "የቴትራግራማቶን የተሳሳተ ንበት"[22]

ጆሆቫ የሚለው ቃል በኪንግ ጀምስ ትርጉም ላይ በአራት ቦታዎች ላይ ተጠቅሶአል (ዘጸ. 6፥3፤ መዝ. 83፥18፤ ኢሳ. 12፥2፤ 26፥4)። እንዲሁም በኒው ኢንግሊሽ ባይብል ሁለት ጊዜ፥ (ዘጸ. 3፥15፤ 6፥3)። የተርጓሚዎቹ ኮሚቴ ቃሉን የተጠቀመበት YHWH የሚለውን የቃል ንበት ማንም በትክክል ስለማያውቀው ነገር ግን በስፋት እየተሠራበት ያለው ቃል ጆሆቫ ስለሆነ ብቻ ነው። ስለዚህ የይሖዋ ምስክሮች የአምላክን ስም በትክክል የምናውቅ እኛ ብቻ ነን ሊሉ በፍጹም አይገባቸውም። ይህን የአምላክ ስም ማንም አያውቀውም።

ዘጸ. 3፥15 እግዚአብሔር በጣም ብዙ ስሞች እንዳሉት መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ጆሆቫ ከሚለውም ስም ሌላ እግዚአብሔር በሌላ ስም ተጠርቶአል። ለምሳሌ በዚሁ ጥቅስ ላይ እግዚአብሔር "የአብርሃም አምላክ፥ የይስሐቅ አምላክ፥ የያዕቆብ አምላክ" ተብሎአል። ይህም ስም

15. Merits Student Encyclopedia (Volume 10, 1973 Edition)
16. Encyclopedia Americana (Volume 16, 1976 Edition)
17. The Jewish Encyclopedia (Volume 7, 1964 Edition)
18. Encyclopedia International (Volume 9, 1974 Edition)
19. The Interpreters Dictionary of the bible (Volume 2,1969 Edition)
20. The New schaff – Herog Encyclopedia (Volume 6, 1910 Edition)
21. The New Catholic Encyclopedia (Volume 7, 1967 Edition)
22. The Universal Jewish Encyclopedia (Volume 6, 1948 Edition)

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ስፍራ ተጠቅሶአል። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ያህዌ በሚለው ስም ቢጠራም በዚህ ስም ብቻ አይደለም የሚታወቀው። ስለዚህ ዘጸ. 3፥15ን በመጥቀስ እግዚአብሔር የሚጠራበት ብቸኛ ስም ያህዌ ነው ማለት በፍጹም አንችልም።

ኢየሱስ ክርስቶስ አባቱን ያህዌ ብሎ ጠርቶት አያውቅም። የይሖዋ ምስክሮች እንደሚሉት እግዚአብሔር አብ ይሖዋ በሚለው ስም ብቻ መጠራት ካለበት ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ይህንን ስም ባለመጥራት ከመስመር ውጪ ነው ማለት ነው [የአዲሲቱ ዓለም ትርጉም (NWT) ተርጓሚዎች 237 ጊዜ ያህል ጆሆቫ የሚለውን ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጨምረዋል]። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስም ሆነ ሐዋርያት በጽሑፎቻቸው ውስጥ አንድም ጊዜ ጆሆቫ የሚለውን ቃል አልተጠቀሙም። ድርጅቱ ለአምላክ ስም ተቆርቋሪ ነኝ በሚል ሽፋን ያለምንም መሠረት ይህንን ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ 237 ጊዜ መጨመሩ የድርጅቱ አባላት የአዲሲቱ ዓለም ትርጉምን አንብበው የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት እንዳያውቁ አድርጓቸዋል። በኋላ ይህንን ጉዳይ በስፋት እንመለከተዋለን።

ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ጸሎት ሲያስተምር "ጆሆቫ አምላክ ሆይ በሰማይ የምትኖር" ብሎ አልጀመረም። ነገር ግን አባታችን ሆይ በሰማይ የምትኖር ብሎ ነው ያስተማረው (ማቴ. 6፥9)። ኢየሱስ ክርስቶስ በሌላም ጊዜ ጸሎቱን በዚህ ሁኔታ ነው ያቀረበው (ማቴ. 11፥25፤ 26፥39–42፤ ማር. 14፥36፤ ሉቃ. 10፥21፤ 22፥42፤ 23፥34)። ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን እርሱ በጸለየበት መልኩ "አባታችን ሆይ" ብለው እንዲጸልዩ ነው ያስተማራቸው። በእርግጥ እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ እግዚአብሔርንም፦ "አባ አባት" ብለን ልንጠራው እንችላለን! ሮሜ 8፥15፤ ገላ. 4፥6። እግዚአብሔርን አባ አባት ብለን መጥራት የምንችል ከሆነ ዘጸ. 3፥15ን በመጥቀስ እግዚአብሔር ሊጠራበት የሚገባው ስም ያህዌ ብቻ ነው ልንል አንችልም።

እንደ አዲስ ኪዳን የግሪክ መጻሕፍት ያህዌ የሚለው ስም አንድም ጊዜ በአዲስ ኪዳን 27ቱም መጻሕፍት ውስጥ አይገኝም። ያህዌ የሚለው ቃል ለእግዚአብሔር መጠሪያ ለትውልድ ሁሉ ብቸኛ ስም ከሆነ በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ መጠቀስ ነበረበት።

ዘጸ. 3፥15 የሚለው ምንድን ነው? ያህዌ የሚለው ስም ከዕብራይስጡ ረዳት ግሥ [Verb "to be"] ጋር የተያያዘ ነው። ይህን ስም በመጀመሪያ የሚገኘው በዘጸ. 3 ላይ ሙሴ እግዚአብሔር በምን ስም እንደሚጠራ በጠየቀበት ጊዜ ነው። እግዚአብሔርም "ያለና የሚኖር 'እኔ ነኝ' [I



AM WHO I AM" "እኔ [I AM] ወደ እናንተ ላከኝ ትላለህ" (ቁ. 14) አለው። "እኔ" ["I AM" ] የሚለው ቃል ያህዌ የሚለው ቃል አይደለም። ነገር ግን "እኔ" (ቁ. 14) እና "ያህዌ" (ቁ. 15) የሚሉት ቃላት ውልደተ-ቃላቸው ከአንድ ዓይነት ግሥ [Verb "to be"] ነው። በቁጥር 14 ላይ እግዚአብሔር ለሙሴ የገለጸለት "እኔ እኔ ነኝ [*I AM WHO I AM*]" የሚለው ስም የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ባሕርይ የሚያሳይ ነው። ይህ ቃል ነው በቁጥር 15 ላይ ያህዌ የተባለው። የሁለቱም ቃላት ውልደተ-ቃል አንድ ነው በተለዋዋጭነትም አገልግለዋል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ስም ባሕሪን፥ ሥራንና ተፈጥሮን ያሳያል። የአንድ ሰው ወይም ነገርን ስም ማወቅ ባሕሪውን፥ ሥራውንና ተፈጥሮውን ማወቅ ነው። ለዚህም ነው በመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ስምና ባሕሪይ በተለዋዋጭነት ተጽፎ የምናገኘው። ለምሳሌ ያህል መዝሙር ዳዊትን ብንወስድ ይህን እውነት ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል፦ "አቤቱ፥ ስለዚህ በአሕዛብ ዘንድ *አመሰግንሃለሁ፥ ለስምህም* እዘምራለሁ" (መዝ. 18፥49)። "*ለእግዚአብሔር* ተቀኙ *ለስሙም* ዘምሩ፤ ወደ ምድረ በዳ ለወጣም መንገድ አድርጉ፤ *ስሙ* እግዚአብሔር ነው" (መዝ. 68፥4)። "ይህን ፍጥረትህን አስብ ጠላት *እግዚአብሔርን* ተላገደ፥ ሰነፍ ሕዝብም *ስሙን* አስቆጣ" (መዝ. 74፥18)። "አቤቱ *አምላኬ* ሆይ፥ በልቤ ሁሉ *አመሰግንሃለሁ፥* ለዘላለምም *ስምህን* አከብራለሁ" (መዝ. 86፥12)። ከመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የምናየው ነገር እግዚአብሔርና ስሙ እንደማይነጣጠሉ ነው። አንዱን ማወቅ ሌላውን ማወቅ ነው።

የሥነ- መለኮት ሊቃውንት እንደሚያስገነዝቡት ያህዌ የሚለው የእግዚአብሔር ስም የእግዚአብሔርን ዘላለማዊነትና ሉዓላዊነት ያሳያል። ስለዚህ እግዚአብሔር ለሙሴ፦ "ይህ ለዘላለሙ ስሜ ነው፥ እስከ ልጅ ልጅ ድረስም መታሰቢያዬ ይህ ነው" (ዘጸ. 3፥15) ሲለው ለሙሴ የነገረው ስሙን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ማንነቱን ለትውልድ ሁሉ ነው ያስታወቀው። በዚህ ስም ውስጥ የተገለጠው የእግዚአብሔር ማንነት ዘላለማዊነቱና ሉዓላዊነቱ ነው። ከዚህም የተነሣ ትውልድ ሁሉ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊነትና ሉዓላዊነት በማወቅ እንደ ማንነቱ ያከብረዋል።

ስለዚህ ዘጸ. 3፥15 ትኩረት የሚሰጠው ውጫዊ በሆነው በእግዚአብሔር ስም ላይ ሳይሆን ከስሙ በስተጀርባ ያለው፥ ትውልድ ሁሉ ሊያውቀው፥ ክብር ሊሰጠው በሚያስፈልገው የእግዚአብሔር ባሕሪይ ላይ ነው። እግዚአብሔር አምላክ ትውልድ ሁሉ እንዲያውቀው የሚፈልገው ዘላለማዊ የሆነውን ባሕሪውን ነው። ይኸውም ሉዓላዊነቱንና ዘላለማዊነቱን።

እስከ አሁን ከቃለ እግዚአብሔር የተማርነውን ጠቅለል ስናደርገው፦ *አንደኛ፥* እግዚአብሔር አምላክ ያህዌ የሚባል ስም አለው። *ሁለተኛ፥*

ይህን የእግዚአብሔር ስም ትክክለኛ አነባበብ ማንም ሰው አያውቀውም። ሦስተኛ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን ያህዌ በሚለው ስም ጠርቶት አያውቅም። ኢየሱስ እግዚአብሔርን የጠራው አባ፥ አባቴ ብሎ ነው። አራተኛ፥ አማኞች እግዚአብሔርን "አባታችን" ብለው የመጥራት መብት ተሰጥቶአቸዋል። አምስተኛ፥ ያህዌ የሚል ስም በአንድም የአዲስ ኪዳን የግሪክ ቅጂዎች ውስጥ አይገኝም። ስድስተኛ፥ ዘጸ. 3፥15 ትልቅ ትኩረት የሚሰጠው በእግዚአብሔር ስም ላይ ሳይሆን ትውልድ ሁሉ ሊያውቀው በሚገባው ከስሙ በስተጀርባ ባለው የእግዚአብሔር ባሕርይ፥ ሉዓላዊነቱና ዘላለማዊነቱ ላይ ነው።

የይሖዋ ምስክሮች ጆሆቫ የሚለውን ስም ከብሉይ ኪዳን የመጀመሪያ ቅጂዎች ላይ ያስወገዱት ጣኦት አምላኪ የነበሩ ዕብራውያን ጸሐፍት ናቸው የሚለው አነጋገራቸው ፍጹም ሐሰት ነው። እነዚህ ጸሐፊዎች ብሉይ ኪዳንን ሲገለብጡ የማይፈልጉትን ትምህርት እንደዚህ የሚቀንሱ ከሆነ ዛሬ በእጃችን ያሉት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ አይወድቅም?

በመናፍቃን ትምህርት ላይ ብዙ ጥናት ያደረጉ የሥነ–መለኮት ሊቃውንት የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ይሖዋ (ጆሆቫ) የሚለውን ቃል በአዲሲቱ ዓለም ትርጉም [NWT] ውስጥ 237 ጊዜ ያህል ማስገባቱ ይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ ክርስቶስን ከአብ አሳንሰው እንዲመለከቱ አድርጓቸዋል ለምሳሌ እነዚህን ጥቅሶች ከአዲሲቱ ዓለም ትርጉም ይመልከቱ (የሐዋ. 2፥1፤ ሮሜ 10፥13፤ ማቴ. 11፥27፤ ዮሐ. 20፥28። በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ፀውዳቸውን ይመልከቱ)።

ፊሊ. 2፥9–11 ከስም ሁሉ በላይ ስም የተሰጠው ለዚህም ስም "በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥ ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው"። ይህ ጥቅስ ከብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሔር ተሰጥቶ ከነበረው ጥቅስ ጳውሎስ በቀጥታ የወሰደው ነው ኢሳ. 45፥23 "ቃል ከአፌ በጽድቅ ወጥታለች፥ አትመለስም፦ ጉልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል፥ ምላስም ሁሉ በእኔ ይምላል ብዬ በራሴ ምያለሁ"። እውነቱ ይህ ከሆነ ጳውሎስ በዚህ ክፍል የሚያስተምረን ለእግዚአብሔር እውነት የሆነው ሁሉ ለክርስቶስም እውነት መሆኑን ነው።

የአዲስ ኪዳን አማኞች የአብ ምስክር እንዲሆኑ ሳይሆን የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር እንዲሆኑ ነው የተጠሩት። የሐዋ. 1፥8 "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ"።



ማቴ. 6፥9 አምላክን በእውነተኛው ስሙ ጆሆቫ [ይሖዋ] ብለን ስንጠራው ነው ስሙ የሚቀደሰው የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት የለውም። ከላይ ስም ባሕርይንና ማንነትን እንደሚያሳይ ተመልክተናል። የእግዚአብሔርን ስም መቀደስ ወይም ማክበር ማለት በዚያ ስም የሚጠራውን እግዚአብሔር ማክበር ማለት ነው። እግዚአብሔር አምላክ የተቀደሰ ነው። ስምህ ይቀደስ ብሎ መጸለይ እግዚአብሔር በሕዝቡ ዘንድ መከበር እንደሚገባው እንዲከበር መሻታችንን መግለጻችን ነው (ዘጸ. 20፥8፤ ዘሌ. 19፥2፥ 32፤ ሕዝ. 36፥23፤ 1ጴጥ. 1፥15)። እግዚአብሔር የሚከበረው ጆሆቫ! ጆሆቫ! ወይም ይሖዋ! ይሖዋ! እያልን አሥሬ ስለጠራነው አይደለም። ስሙን አሥሬ ጠርተን በምግባራችንና በባሕርያችን ላናስከብረው እንችላለን።

## ኢየሱስ ክርስቶስ ያህዌ ተብሎአል



የይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ ክርስቶስ ያህዌ በሚባለው ስም አልተጠራም ባዮች ናቸው። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ያህዌ በሚለው አምላካዊ ስም ተጠርቶአል።

ያህዌ የሚለው ስም በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ እንደማይገኝ፥ ይህ ስም ቴዎስ (እግዚአብሔር ወይም አምላክ) እንዲሁም ኩሪዮስ (ጌታ) በሚሉት የግሪክ ስሞች እንደተተካ ከላይ ተመልክተናል። ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ ያህዌ ነው የሚለውን ትምህርት ብዙ የብሉይ ኪዳን ክፍሎች ከአዲስ ኪዳን ጋር በመቀናጀት ያስተምሩናል።

በብሉይ ኪዳን ስለ ያህዌ የተነገረው በአዲስ ኪዳን በቀጥታ ለክርስቶስ ተሰጥቶአል። ለምሳሌ፦ ኢሳ. 40፥3 "የአዋጅ ነጋሪ ቃል፦ የእግዚአብሔርን [ያህዌ] መንገድ በምድረበዳ ጥረጉ፥ ለአምላካችንም [ኤሎሒም] ጎዳና በበረሀ አስተካክሉ"። ወንጌላት የነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢት መጥምቁ ዮሐንስ ለኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ በማስተካከሉ እንደተፈጸመ ይናገራሉ (ማር. 1፥2–4፤ ማቴ. 3፥3)። በብሉይ ኪዳን መንገድ ጥረጉልኝ ያለው ያህዌ በአዲስ ኪዳን ክርስቶስ ሆኖ እናገኘዋለን።

ያህዌ መልእክተኛውን እንደሚልክ ፊት ፊቱም በመሄድ መንገዱን እንደሚያስተካክልለት በነቢያት ትንቢት ተናግሮ ነበር "እንሆ፥ መልእክተኛዬን እልካለሁ፥ መንገድንም በፊቴ ያስተካክላል እናንተም የምትፈልጉት ጌታ በድንገት ወደ መቅደሱ ይመጣል የምትወድዱትም የቃል ኪዳን መልእክተኛ እነሆ፥ ይመጣል፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር" (ሚል. 3፥1) አዲስ ኪዳን በያህዌ ፊት ፊት በመሄድ መንገድ ያስተካከለው መጥምቁ ዮሐንስ እንደነበር ያስተምረናል "ደግሞ አንተ ሕፃን ሆይ፥ የልዑል ነቢይ ትባላለህ

መንገዱን ልትጠርግ በጌታ ፊት ትሄዳለህና" (ሉቃ. 1፥76)። "እነሆ፥ መንገድን በፊትህ የሚጠርግ መልእክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ ተብሎ የተጻፈለት ይህ ነውና" (ማቴ. 11፥10)። መንገድ ከተስተካከለለት በኋላ የመጣው ብሉይ ኪዳን ያህዌ ነው ሲለው አዲስ ኪዳን ደግሞ ጌታ (በግሪኩ፦ ኩሩዮስ ይለዋል) ነው። ይኸውም ኢየሱስ ክርስቶስ።

በብሉይ ኪዳን የይህዌ ድምፅ "እንደ ብዙ ውኆች ይተምም ነበር" (ሕዝ. 43፥2) ይለናል። በአዲስ ኪዳን ስለ ኢየሱስ ተመሳሳይ ነገር እናነባለን፦ "ድምፁም እንደ ብዙ ውኃዎች ድምፅ ነበር" (ራእ. 1፥15)። በብሉይ ኪዳን ለያህዌ እውነት የሆነው ሁሉ ለኢየሱስም እውነት መሆኑ ምን ያስተምረናል? ዴቪድ ዌልስ "የክርስቶስ ማንነት" በተባለው መጽሐፍ ከዚህ የበለጠ ትይዮዎችን በክርስቶስና በያህዌ መካከል መኖሩን ያሳያል፦ "ያህዌ" ቀዳሻችን (ዘጸ. 31፥13)፥ በሁሉ ቦታ የሚገኝ (መዝ. 139፥7–10)፥ ሰላማችን (መሳ. 6፥24)፥ ጽድቃችን (ኤር. 23፥6)፥ ድላችን (ዘጸ. 17፥8–16)፥ ፈውሳችን (ዘጸ. 15፥26) እንደሆነ ሁሉ ክርስቶስም እንደዚያው ነው (1ቆሮ. 1፥30፤ ቆላ. 1፥27፤ ኤፌ. 2፥14)። ወንጌል የእግዚአብሔር እንደሆነ (1ተሰ. 2፥2፤ 6–9፤ ገላ. 3፥8) ሁሉ፤ የክርስቶስም ነው (1ተሰ. 3፥2፤ ተሳ. 1፥7)። ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር እንደሆነች ሁሉ (ገላ. 1፥13፤ 1ቆሮ. 15፥9) ያችው ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ነች (ሮሜ 16፥16)። የእግዚአብሔር መንግሥት (1ተሰ. 2፥12) የክርስቶስ መንግሥት ነው (ኤፌ. 5፥5)። የእግዚአብሔር ፍቅር (ኤፌ. 1፥3–5)፥ የክርስቶስ ፍቅር ነው (ሮሜ 8፥35)። የእግዚአብሔር ቃል (ቆላ. 1፥25፤ 1ተሰ. 2፥13)፥ የክርስቶስ ቃል ነው (1ተሰ. 1፥8፤ 4፥15)። የእግዚአብሔር መንፈስ (1ተሰ. 4፥8)፥ የክርስቶስም ነው (ፊል. 1፥19)። የእግዚአብሔር ሰላም (ገላ. 5፥22፤ ፊል. 4፥9)፥ የክርስቶስም ነው (ቆላ. 13፥15፤ ፊል. 1፥2፤ 4፥7)። የእግዚአብሔር የፍርድ ቀን (ኢሳ. 13፥6) የክርስቶስም ነው (ፊል. 1፥6፤ 10፤ 2፥16፤ 1ቆሮ. 1፥8)። የእግዚአብሔር ጸጋ (ኤፌ. 2፥8–9፤ ቆላ. 1፥6፤ ገላ. 1፥15)፥ የክርስቶስ ጸጋ ነው (1ተሰ. 5፥28፤ ገላ. 1፥6፤ 6፥18)።

የእግዚአብሔር ማዳን (ቆላ. 1፥13) የክርስቶስም ማዳን ነው (1ተሰ. 1፥10)። የእግዚአብሔር ፈቃድ (ኤፌ. 1፥11፤ 1ተሰ. 4፥3፤ ገላ. 1፥4) የክርስቶስ ፈቃድ ነው (ኤፌ. 5፥17፤ 1ተሰ. 5፥18)። ስለዚህም ነበር ጳውሎስ የእግዚአብሔር ባሪያ (ሮሜ 1፥19) እንደሆነ ሁሉ የክርስቶስም ባሪያ ነኝ (ሮሜ 1፥1፤ ገላ. 1፥10) ይል የነበረው። ኑሮውም ለእግዚአብሔር ክብር እንደሆነ ሁሉ (ሮሜ 5፥2፤ ገላ. 1፥24)፥ ለክርስቶስም ክብር ነበር (2ቆሮ. 8፥19፥ 23፤ 4፥6)። እምነቱ በእግዚአብሔር ላይ እንደሆነ ሁሉ (1ተሰ. 1፥8–9፤ ሮሜ 4፥1–5)፥ በክርስቶስ ኢየሱስም ላይ ነበር (ገላ. 4፥8፤ 1ተሰ. 4፥5)፥ ክርስቶስንም አውቆታል (2ቆሮ. 4፥6)[23]።

23. David F. Wells, The Person of Christ (West chester, IL: Cross way Books, 1984), ገጽ. 64-65.



## እግዚአብሔር አብና ኢየሱስ ክርስቶስ



| አምላካዊ ስምና አምላካዊ ባህሪይ | ለእግዚአብሔር አብ | ለኢየሱስ ክርስቶስ |
|---|---|---|
| ያህዌ (ጆሆቫ) ["I AM"] | ዘጸ. 3፥14፤ ዘዳ. 32፥39፤ ኢሳ. 43፥10 | ዮሐ. 8፥24፤ 8፥58፤ 18፥4–6 |
| እግዚአብሔር ወይም አምላክ | ዘፍ. 1፥1፤ ዘዳ. 6፥4፤ መዝ. 45፥6–7 | ኢሳ. 9፥6፤ 1ዮሐ. 5፥20–21፤ ዮሐ. 1፥1፤ 2ጴጥ. 1፥1፤ ዮሐ. 20፥28፤ የሐዋ. 18፥25–26፤ 20፥28 ቲቶ 2፥13፤ ዕብ. 1፥3 |
| አልፋና ያሜጋ (መጀመሪያና መጨረሻ) | ተሳ. 41፥4፤ 48፥12፤ ራእ. 1፥8 | ራእ. 1፥17–18፤ 2፥8፤ 22፥12–16 |
| ጌታ | ተሳ. 45፥23 | ማቴ. 12፥8፤ የሐዋ. 7፥59–60፤ 10፥36፤ ሮሜ 10፥12፤ 1ቆሮ. 2፥8፤ 12፥3፤ ፊል. 2፥10–11 |
| አዳኝ | ተሳ. 43፥3፤ 43፥11፤ 63፥8፤ ሉቃ. 1፥47፤ 1ጢሞ. 4፥10 | ማቴ. 1፥21፤ ዕብ. 5፥9፤ ሉቃ. 2፥11፤ ዮሐ. 1፥29፤ ዮሐ. 4፥42፤ ቲቶ 2፥13 |
| ንጉሥ | መዝ. 95፥3፤ ኢሳ. 43፥15፤ 1ጢሞ. 6፥14–16 | ራእ. 17፥14፤ 19፥16 |
| ፈራጅ | ዘፍ. 18፥25፤ መዝ. 50፥4,6፤ መዝ. 96፥13፤ ሮሜ 14፥10 | ዮሐ. 5፥22፤ 2ቆሮ. 5፥10፤ 2ጢሞ. 4፥1 |
| ብርሃን | 2ሳሙ. 22፥29፤ መዝ. 27፥1፤ ኢሳ. 42፥6· | ዮሐ. 1፥4, 9፤ 3፥19፤ 8፥12፤ 9፥5 |
| አለት | ዘዳ. 32፥3–4፤ 2ሳሙ. 22፥32፤ መዝ. 89፥26 | ሮሜ 9፥33፤ 1ቆሮ. 10፥3–4፤1ጴጥ. 2፥4–8 |
| ቤዛ አዳኝ | መዝ. 130፥7–8፤ ኢሳ. 48፥17፤ 54፥5፤ ኢሳ. 63፥9 | የሐዋ. 20፥28፤ ኤፌ. 1፥7፤ ዕብ. 9፥12 |
| ጽድቃችን | ተሳ. 45፥24 | ኤር. 23፥6፤ ሮሜ 3፥21–22 |
| ባል | ተሳ. 54፥5፤ ሆሴ. 2፥18 | ማቴ. 25፥1፤ ማር. 2፥18–19፤ 2ቆሮ. 11፥2፤ ኤፌ. 5፥25–32፤ ራእ. 21፥2, 9 |
| እረኛ | ዘፍ. 49፥24፤ መዝ. 23፥1፤ መዝ. 80፥1 | ዮሐ. 10፥11, 16፤ ዕብ. 13፥20፤ 1ጴጥ. 2፥25፤ 5፥4 |
| ፈጣሪ | ዘፍ. 1፥1፤ ኢዮ. 33፥4፤ መዝ. 95፥5–6፤ 102፥25–26፤ ኢሳ. 40፥28 | ዮሐ. 1፥2–3, 10፤ ቆላ. 1፥15–18፤ ዕብ. 1፥1–3, 10 |
| ሕይወት ሰጪ | ዘፍ. 2፥7፤ ዘዳ. 32፥39፤ 1ሳሙ. 2፥6፤ መዝ. 36፥9 | ዮሐ. 5፥21፤ 10፥28፤ 11፥25 |
| ኃጢአትን ይቅር ባይ | ዘጸ. 34፥6–7፤ ነህ. 9፥17፤ ዳን. 9፥9፤ ዮና. 4፥2 | ማር. 2፥1–12፤ የሐዋ. 26፥18፤ ቆላ. 2፥13፤ 3፥13 |
| ፈዋሽ እግዚአብሔር | ዘጸ. 15፥26 | የሐዋ. 9፥34 |
| በሁሉ ቦታ የሚገኝ | መዝ. 139፥7–12፤ ምሳ. 15፥3 | ማቴ. 18፥20፤ 28፥20፤ ኤፌ. 3፥17፤ 4፥10 |
| ሁሉን የሚያውቅ | 1ነገ. 8፥39፤ ኤር. 17፥9–10, 16 | ማቴ. 11፥20–28፤ ሉቃ. 5፥4–6፤ ዮሐ. 2፥25፤ 16፥30፤ 21፥17፤ የሐዋ. 1፥24 |
| ሁሉን ቻይ | ተሳ. 40፥31፤ 45፥5–13 | ማቴ. 28፥18፤ ማር. 1፥29–34፤ ዮሐ. 10፥18፤ ይሁ. 24 |
| ዘላለማዊ | መዝ. 102፥26–27፤ ዕብ. 3፥6 | ኢሳ. 9፥6፤ ሚኪ. 5፥2፤ ዮሐ. 8፥58 |
| የማይለወጥ | ተሳ. 46፥9, 16፤ ሚኪ. 3፥6፤ ያዕ. 1፥17 | ዕብ. 13፥8 |
| የሚመለክ (ስግደትን የሚቀበል) | ማቴ. 4፥10፤ ዮሐ. 4፥24፤ ራእ. 5፥14፤ 7፥11፤ 11፥16 | ማቴ. 14፥33፤ 28፥9፤ ዮሐ. 9፥38፤ ፊል. 2፥10–11፤ ዕብ. 1፥6 |

## የአምላክን ስም አስመልክቶ ጥያቄ ለይሖዋ ምስክሮች

?

1. በጰ. 3፥15 እግዚአብሔር ያህዌ የሚለው ስም ሳይጨመርበት "የአባቶቻችሁ አምላክ የአብርሃም አምላክ፤ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ" ተብሎ ከተጠራ እግዚአብሔር ያህዌ በሚለው ስም ብቻ መጠራት ያለበት ለምንድን ነው?
2. ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን ያህዌ በሚለው ስም ፈጽሞ ካልጠራው "አባት" ብሎ ግን መጥራቱ እግዚአብሔር ሊጠራበት የሚገባው ስም ያህዌ ብቻ ነው እንድንል ያደርገናል?
3. የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት መጽሐፍ ቅዱስ ስህተት የሌለበት መጽሐፍ ነው እያለ በአንጻሩ የዕብራውያን ማእት አምላኪ ጸሐፍት ጆሆቫ የሚለውን የእግዚአብሔር ስም ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አስወግደውታል ማለቱ የቃለ እግዚአብሔርን ተአማኒነት በጥያቄ ውስጥ አይጥለውምን?
4. አዲስ ኪዳን ከአብ ይልቅ የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ከፍ እንደሚያደርግ አውቀዋልን? ከዚህ በታች የሚከተሉትን ሁሉ በማን ስም የሚከናወኑ ናቸው?
   - በማን ስም ነው መሰብሰብ ያለብን (ማቴ. 18፥20፤ 1ቆሮ. 5፥4)?
   - አጋንት የሚታዘዙት በማን ስም ነው (ሉቃ. 10፥17፤ የሐዋ. 16፥18)?
   - ንስሐና የኃጢአት ይቅርታ የሚሰበከው በማን ስም ነው (ሉቃ. 24፥47)?
   - የኃጢአት ይቅርታ ለማግኘት በማን ስም ነው ያመነው (ዮሐ. 1፥12፤ 3፥16፤ የሐዋ. 10፥43፤ 1ዮሐ. 3፥23፤ 5፥13)?
   - በማን ስም ብቻ ነው ደኅንነት የሚገኘው (የሐዋ. 4፥12)?
   - ጸሎታችንን መጸለይ ያለብን በማን ስም ነው (ዮሐ. 14፥13–14፤ 15፥16፤ 16፥23–24)?
   - መንፈስ ቅዱስ የተላከው በማን ስም ነው (ዮሐ. 14፥26)?



   - ጳውሎስ የማንን ስም ነው እንድንጠራ ያስተማረን (1ቆሮ. 1፥2)?
   - በማን ስም ሥልጣን ነበር ደቀ መዛሙርት በሽተኛን የፈወሱት፥ ሽባን የተረተሩት (የሐዋ. 3፥16፤ 4፥7–10, 30)?
   - የማን ስም ነው ከሁሉ በላይ የሆነው ስም (ኤፌ. 1፥21፤ ፊል. 2፥9–11)?
5. መልሱ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከሆነ፤ የይሖዋ ምስክሮች አዲስ ኪዳን ከኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይልቅ የአብን ስም ይህን ያህል ማወደሱን የሚያመለክቱ ጥቅሶች ማቅረብ ይችላሉን?
6. የይሖዋ ምስክሮች የይሖዋ ምስክር ነን እንደሚሉት ሁሉ ከሙሉ ልባቸው የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ነን ማለት ይችላሉ (የሐዋ. 1፥8)?
7. እንደ የሐዋ. 1፥8 የማን ምስክሮች ነው መሆን ያለብን?
8. የይሖዋ ምስክሮች የእግዚአብሔር እውነተኛና ብቸኛ ምስክሮች ከሆኑ፤ ድርጅታቸው፥ የመጠበቂያ ግንብ የተፈጠረው በአሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከሆነ [የይሖዋ ምስክሮች ታሪካዊ ዳራ የሚለውን ርዕስ ይመልከቱ] እግዚአብሔር ለአንድ ሺ ስምንት መቶ ዓመታት ያለ ምስክር ነበር ማለት ነው? እግዚአብሔር በነዚህ ዘመናት ውስጥ የነበሩ ሰዎች እርሱን እንዲያውቁት አይፈልግም ነበር ማለት ነው? ለሰዎች አይገደውም?
9. ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ። በኢየሩሳሌም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ" (የሐዋ. 1፥8)። ከዚህ በኋላ አዲስ ኪዳንን ስንመረምር ደቀመዛሙርት የአብ ወይም የያህዌ ምስክር ሳይሆን የኢየሱስ ምስክር ነው የሆኑት። ምስክርነታቸውም መሠረት ያደረገው ኢየሱስ በአካል ከሙታን መነሣቱን ነበር። ይህም አስተምህሮ የወንጌል መሠረት ነው (1ቆሮ. 15፥1–4)። ሐዋርያው ጳውሎስ የኢየሱስ ትንሣኤ የደኅንነት መሠረት እንደሆነ አስተምሮአል (ሮሜ 10፥9–10)። ነገር ግን የይሖዋ ምስክሮች የኢየሱስ ክርስቶስን የአካል ትንሣኤ አይቀበሉም ["የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ" የሚለውን ክፍል ይመለከቷል]።

ደቀ መዛሙርት የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር እንጂ የይሖዋ ምስክር አልነበሩም። የሚከተሉትን የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ይመልከቱ፡–

- “ይህን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሣው ለዚህም ነገር እኛ ሁላችን ምስክሮች ነን” (የሐዋ. 2፥32)
- “የሕይወትን ራስ ገደላችሁት እርሱን ግን እግዚአብሔር ከሙታን አስነሣው፥ ለዚህም ነገር እኛ ምስክሮች ነን” (የሐዋ. 3፥15)
- “ሐዋርያትም የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በታላቅ ኃይል ይመሰክሩ ነበር፤ በሁሉም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው” (የሐዋ. 4፥33)
- “እግዚአብሔር ግን ከሙታን አስነሣው በሕዝብም ዘንድ ምስክሮቹ ለሆኑት ከእርሱ ጋር ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም ለወጡት ብዙ ቀን ታያቸው” (የሐዋ. 13፥30–31) በእነዚህ ጥቅሶች መሠረት የጥንት ክርስቲያኖች የይሖዋ ምስክሮች ነበሩ ወይስ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክሮች?

## 3.3 የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮተ ሥላሴ

የይሖዋ ምስክሮች በሥላሴ አስተምህሮ አያምኑም። የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር በሚል ስያሜ የሚታወቀው ድርጅታቸው “በሥላሴ ማመን ይገባሃልን?” በሚል ርዕስ ያሳተመው ጽሑፍ እንዲህ በማለት ይጠይቃል “ሰዎች ስለ ሥላሴ በቅድሚያ የሚያውቁት ነገር ሳይኖር መጽሐፍ ቅዱስን ከዳር እስከ ዳር ቢያነቡት ካነበቡት ነገር የሥላሴን ጽንሰ ሐሳብ ሊያገኙ ይችላሉን? በፍጹም አይችሉም”[1]። “ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር ” በሚለው መጽሐፋቸው ደግሞ “የሥላሴ ትምህርትም ሆነ ስለ አምላክ ያላቸው ፅንሰ ሐሳብ [የሥላሴ አማኞች] ከአረማውያን ምንጮች የተቀዳና መጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ ካለቀ ከአያሌ መቶ ዘመናት በኋላ የአሁኑን ቅርጽ እንዲይዝ የተደረገ ነው”[2] ይላል።
የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ኢየሱስ ክርስቶስ የሥላሴን ትምህርት ፈጽሞ አላስተማረም ባይ ነው። “ሌት ጎድ ቢ ትሩ” [እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን] የሚለው የድርጅቱ መጽሐፍ እንዲህ ይላል “ይህ እንግዳ የሆነና የተወሳሰበ አደናጋሪ አስተምህሮ በክርስቶስ ኢየሱስ

1. በሥላሴ ማመን ይገባሃልን? (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1993) ገጽ 2
2. ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር (Booklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1994 ገጽ 204–205 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።



ምንም ትኩረት አልተሰጠውም፤ አላብራራውም፥ አላስተማረውም”[3]
ይኸው መጽሐፍ ለዚህ አቋሙ የሚያቀርበው አመክንዮአዊ ማስረጃ ደግሞ “ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ በመቃብር ውስጥ ሦስት ቀን በቆየበት ጊዜ ዓለማትን የሚያስተዳድረው ማን ነበር። ይህ ነው መሠረታዊው ጥያቄ. . . ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ከሆነ ኢየሱስ በሞተበት ጊዜ እግዚአብሔርም በመቃብር ውስጥ ሞቶ ነበር ማለት ነው። ዓለማትን በሙላት ለመቆጣጠር ለሰይጣን እንዴት ዓይነት አስደናቂ አጋጣሚ ነው! . . . ኢየሱስ ክርስቶስ የማይሞት እግዚአብሔር ቢሆን ኖሮ መሞት አይችልም ነበር”[4]።

ይህ ብቻ አይደለም የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት በዘመናት ሁሉ የሥላሴን አስተምህሮ በሰዎች እንዲወገዝና ምክንያታዊ አቀራረብ ለማስያዝ ሲል የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን የሥላሴን መሠረተ እምነት ከምታምንበት መንገድ ውጪ አጣሞ እንዲህ ሲል ያቀርበዋል፦ “ይህ ሦስት እግዚአብሔሮች በአንድ እግዚአብሔር የሚለው አስተምህሮ. . . ከሰይጣን ጨለማዊ ምስጢሮች አንዱ፥ በጸጸሱ በኩል ቃሉንና የእግዚአብሔርን ዓላማ ያጨለመበት ነው” [5] [ልብ ይበሉ የክርስትና እምነት ስለ ሥላሴ ያለው አስተምህሮ እግዚአብሔር አንድ ነው፤ በአንድ በእግዚአብሔር ግጻዌ መለኮት [Godhead] ሦስት እኩል የሆኑ አካላት [Persons] አሉ የሚል እንጂ “ሦስት እግዚአብሔሮች በአንድ እግዚአብሔር” የሚል ትምህርት አይደለም]። ይህ ብቻ አይደለም ይኼው የመጠበቂያ ግንብ መጽሐፍ፦ “ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊና ኢአመክንዮአዊ የሆነው የሥላሴ አስተምህሮ ሦስት አምላኮች በአንድ አካል [One Person]”[6] ይላል። [የሥላሴ አማኞች ግን የሚያምኑት “ሦስት እግዚአብሔሮች በአንድ እግዚአብሔር” የሚል ሳይሆን አንድ እግዚአብሔር አለ፤ በአንዱም በእግዚአብሔር ግጻዌ መለኮት ሦስት እኩል የሆኑ አካላት አሉ የሚል ነው]።

“ሪኮንስሊዬሽን” የሚለው የድርጅቱ መጽሐፍ፦ “እንደ ሥላሴ የሚያታልልና የተስፋፋ አስተምህሮ የለም። ይህም አስተምህሮ የተጠነሰሰው በአንድ አእምሮ ነው፤ ይህውም በሰይጣን ዲያቢሎስ ነው”[7] ይላል።

3. “Let God Be True” (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1952) ገጽ. 200
4. ዝኒ ከማሁ ገጽ 109
5. Studies in the scriptures. Vol 5 (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1899), ገጽ. 60 61
6. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 76
7. Reconciliation (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1928), ገጽ. 101

"ሪችስ" የሚለው መጽሐፍ ደግሞ፡- "የእግዚአብሔርን ስም ለማጉደፍና ሰዎችን ከእግዚአብሔር ለማሸሽ በሰይጣን የተሠራውና የተነገረው ሌላው ውሸት 'ሥላሴ' ነው"[8] ይላል።

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የሥላሴ አስተምህሮ ጠንሳሽ ሰይጣን ነው ባይ ብቻ ሳይሆን የሥላሴ ትምህርት ጽንሰ ሐሳብ የተቀዳው ከአረማውያን መድበለ አማልክት ነው የሚልም አስተያየት አለው። በሥላሴ ማመን ተገቢ እንዳልሆነ ለማሳሰብ በዚሁ በመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የወጣው ጽሑፍ፥ "በሥላሴ ማመን ይገባሃልን?" "ዘ ፖጋኒዝም ኢንአወር ክርስቲያኒቲ" ["አረማዊነት በክርስትናችን ውስጥ"] የተሰኘውን መጽሐፍ በመጥቀስ "[የሥላሴ] እምነት የመጣው ሙሉ በሙሉ ከአረማውያን ነው"[8] ይላል።

በተጨማሪም ይኼው የድርጅቱ ጽሑፍ የሥላሴን አስተምህሮ እንዲህም እያለ ያጣጥለዋል "[የሥላሴ] እምነት የመነጨው ሙሉ በሙሉ ከአረማውያን ነው። . . . ለምሳሌ በሕንዳውያን ሃይማኖት ውስጥ ብራህማ፥ ሲቫ እና ሲሰኑ የተባሉት የሦስት አማልክት ጥምረት፥ በግብፃውያን ሃይማኖት ደግሞ ኦሲሪስ፥ አይሲስ እና ሆረስ የተባሉ የሦስት አማልክት ጥምረት እናገኛለን. . . አምላክ ሥላሴ እንደሆነ የሚታመነው በታሪክ በታወቁ ሃይማኖቶች ብቻ አይደለም"[10] በአጠቃላይ የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የሥላሴን አስተምህሮ እንዲህ ሲል ይደመድመዋል፡- "እግዚአብሔር የዚህ አስተምህሮ ጠንሳሽ አይደለም"[11]

በአጠቃላይ "የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር" በመባል የሚታወቀው ሃይማኖታዊ ድርጅት ስለ ሥላሴ ያለው አስተምህሮ ከዚህ እንደሚከተለው ነው፡- ይሖዋ አምላክ በአንድ አካል [Person] ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ሥላሴ አይደለም። በክርስትና የሃይማኖት መግለጫዎች ላይ እንደ ሠፈረው በእግዚአብሔር ግጻዌ መለኮት ውስጥ ሦስት እኩል የሆኑ አካላት የሉም።

8. Riches (Brooklyn: Watchtower bible and Tract Society, 1936), ገጽ. 185
9. በሥላሴ ማመን ይገባሃልን? ገጽ 3። በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።
10. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 11። በቅንፍ ያለውን አይጨምርም
11. "Let God Be True" ገጽ. 101



ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ አምላክ አይደለም። ኢየሱስ በቅድመ-ስብእናው ጊዜ በእግዚአብሔር በቀጥታ የተፈጠረ ብቸኛ ፍጡር ነው - ሊቀ መልአክ ሚካኤል ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ሌሎችን ፍጥረታት እንዲፈጥር በእግዚአብሔር አምላክ ኃይል ተሰጥቶታል። ክርስቶስ አሁን የሚኖረው መለኮት መሰል ሥልጣኑን እንደያዘ ነው። እንደያውም ከሞቱና ከትንሣኤው በኋላ ከይሖዋ አምላክ ጥቅማጥቅሞችንና ኃይልን በማግኘት በይሖዋ ሥር ሆኖ መላውን ዓለም እያስተዳደረ ነው።

መንፈስ ቅዱስ አካላዊ እኔነት [Personality] የለውም በእግዚአብሔር ግጻዌ መለኮት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የሚባል ሦስተኛ አካል የለም። መንፈስ ቅዱስ አካላዊ እኔነት የሌለው የአምላክ ፈጣን ኃይል ነው። እግዚአብሔር አምላክ ሕዝቡ እንዲታዘዘው ለማድረግ ሲፈልግ ለሕዝቡ የሚሰጠው ኃይል ነው።

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የሥላሴን አስተምህሮ ላለመቀበልና ትምህርቱም ከአረማውያን መድበለ አማልክታዊ እሳቤ የተቀዳ ነው ብሎ ለመደምደም ከቃለ እግዚአብሔር የሚጠቅሳቸው "ማስረጃዎች" የሚከተሉት ናቸው[12]።

የሥላሴ ትምህርት ያቆጠቆጠውና በስፋት ይታመንበት የጀመረው ከሐዋርያት ዘመን በኋላ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ "ሥላሴ" ወይም "ሦስት አካላት አንድ እግዚአብሔር" የሚለውን ቃላት አይጠቀምም። የብዙ ሊቃውንቶች ሥራ እንደሚያረጋግጠው የሥላሴ ትምህርት የመነጨው ወይም መሠረታዊ እሳቤው መንጸባረቅ የጀመረው በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ ነው።

12. በግርጌ ማስታወሻ ካልተመለከተ በስተቀር የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርቶች የተወሰዱት፡- በሥላሴ ማመን ይገባሃልን? (1993) እንዲሁም ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር (1994) ገጽ 197-198፥ 212-218፥ 405-426 ከተሰኙት መጻሕፍት ላይ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሥላሴ ትምህርት የሚያስተምረው ምንም ነገር የለም። እንደ ማቴ. 28፥19 ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሥላሴን ትምህርት ለማስተማር ብቁ አይደሉም። ክፍሉ የሚያሳየን አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተወሰነ ኅብረት እንዳላቸው እንጂ በግጻዌ መለኮት ውስጥ ሦስት እኩል የሆኑ አካላት ስለመኖራቸው አይደለም።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ አምላክ አይደለም። ፍጥረታት "አማልክት" ["gods"] ተብለዋል። ዕብራውያን 2፥7 የተጠቀሰው ከመዝ. 8፥5 ላይ ሲሆን "መልአክ" የሚለው ቃል ከዕብራይስጡ "ኤሎሒም" ከሚለው ቃል የተመለሰ ነው። ስለዚህ መዝሙር 8፥5 ላይ የሚገኘው "ኤሎሒም" የሚለው ቃል "አማልክት" ወይም "እግዚአብሔር መስል" ["godlike Ones"] [NWT] ተብሎ መተርጎም አለበት። መዝ. 82፥1 6፤ ዮሐ. 10፥34 የእስራኤል ፈራጆች "አማልክት" ተብለዋል። በዚህ ክፍል ላይ "አማልክት" የሚለው ቃል የገባው እግዚአብሔርን በሚወክል መልኩ ነው። ምክንያቱም ፈራጆቹ የእግዚአብሔር ወኪሎች ናቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለማስረዳት የቀረበው መከላከያ ጥቅስ መዝ. 82፥6 ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር የሚያንስ አምላክ [a god] ነው እንጂ "ሁሉን ቻይ አምላክ" አይደለም። በኢሳ. 9፥6 ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ "ኃያል አምላክ" ተባለ እንጂ "ሁሉን ቻይ አምላክ" አልተባለም። ዮሐ. 1፥1 እግዚአብሔር ከሚለው የግሪክ ቃል ፊት የተወሰነ መስተፃምር [The] ካለ ቃሉ በአብዛኛው መተርጎም ያለበት እግዚአብሔር [God] ተብሎ ነው። ነገር ግን ቃሉ አብዛኛውን ጊዜ እንደ ሚገኝበት ዐውድ ስለሚወሰን የቃሉን ፍቺ የሚወስኑት ተርጓሚዎቹ ናቸው። በዚህ ክፍል ግን "ቃል" የተባለው ክርስቶስ "በእግዚአብሔር ዘንድ" ስለነበር እርሱ ራሱ እግዚአብሔር [God] ሊሆን አይችልም። ይህንንም ዐውድ ራሱ ግልጽ ያደርገዋል። ምክንያቱም ማንም ከራሱ ጋር ["ዘንድ"] አብሮ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ የዮሐ. 1፥1 ትክክለኛ ትርጉም [a god] የሚለው ነው።

እንደ ሥላሴ አማኞች ትምህርት በዮሐ. 5፥18 ላይ ሐዋርያው ዮሐንስ እየተናገረ ያለው ኢየሱስ ክርስቶስ "ከእግዚአብሔር ጋር እኩል" እንደ ሆነ ነው። ነገር ግን ዮሐንስ የዘገበልን ዕብራውያኑ የኢየሱስ አነጋገር የገባቸው ኢየሱስ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር እንዳስተካከለ ነው። ስለዚህ ሰንበትን ሽረሃል የሚለው የዕብራውያኑ አነጋገር ሐሰት እንደሆነ ሁሉ፤ ራስህን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክለሃል የሚለውም ሐሰት ነው።



በዮሐ. 20፥28 ቶማስ ኢየሱስ ክርስቶስ "አማላኩ" [God] መሆኑን ማመኑ ኢየሱስ ከእርሱ በላይ ኃያል መሆኑን መቀበሉን የሚያመለክት ነው። ወይም ኢየሱስ ክርስቶስ ሕያው ሆኖ በማየቱ ወደ እግዚአብሔር አምላክ በመደነቅ መጮሁን የሚያሳይ ነው። ይህ ክፍል ቶማስ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ሁሉን ቻይ አምላክ ማመኑን የሚያስተምር አይደለም። ዮሐ. 20፥17 የሚያስተምረን እግዚአብሔር የኢየሱስ ክርስቶስ የበላይ መሆኑን ነው። እንዲሁም ዮሐ. 20፥31 የሚያሳየን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ወልድ እንደሆነ ሳይሆን የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጡር ነው። ምሳ. 8፥22 "እግዚአብሔር የመንገዱ መጀመሪያ አደረገኝ በቀድሞ ሥራው መጀምሪያ" ክፍሉ ስለ ጥበብ ነው የሚያወራው። ስለ እግዚአብሔር ጥበብ አይደለም ምክንያቱም እግዚአብሔር የራሱን ጥበብ ሊፈጥር አይደልም። ስለዚህ ክፍሉ ስለ ሌላ ጥበብ ነው የሚናገረው። በ1ኛ ቆሮ. 1፥24 ክርስቶስ ጥበብ ተብሎአል ስለዚህ ምሳ. 8 የሚናገረው ስለ ክርስቶስ ነው። ይህም የሚያሳየው ክርስቶስ እንደተፈጠረ ነው።

በቆላ. 1፥15 "ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው" ይላል። በኩር የሚለው ቃል የሚያሳየን በመወለድ ሂደት ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጀመሪያ መሆኑን ነው። ይህም የሚያረጋግጥልን ኢየሱስ ክርስቶስ በይሖዋ አምላክ እንደተፈጠረ ነው። ራእ. 3፥14 ኢየሱስ ክርስቶስ ለ"እግዚአብሔርም ፍጥረት መጀመሪያ የነበረው" ከዚህ ዐረፍተ ነገር በቀላሉ የምንግረው ኢየሱስ ክርስቶስ ይሖዋ አምላክ ከፈጠራቸው ፍጥረታት የመጀመሪያው መሆኑን ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርሱ በላይ የሆነ አምላክ አለው። ኢየሱስ አባቱን እግዚአብሔር ብሎአል ኢየሱስ ይህንን ያለው ከትንሣኤው በኋላ ሰማያዊ በሆነው ክብሩ ሳለ ነው (ዮሐ. 20፥17፤ ራእ. 3፥12)። ኢየሱስ ከእርሱ በላይ የሆነ አምላክ ካለው ሁሉን ቻይ አምላክ ሊሆን አይችልም።

ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን እንኳ በሰማይ ከእግዚአብሔር በታች ሆኖ ነው ያለው። መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይ ለእግዚአብሔር እየተገዛ እንዳለ ያስተምረናል። ይህም በምድር በነበረበት ጊዜ እንደተገዛው ማለት ነው (ዮሐ. 14፥28፤ 1ቆሮ. 11፥3፤ 15፥28)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ መልአክ ሚካኤል ነው። በዳንኤል 10፥13 ላይ "ሚካኤል "ከዋንኞቹ አለቆች አንዱ" ነው። ዳን. 12፥1 ላይ "በዚያም ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል. .

.”። የሚለው ትንቢት የተፈጸመው በኢየሱስ ክርስቶስ (ሚካኤል) በሰማይ እንደ ንጉሥ ሆኖ በ1914 በነገሠበት ጊዜ ነው[13]። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ የሚያሳየን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅድመ ሕልውናውም ሆነ በደኅረ ሕልውናው ጊዜ ሚካኤል እንደሆነ ነው።

1ተሰ. 4፥16 “ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔር መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሳሉ”። “ጌታ ራሱ” ነው “በመላእክት አለቃ ድምፅ” የሚናገረው። ይህም ኢየሱስ ሚካኤል እንደሆነ ያሳያል “ሚካኤል ብቻ ነው ‘ሊቀ መልአክ’ የተባለው፤ ይህም ማለት ‘የመላእክት ዋናኛ’ ወይም ‘የመላእክት ገዥ’ ማለት ነው። ቃሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው በነጠላ ቁጥር ነው። ይህም እግዚአብሔር ለመላእክት አንድ አለቃ ብቻ እንዲኖራቸው ያደረገ ይመስላል። በ1ተሰ. 4፥16 የትንሣኤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ድምፅ በሊቀ መልአክ ሚካኤል ድምፅ ተገልጽዋል፤ ይህ የሚያመለክተን በእርግጥ ራሱ ሊቀ መልአክ እንደሆነ ነው”[14]።

መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና (Personality) የለውም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና እንደሌለው ተደርጎ ነው የተገለጸው። በማር. 1፥10 መንፈስ ቅዱስ በእርግብ አምሳል ነው የታየው። በማቴ. 3፥11፤ በሉቃ. 3፥16 መንፈስ ቅዱስ ከእሳት ጋር ተነጻጽሮአል። በኤፌ. 5፥18 መንፈስ ቅዱስን መሞላት በወይን ጠጅ ከመስከር ጋር ተነጻጽሮአል። አካላዊ ህልውና ባለው ነገር መሞላት ሞኝነት ነው። መንፈስ ቅዱስ በሰውኛ አገላለጽ ቀርቦአል። ስለዚህ አካላዊ ህልውና ሊኖረው አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን አካላዊ ህልውና እንዳለው አቅርቦታል፤ ነገር ግን በሰውኛ መንፈስ አካላዊ ህልውና እንዳለው አቅርቦታል፤ ነገር ግን በሰውኛ አገላለጽ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንዴ አካላዊ ህልውና የሌላቸውንም ነገሮች በሰውኛ አገላለጽ አቅርቦአቸዋል። ለምሳሌ፦ ጥበብ ልጅ እንዳለው (ሉቃ. 7፥35)። ኃጢአትና ሞት እንደ ንጉሥ እንደነገሡ (ሮሜ 5፥14,21)። ውኃና ደም ከመንፈሱ ጋር እንደሚመሰክሩ (1ዮሐ. 5፥8)።

13. “Your Will Be Done On Earth” (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1944), ገጽ. 259
14. Aid to Bible Understanding (Brooklyn: Watchtower Bible and Tract Society, 1971), ገጽ.1152





# የይሖዋ ምስክሮች
# የሥላሴ ትምህርት
# በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን



የሥላሴ ትምህርት የተቀዳው የእግዚአብሔር ስልጣናዊ ቃል ከሆነው ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ነው። እንደ ማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ሁሉ የሥላሴ ትምህርት ሥርዓታዊ ትንተናን ተከትሎ የቀረበው የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ ለተነሣው የመናፍቃን እንቅስቃሴ መልስ ለመስጠት እንዲያስችላት ነው። የምሁራን ማስረጃ የሚረጋግጠው ይህንኑ እውነታ እንጂ የሥላሴ አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አለመሆኑን አይደለም።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሥላሴ ሰፊ ትምህርት አለው። አስተምህሮተ ሥላሴ የተመሠረተው በማቴ. 28፥19 ላይ ብቻ አይደለም። የበሰለ የሥላሴ አማኝ የሥላሴ ትምህርት ያረፈው በዚህ ክፍል ላይ ብቻ ነው አይልም። ክፍሉ አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና እንዳላቸው ጥርት አድርጎ ያሳያል። አብና ወልድ አካላዊ ህልውና ካላቸው ከእነርሱ ጋር አብሮ የተጠቀሰው መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና የለውም የተባለበት ምክንያት ምንድን ነው? በሦስቱም ስም መጠመቃችን ራሳችንን ሙሉ በሙሉ ለሦስቱም ሥልጣን ማስገዛታችንን የሚያሳይ ነው። ይህም እኩል የሆነ ሥልጣን እንዳላቸው ያሳያል።

በአዲስ ኪዳን ብቻ አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር፥ የዘላለም ሕይወትን በመስጠት፥ እንዲሁም በክርስትና ሕይወታችን ላይ ተሳትፎ ሲያደርጉ እናያለን። ይህ የሚያሳየን የሥላሴ አስተምህሮ ቀዳማዊ አመንጪው ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ነው። የእግዚአብሔርንና የአማልክትን [gods] የትርጉም አጠቃቀም በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የሚለውን ነጠላ ቃል የሚጠቀመው ያህዌን ለማመልከት ነው። ለምሳሌ፦ እግዚአብሔር [በግሪኩ ቴዎስ] የሚለው ነጠላ ቃል በአዲስ ኪዳን 1400 ጊዜ ተጠቅሶአል። ሐሰተኛ አማልክትን ወይም ጣኦታትን ለማሳየት ቃሉ ጥቅም ላይ የዋለው ስድስት ጊዜ ብቻ ነው። ይህም ቃሉ ለሐሰተኛ አማልክት ስለ መዋሉ ዐውዱ ያሳየናል (የሐዋ. 7፥43፤ 12፥22፤ 28፥6፤ 2ቆሮ. 4፥4፤ ፊል. 3፥19፤ 2ተሰ. 2፥7)። **መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የሚለውን ቃል በነጠላ ቁጥር ሲጠቀምበት**

[በዕብራይስጥ 'ኤል' ወይም 'ኤሎሂም'። በግሪክ 'ቴዎስ'] የሚያመለክተው ሁሉን ቻይ የሆነውን አምላክ ነው። ስለዚህ ይህ ወጥነት ያለውና አንድ ዓይነት የቃል አጠቃቀም በግልጽ የሚያሳየን ሁሉም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቃሉን የተጠቀሙበት እውነተኛውን አምላክ እንዲያመለክት አድርገው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ እውነተኛ አምላክ ብቻ እንዳለ ይናገራል (ለምሳሌ፡- ኢሳ. 43፥10፤ 44፥6–8፤ ኤር. 10፥10፤ ዮሐ. 17፥3፤ 1ጢሞ. 2፥5፤ ያዕ. 2፥19፤ 1ዮሐ. 5፥20)። በአንጻሩም አማልክት [gods] ተብለው የተጠሩት ሁሉ ሐሰተኛ አምላክ ናቸው (1ቆሮ. 8፥5፤ ዘዳ. 32፥21፤ መዝ. 96፥5፤ ኢሳ. 41፥23–24)። እውነቱ ይህ ከሆነ የይሖዋ ምስክሮች በዮሐንስ 1፥1 እና 20፥28 ላይ ቴዎስ የሚለው ነጠላ ቃል ለክርስቶስ ለምን እንደተሰጠ መልስ ሊሰጡበት ይችላሉ?

መዝ. 82፥1 ላይ ሰዎች አማልክት (gods) ተብለዋል፤ ይህም በውክልና ደረጃ ብቻ ነው። ቃሉንም የሚጠቀምበት በምፀት [ironical] ነው። በክፍሉ ላይ "አማልክት" እያለ የሚጠራቸው አድሎአዊ ፍርድ የሚበይኑትን ሐሰተኛ ፈራጆች ነው። ምክንያቱም ራሳቸውን እንደ አማልክት አድርገው ስለሚቆጥሩ ነው። ነገር ግን አሳፍ እንደ ሰው ትሞታላችሁ ይላቸዋል (ቁ. 6, 7)። ጌታ ይህንን ጥቅስ በመጥቀስ "የእግዚአብሔር ቃል አይሻርም" እያስተማረ ያለው (ዮሐ. 10፥34) ለእነርሱ በምፀት የመጣው ቃል ለእኔ በቀጥታ መዋል አለበት የሚል ነው። ምክንያቱም ኢየሱስ ከአባቱ ጋር እኩል ነውና (ቁ. 27–30, 36)።

በኢሳ. 9፥6 መሲሑ "ኃያል አምላክ" እንደተባለ ሁሉ፤ በዚያው ዐውድ ውስጥ የያዕቆብ አምላክ "ኃያል አምላክ" ተብሎአል (ኢሳ. 10፥21)። ይህ ክፍል "ኃያል አምላክ" የሚለውን ቃል ለአብ እንደሰጠ ሁሉ ለወልድም መስጠቱ የወልድን አምላክነት የሚያረጋግጥ ነው።

ዮሐ. 1፥1 ቴዎስ [እግዚአብሔር] የሚለው የግሪክ ቃል አብዛኛውን ጊዜ የሚተረጎመው እግዚአብሔር ወይም አምላክ [God] ተብሎ ነው። ቃሉ በዚህ መልኩ የሚተረጎመው ከቃሉ ፊት የተወሰነ መስተፃምር ሲኖርም ሳይኖርም ነው። በግሪክ፥ በእንግሊዝኛም ሆነ በሌሎች ቋንቋዎች የተወሰነ መስተፃምር [the] መኖርም ሆነ አለመኖር በስም [Noun] ላይ መሠረታዊ ለውጥ አያመጣም። በተለይ ቴዎስ የሚለውን የግሪክ ቃል አስመልክቶ ያለው የተወሰነ መስተፃምር ጉዳይ በአዲስ ኪዳን ግሪክ የትርጉም ለውጥ አያስከትልም። ለምሳሌ፡- ሰይጣን "የዚህ ዓለም አምላክ" (2ቆሮ. 4፥4) ተብሎአል። ነገር ግን ቴዎስ [አምላክ] ከሚለው ቃል ፊት የተወሰነ መስተፃምር መኖሩ ቃሉ እውነተኛውን አምላክ እንዲያሳይ አላደረገውም።



በአጠቃላይ ቴዎስ ከሚለው ነጠላ ቃል ፊት የተወሰነ መስተፃምር ቢኖርም ባይኖርም ቃሉ እግዚአብሔር ወይም አምላክ [God] ተብሎ መተርጎም ይኖርበታል። ነገር ግን ዐውዱ እውነተኛውን አምላክ የማያመለክት ከሆነ በእንግሊዝኛው (god) ተብሎ ይተረጎማል። በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ላይ ቴዎስ የሚለው ቃል የተወሰነ መስተፃምር ሳይኖረው እግዚአብሔር [God] ተብሎ ነው የተተረጎመው (ዮሐ. 1፥1, 12, 13, 18)። በዮሐ. 1፥1ላይ "ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር" እግዚአብሔር (ቴዎስ) ከሚለው ቃል ፊት የተወሰነ መስተፃምር አለ። የትርጉም ይዘቱን ሳይቀይር ቴዎስ የሚለው ቃል የተወሰነ መስተፃምር ሳይኖረው በሚቀጥለው ሐረግ ውስጥ ተጠቅሶአል፥ "ቃልም እግዚአብሔር ነበር"። የተወሰነ መስተፃምር ከቴዎስ ፊት መኖርም ሆነ አለመኖር የትርጉም ለውጥ እንደማያመጣ የሚከተሉትን ጥቅሶች በአዲሲቱ ዓለም ትርጉም እንኳን ማየት ይቻላል (ዮሐ. 3፥2፤ 13፥3፤ ሮሜ 1፥21፤ 1ተሰ. 1፥9፤ ዕብ. 9፥14፤ 1ጴጥ. 4፥11–12)[15]።

"ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር" የሚለው ዐረፍተ ነገር የሚያሳየን ቃል የተባለው ክርስቶስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር አብሮ እንዳለና ["ዘንድ"] ቃልም ከእግዚአብሔር አብ የተለየ ህልውና [personality] እንዳለው የሚያስተምረን ነው። በዚህ ትምህርት የይሖዋ ምስክሮች ራሳቸው ይስማማሉ [ነገር ግን "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" አብም ወልድም አንድ ህላዌ አላቸው ከሚለው ትምህርታቸው ጋር ይህን ጥቅስ እንዴት ያስታርቁት ይሆን?] ቀጣዩ ዐረፍተ ነገር "ቃልም እግዚአብሔር ነበር" ሲል ቃል የእግዚአብሔር ባሕርይ [Nature] እንዳለው የሚያሳይ ነው እንጂ የይሖዋ ምስክሮች እንደሚሉት እግዚአብሔር የሚለው ቃል ከሁሉን ቻዩ እግዚአብሔር ወደ ኃያሉ እግዚአብሔር መለወጡን ለማሳየት ተፈልጎ አይደለም። በአጠቃላይ በዮሐ. 1፥1 ላይ ለማለት የተፈለገው ቃል በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ነበር። እንዲሁም ቃል ራሱ የእግዚአብሔር ባሕርይ [Nature] እንዳለው ነው። ዮሐንስ እግዚአብሔር (ቴዎስ) ከሚለው ቃል ፊት የተወሰነ መስተፃምር ("ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር") በማድረግ እግዚአብሔር አብን ለማመልከት እንደፈለገ ሁሉ ለወልድም፥ "ቃልም እግዚአብሔር ነበር" የተወሰነ መስተፃምር ቢጠቀም ኖሮ "ቃል" የተባለው ክርስቶስ ራሱ እግዚአብሔር አብ ነው የሚል ትርጉም ይኖረው ነበር። ዮሐንስ የክርስቶስን ፍጹም አምላክነትና ክርስቶስ ከአብ የተለየ ህላዌ እንዳለው ያሳየው ዐረፍተ ነገሩን ያለ መስተፃምር በመገንባት ነው።

15. ለበለጠ መረጃ Robert M. Bowman, Jr., Jesus Christ, and the Gospel of John. (Grand Rapids: Baker, 1989) እንዲሁም Murray J. Harris, Jesus as God: The New Testament Use of Theos in Reference to Jesus (Grand Rapids: Baker, 1992) ይመለከቷል።

[በዕብራይስጥ 'ኤል' ወይም 'ኤሎሂም'። በግሪክ 'ቴዎስ'] የሚያመለክተው ሁሉን ቻይ የሆነውን አምላክ ነው። ስለዚህ ይህ ወጥነት ያለውና አንድ ዓይነት የቃል አጠቃቀም በግልጽ የሚያሳየን ሁሉም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቃሉን የተጠቀሙበት እውነተኛውን አምላክ እንዲያመለክት አድርገው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ እውነተኛ አምላክ ብቻ እንዳለ ይናገራል (ለምሳሌ፡- ኢሳ. 43፥10፤ 44፥6–8፤ ኤር. 10፥10፤ ዮሐ. 17፥3፤ 1ጢሞ. 2፥5፤ ያዕ. 2፥19፤ 1ዮሐ. 5፥20)። በአንጻሩም አማልክት [gods] ተብለው የተጠሩት ሁሉ ሐሰተኛ አምላክ ናቸው (1ቆሮ. 8፥5፤ ዘዳ. 32፥21፤ መዝ. 96፥5፤ ኢሳ. 41፥23–24)። እውነቱ ይህ ከሆነ የይሖዋ ምስክሮች በዮሐንስ 1፥1 እና 20፥28 ላይ ቴዎስ የሚለው ነጠላ ቃል ለክርስቶስ ለምን እንደተሰጠ መልስ ሊሰጡበት ይችላሉ?

መዝ. 82፥1 ላይ ሰዎች አማልክት (gods) ተብለዋል፤ ይህም በውክልና ደረጃ ብቻ ነው። ቃሉንም የሚጠቀምበት በምፀት [ironical] ነው። በክፍሉ ላይ "አማልክት" እያለ የሚጠራቸው አድሎአዊ ፍርድ የሚበይኑትን ሐሰተኛ ፈራጆች ነው። ምክንያቱም ራሳቸውን እንደ አማልክት አድርገው ስለሚቆጥሩ ነው። ነገር ግን አሳፍ እንደ ሰው ትሞታላችሁ ይላቸዋል (ቁ. 6, 7)። ጌታ ይህንን ጥቅስ በመጥቀስ እያስተማረ ያለው (ዮሐ. 10፥34) "የእግዚአብሔር ቃል አይሻርም" ለእነርሱ በምፀት የመጣው ቃል ለእኔ በቀጥታ መዋል አለበት የሚል ነው። ምክንያቱም ኢየሱስ ከአባቱ ጋር እኩል ነውና (ቁ. 27–30, 36)።

በኢሳ. 9፥6 መሲሑ "ኃያል አምላክ" እንደተባለ ሁሉ፤ በዚያው ዐውድ ውስጥ የያዕቆብ አምላክ "ኃያል አምላክ" ተብሎአል (ኢሳ. 10፥21)። ይህ ክፍል "ኃያል አምላክ" የሚለውን ቃል ለአብ እንደሰጠ ሁሉ ለወልድም መስጠቱ የወልድን አምላክነት የሚያረጋግጥ ነው።

ዮሐ. 1፥1 ቴዎስ [እግዚአብሔር] የሚለው የግሪክ ቃል አብዛኛውን ጊዜ የሚተረጎመው እግዚአብሔር ወይም አምላክ [God] ተብሎ ነው። ቃሉ በዚህ መልኩ የሚተረጎመው ከቃሉ ፊት የተወሰነ መስተፃምር ሲኖርም ሳይኖርም ነው። በግሪክ፥ በእንግሊዝኛም ሆነ በሌሎች ቋንቋዎች የተወሰነ መስተፃምር [the] መኖርም ሆነ አለመኖር በስም [Noun] ላይ መሠረታዊ ለውጥ አያመጣም። በተለይ ቴዎስ የሚለውን የግሪክ ቃል አስመልክቶ ያለው የተወሰነ መስተፃምር ጉዳይ በአዲስ ኪዳን ግሪክ የትርጉም ለውጥ አያስከትልም። ለምሳሌ፡- ሰይጣን "የዚህ ዓለም አምላክ" (2ቆሮ. 4፥4) ተብሎአል። ነገር ግን ቴዎስ [አምላክ] ከሚለው ቃል ፊት የተወሰነ መስተፃምር መኖሩ ቃሉ እውነተኛውን አምላክ እንዲያሳይ አላደረገውም።



በአጠቃላይ ቴዎስ ከሚለው ነጠላ ቃል ፊት የተወሰነ መስተፃምር ቢኖርም ባይኖርም ቃሉ እግዚአብሔር ወይም አምላክ [God] ተብሎ መተርጎም ይኖርበታል። ነገር ግን ዐውዱ እውነተኛውን አምላክ የማያመለክት ከሆነ በእንግሊዝኛው (god) ተብሎ ይተረጎማል። በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ላይ ቴዎስ የሚለው ቃል የተወሰነ መስተፃምር ሳይኖረው እግዚአብሔር [God] ተብሎ ነው የተተረጎመው (ዮሐ. 1፥1, 12, 13, 18)። በዮሐ. 1፥1ላይ "ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር" እግዚአብሔር (ቴዎስ) ከሚለው ቃል ፊት የተወሰነ መስተፃምር አለ። የትርጉም ይዘቱን ሳይቀይር ቴዎስ የሚለው ቃል የተወሰነ መስተፃምር ሳይኖረው በሚቀጥለው ሐረግ ውስጥ ተጠቅሶአል፥ "ቃልም እግዚአብሔር ነበር"። የተወሰነ መስተፃምር ከቴዎስ ፊት መኖርም ሆነ አለመኖር የትርጉም ለውጥ እንደማያመጣ የሚከተሉትን ጥቅሶች በአዲሲቱ ዓለም ትርጉም እንኳን ማየት ይቻላል (ዮሐ. 3፥2፤ 13፥3፤ ሮሜ 1፥21፤ 1ተሰ. 1፥9፤ ዕብ. 9፥14፤ 1ጴጥ. 4፥11–12)[15]።

"ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር" የሚለው ዐረፍተ ነገር የሚያሳየን ቃል የተባለው ክርስቶስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር አብሮ እንዳለና ["ዘንድ"] ቃልም ከእግዚአብሔር አብ የተለየ ህልውና [personality] እንዳለው የሚያስተምረን ነው። በዚህ ትምህርት የይሖዋ ምስክሮች ራሳቸው ይስማማሉ [ነገር ግን "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" አብም ወልድም አንድ ህላዌ አላቸው ከሚለው ትምህርታቸው ጋር ይህን ጥቅስ እንዴት ያስታርቁት ይሆን?] ቀጣዩ ዐረፍተ ነገር "ቃልም እግዚአብሔር ነበር" ሲል ቃል የእግዚአብሔር ባሕርይ [Nature] እንዳለው የሚያሳይ ነው እንጂ የይሖዋ ምስክሮች እንደሚሉት እግዚአብሔር የሚለው ቃል ከሁሉን ቻዩ እግዚአብሔር ወደ ኃያሉ እግዚአብሔር መለወጡን ለማሳየት ተፈልጎ አይደለም። በአጠቃላይ በዮሐ. 1፥1 ላይ ለማለት የተፈለገው ቃል በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ነበር። እንዲሁም ቃል ራሱ የእግዚአብሔር ባሕርይ [Nature] እንዳለው ነው። ዮሐንስ እግዚአብሔር (ቴዎስ) ከሚለው ቃል ፊት የተወሰነ መስተፃምር ("ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር") በማድረግ እግዚአብሔር አብን ለማመልከት እንደፈለገ ሁሉ ለወልድም፥ "ቃልም እግዚአብሔር ነበር" የተወሰነ መስተፃምር ቢጠቀም ኖሮ "ቃል" የተባለው ክርስቶስ ራሱ እግዚአብሔር አብ ነው የሚል ትርጉም ይኖረው ነበር። ዮሐንስ የክርስቶስን ፍጹም አምላክነትና ክርስቶስ ከአብ የተለየ ህላዌ እንዳለው ያሳየው ዐረፍተ ነገሩን ያለ መስተፃምር በመገንባት ነው።

15. ለበለጠ መረጃ Robert M. Bowman, Jr., Jesus Christ, and the Gospel of John. (Grand Rapids: Baker, 1989) እንዲሁም Murray J. Harris, Jesus as God: The New Testament Use of Theos in Reference to Jesus (Grand Rapids: Baker, 1992) ይመለከቷል።

[በዕብራይስጥ ‘ኤል’ ወይም ‘ኤሎሂም’። በግሪክ ‘ቴዎስ’] የሚያመለክተው ሁሉን ቻይ የሆነውን አምላክ ነው። ስለዚህ ይህ ወጥነት ያለውና አንድ ዓይነት የቃል አጠቃቀም በግልጽ የሚያሳየን ሁሉም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቃሉን የተጠቀሙበት እውነተኛውን አምላክ እንዲያመለክት አድርገው ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አንድ እውነተኛ አምላክ ብቻ እንዳለ ይናገራል (ለምሳሌ፦ ኢሳ. 43፥10፤ 44፥6–8፤ ኤር. 10፥10፤ ዮሐ. 17፥3፤ 1ጢሞ. 2፥5፤ ያዕ. 2፥19፤ 1ዮሐ. 5፥20)። በአንጻሩም አማልክት [gods] ተብለው የተጠሩት ሁሉ ሐሰተኛ አምላክ ናቸው (1ቆሮ. 8፥5፤ ዘዳ. 32፥21፤ መዝ. 96፥5፤ ኢሳ. 41፥23–24)። እውነቱ ይህ ከሆነ የይሖዋ ምስክሮች በዮሐንስ 1፥1 እና 20፥28 ላይ ቴዎስ የሚለው ነጠላ ቃል ለክርስቶስ ለምን እንደተሰጠ መልስ ሊሰጡበት ይችላሉ?

መዝ. 82፥1 ላይ ሰዎች አማልክት (gods) ተብለዋል፤ ይህም በውክልና ደረጃ ብቻ ነው። ቃሉንም የሚጠቀምበት በምፀት [ironical] ነው። በክፍሉ ላይ “አማልክት” እያለ የሚጠራቸው አድሎአዊ ፍርድ የሚበይኑትን ሐሰተኛ ፈራጆች ነው። ምክንያቱም ራሳቸውን እንደ አማልክት አድርገው ስለሚቆጥሩ ነው። ነገር ግን አሳፍ እንደ ሰው ትሞታላችሁ ይላቸዋል (ቁ. 6, 7)። ጌታ ይህንን ጥቅስ በመጥቀስ እያስተማረ ያለው (ዮሐ. 10፥34) “የእግዚአብሔር ቃል አይሻርም” ለእነርሱ በምፀት የመጣው ቃል ለእኔ በቀጥታ መዋል አለበት የሚል ነው። ምክንያቱም ኢየሱስ ከአባቱ ጋር እኩል ነውና (ቁ. 27–30, 36)።

በኢሳ. 9፥6 መሲሑ “ኃያል አምላክ” እንደተባለ ሁሉ፤ በዚያው ዐውድ ውስጥ የያዕቆብ አምላክ “ኃያል አምላክ” ተብሎአል (ኢሳ. 10፥21)። ይህ ክፍል “ኃያል አምላክ” የሚለውን ቃል ለአብ እንደሰጠ ሁሉ ለወልድም መሰጠቱ የወልድን አምላክነት የሚያረጋግጥ ነው።

ዮሐ. 1፥1 ቴዎስ [እግዚአብሔር] የሚለው የግሪክ ቃል አብዛኛውን ጊዜ የሚተረጎመው እግዚአብሔር ወይም አምላክ [God] ተብሎ ነው። ቃሉ በዚህ መልኩ የሚተረጎመው ከቃሉ ፊት የተወሰነ መስተፃምር ሲኖርም ሳይኖርም ነው። በግሪክ፥ በእንግሊዝኛም ሆነ በሌሎች ቋንቋዎች የተወሰነ መስተፃምር [the] መኖርም ሆነ አለመኖር በስም [Noun] ላይ መሠረታዊ ለውጥ አያመጣም። በተለይ ቴዎስ የሚለውን የግሪክ ቃል አስመልክቶ ያለው የተወሰነ መስተፃምር ጉዳይ በአዲስ ኪዳን ግሪክ የትርጉም ለውጥ አያስከትልም። ለምሳሌ፦ ሰይጣን “የዚህ ዓለም አምላክ” (2ቆሮ. 4፥4) ተብሎአል። ነገር ግን ቴዎስ [አምላክ] ከሚለው ቃል ፊት የተወሰነ መስተፃምር መኖሩ ቃሉ እውነተኛውን አምላክ እንዲያሳይ አላደረገውም።



በአጠቃላይ ቴዎስ ከሚለው ነጠላ ቃል ፊት የተወሰነ መስተፃምር ቢኖርም ባይኖርም ቃሉ እግዚአብሔር ወይም አምላክ [God] ተብሎ መተርጎም ይኖርበታል። ነገር ግን ዐውዱ እውነተኛውን አምላክ የማያመለክት ከሆነ በእንግሊዝኛው (god) ተብሎ ይተረጎማል። በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ላይ ቴዎስ የሚለው ቃል የተወሰነ መስተፃምር ሳይኖረው እግዚአብሔር [God] ተብሎ ነው የተተረጎመው (ዮሐ. 1፥1, 12, 13, 18)። በዮሐ. 1፥1ላይ “ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር” እግዚአብሔር (ቴዎስ) ከሚለው ቃል ፊት የተወሰነ መስተፃምር አለ። የትርጉም ይዘቱን ሳይቀይር ቴዎስ የሚለው ቃል የተወሰነ መስተፃምር ሳይኖረው በሚቀጥለው ሐረግ ውስጥ ተጠቅሶአል፥ “ቃልም እግዚአብሔር ነበር”። የተወሰነ መስተፃምር ከቴዎስ ፊት መኖርም ሆነ አለመኖር የትርጉም ለውጥ እንደማያመጣ የሚከተሉትን ጥቅሶች በአዲሲቱ ዓለም ትርጉም እንኳን ማየት ይቻላል (ዮሐ. 3፥2፤ 13፥3፤ ሮሜ 1፥21፤ 1ተሰ. 1፥9፤ ዕብ. 9፥14፤ 1ጴጥ. 4፥11–12)[15]።

“ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር” የሚለው ዐረፍተ ነገር የሚያሳየን ቃል የተባለው ክርስቶስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር አብሮ እንዳለና [“ዘንድ”] ቃልም ከእግዚአብሔር አብ የተለየ ህላውና [personality] እንዳለው የሚያስተምረን ነው። በዚህ ትምህርት የይሖዋ ምስክሮች ራሳቸው ይስማማሉ [ነገር ግን “የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን” አብም ወልድም አንድ ህላዌ አላቸው ከሚለው ትምህርታቸው ጋር ይህን ጥቅስ እንዴት ያስታርቁት ይሆን?] ቀጣዩ ዐረፍተ ነገር “ቃልም እግዚአብሔር ነበር” ሲል ቃል የእግዚአብሔር ባሕርይ [Nature] እንዳለው የሚያሳይ ነው እንጂ የይሖዋ ምስክሮች እንደሚሉት እግዚአብሔር የሚለው ቃል ከሁሉን ቻዩ እግዚአብሔር ወደ ኃያሉ እግዚአብሔር መለወጡን ለማሳየት ተፈልጎ አይደለም። በአጠቃላይ በዮሐ. 1፥1 ላይ ለማለት የተፈለገው ቃል በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ነበር። እንዲሁም ቃል ራሱ የእግዚአብሔር ባሕርይ [Nature] እንዳለው ነው። ዮሐንስ እግዚአብሔር (ቴዎስ) ከሚለው ቃል ፊት የተወሰነ መስተፃምር (“ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር”) በማድረግ እግዚአብሔር አብን ለማመልከት እንደፈለገ ሁሉ ለወልድም፥ “ቃልም እግዚአብሔር ነበር” የተወሰነ መስተፃምር ቢጠቀም ኖሮ “ቃል” የተባለው ክርስቶስ ራሱ እግዚአብሔር አብ ነው የሚል ትርጉም ይኖረው ነበር። ዮሐንስ የክርስቶስን ፍጹም አምላክነትና ክርስቶስ ከአብ የተለየ ህላዌ እንዳለው ያሳየው ዐረፍተ ነገሩን ያለ መስተፃምር በመገንባት ነው።

15. ለበለጠ መረጃ Robert M. Bowman, Jr., Jesus Christ, and the Gospel of John. (Grand Rapids: Baker, 1989) እንዲሁም Murray J. Harris, Jesus as God: The New Testament Use of Theos in Reference to Jesus (Grand Rapids: Baker, 1992) ይመለከቷል።

በዮሐ. 5፥18 ላይ ዮሐንስ ዕብራውያን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብ ጋር እኩል ነኝ ማለቱ ነው ብለው መረዳታቸውን መዘገቡ እውነት ነው። እንዲሁም ሰንበትን ሽረሃል የሚለው የዕብራውያን ክስ ትክክል ያለመሆኑ እውነት ነው። ነገር ግን ይህ ጉዳይ የይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ እኔ ከአብ ጋር እኩል ነኝ አላለም የሚለውን ትምህርታቸው አያመለክትም። በሌላ ዐውድ ኢየሱስ ዕብራውያንን የሰንበትን መንፈስ በመሻራቸው ሲቃወማቸው እናያለን (ማቴ. 12፥9–14)። ነገር ግን በዚህ ክፍል ላይ ኢየሱስ የሰንበት ጌታ መሆኑን እያስተማረ ነው። በዮሐ. 5፥17 ላይ ኢየሱስ ሰንበትን እየተቸ ሳይሆን ሕጉ እርሱን እንደማይወክል፥ ሕጉ በሰበአዊያን ላይ ብቻ ተግባራዊ እንደሚሆን እያስተማረ ነው። ስለዚህ ዕብራውያን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ማድረጉ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር ማስተካከሉ ነው በማለታቸው አልተሳሳቱም። ጌታ በሚቀጥሉት ጥቅሶች እያለ ያለው እግዚአብሔር መሆኑን እየካደ ሳይሆን የልጁ ሥልጣን በአባቱ ላይ የተመሠረተ መሆኑን እያስረገጠ ነው።

ዮሐ. 20፥28 ኢየሱስ ሕያው ሆኖ ከሙታን በመነሣቱ ቶማስ በመደነቅ ወደ እግዚአብሔር "አ አምላኬ!" ብሎ መጮኹ ነው የሚለው የይሖዋ ምስክሮች ትምህርት ከክፍሉ ዐውድ ጋር ብቻ ሳይሆን ከታሪካዊ ዳራውም ጋር አብሮ የሚሄድ አይደለም። በመጀመሪያ ክፍለ ዘመን የነበሩ ዕብራውያን የእግዚአብሔር ስም በንዝህላልነት በዚህ መልኩ አይጠቀሙበትም ነበር[16]። ከክፍሉ የምንመለከተው ነገር ቶማስ በቀጥታ ለኢየሱስ መልስ እየሰጠ እንዳለ ነው፡– "ቶማስም ጌታዬ አምላኬ ብሎ መለሰለት"።

የይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጡር ነው ለሚለው ትምህርታቸው ከቃለ እግዚአብሔር የሚጠቅሱአቸው ጥቅሶች፥ (ምሳ. 8፥22፤ ቆላ. 1፥15፤ ራእ. 3፥14) በፍጹም ትምህርታቸውን የሚደግፉ አይደሉም። ይልቁንም ድርጅታቸው የአምላክን ቃል እንዴት እንደሚያጣምም እንዲሁም ለእግዚአብሔር ቃል ያለው ዕውቀት ደካማ እንደሆነ የሚያሳይ ነው።

ምሳ. 8፥22 በምሳሌ መጽሐፍ ከምዕራፍ 1–9 ባሉት ክፍሎች ሁሉ ጥበብ በሰውኛ አነጋገር ጥቅም ላይ ውሎአል። ስለዚህ ምሳ. 8፥22–31 ስለ ክርስቶስ ይናገራል ማለት ትክክል አይደለም። የምሳሌ መጽሐፍ ፍጹም ቅኔያዊ በመሆኑ ከ1ቆሮ. 1፥24 30 ጋር በማያያዝ ክፍሉ ስለ

16. David Reed, Jehovah's Withnesses Answered Verse by Verse (Grand Rapids: Baker Book House, 1992), ገጽ .84



ክርስቶስ ይናገራል ማለት አግባብ አይደለም። የምሳሌ መጽሐፍ የቅኔ መጽሐፍ ነው፤ ሥነ–ጽሑፋዊ ቅርጹም ቅኔያዊ ነው። በምሳ. 1–9 ባሉት ክፍሎች ጥበብ በሰውኛ (personification) አገላለጽ ነው የተጠቀሰችው ዳዊት መሰንቆንና በገናን ተነሡ እንደሚለው ማለት ነው፥ "በገና ሆይ፥ ተነሥ፥ መሰንቆም፤ እኔም ማልጄ እነሣለሁ" (መዝ. 108፥2)። ክፍሉ ስለ ጥበብ ሳይሆን ስለ ክርስቶስ ነው የሚናገረው ካልን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልናነሣ እንችላለን፡–

- ክፍሉ ጥበብን በአንስታይ [feminine] ነው የሚጠራት (ቁጥር 1, 2, 3, 11) ክርስቶስ በየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው "አንቺ" [she] የተባለው?
- ምሳሌ 8 የሚናገረው ስለ ጥበብ ብቻ ሳይሆን ስለ ማስተዋልም ጭምር ነው (ቁ.1)። 1ቆሮ. 1፥24, 30 በመጥቀስ ክርስቶስ ጥበብ ነው ካልን ማስተዋልስ ደግሞ ማነው?
- "ጥበብ ቤትዋን ሠራች ሰባቱንም ምሶሶችዋን አቆመች" (9፥1) ሲል ምን ማለቱ ነው?
- ሰለሞን ስለ ክርስቶስ የመናገር ከሆነ "በውኑ ጥበብ አትጮኽምን? ማስተዋልስ ድምፅዋን አትሰጥምን? " በማለት ሰውኛ አገላለጽ መጠቀም ለምን አስፈለገው?
- ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጡር ከሆነ፤ የእግዚአብሔር ኃይልና ጥበብ ክርስቶስ ነውና (1ቆሮ. 1፥24) እግዚአብሔር ክርስቶስን ከመፍጠሩ በፊት ኃይልና ጥበብ የለውም ነበር ማለት ነው?
- በምሳሌ መጽሐፍ ውስጥ ጥበብ እንደሚገዛ ንብረት ነው የቀረበችው (1፥5፤ 4፥5፤ 15፥32፤ 16፥16፤ 17፥16፤ 18፥15፤ 19፥8፤ 20፥14፤ 23፥23) ይህስ ምን ያስተምረናል?

በእርግጥ የምሳሌ መጽሐፍ የጥበብን [Wisdom] አስፈላጊነት እንጂ ስለ ክርስቶስ አያወራም።

ቆላ. 1፥15 "በኩር" የሚለው ቃል በመወለድ ቅደም ተከተል የመጀመሪያ ማለት ሳይሆን ክርስቶስ የፍጥረታት ሁሉ ወራሽና ባለቤት መሆኑን የሚያስተምር ነው። "በኩር" ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል [ፕሮቶቶኮስ] የሚያመለክተው በጊዜ ቅደም ተከተል የመጀመሪያ መሆንን ሳይሆን ታላቅነትንና ክብርን የሚያሳይ ቃል ነው። ንጉሥ ዳዊት የእሴይ የመጨረሻ ልጅ ነው። በንግሥና ከሄድን ከዳዊት በፊት ንጉሥ ሳኦል 40 ዓመት ነግሦ አል። ነገር ግን እግዚአብሔር ዳዊትን

በኩር ይለዋል መዝ. 89፥27። ይህ የሚያሳየን የዳዊትን ክብር እንጂ የጊዜ ብልጫን አይደለም። የዮሴፍ የመጀመሪያ ልጅ ምናሴ ሆኖ ሳለ (ዘፍ. 41፥50–51) ኤፍሬም "በኩር" ተብሎአል (ኤር. 31፥9)። ያዕቆብ የኤሳውን ብኩርና ወሰደ ስንል ክብሩን ወሰደ ማለታችንም አይደል? ጳውሎስ በቆላ. 1፥15 ላይ የኢየሱስን ፍጡር መሆን ለማመልከት ቢፈልግ ኖሮ "ፕሮቶቶክስ" ከሚለው የግሪክ ቃል ይልቅ "ፕሮቶኪቲሲስ" የሚለውን ቃል ይጠቀም ነበር[17]። በአዲስ ኪዳን ግሪክ "ፕሮቶኪቲሲስ" የሚለው ቃል አንድም ጊዜ ክርስቶስን ለማሳየት በጥቅም ላይ አልዋለም[18] የይሖዋ ምስክሮች በቆላ. 1፥15 ላይ አራት ጊዜ ሌሎች [other] የሚለውን ቃል በአዲሲቱ ዓለም ትርጉም ላይ ጨምረዋል። ነገር ግን የግሪክ አዲስ ኪዳን ሌሎች [other] የሚል ቃል የለውም። ይህን ቃል በክፍሉ ውስጥ አራት ጊዜ መጨመራቸው ኢየሱስን ፍጡር አድርጎ እንዴት እንዳቀረበው ከአዲሲቱ ዓለም ትርጉም ይመልከቱ።

ራእ. 3፥14 የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት "አርኬ" የሚለውን የግሪክ ቃል "ከተፈጠሩት ነገሮች የመጀመሪያ" አድርጎ ተርጉመውታል። ቃሉ በአዲስ ኪዳን የጊዜን መጀመሪያ ለማሳየትም ሆነ ( ዮሐ. 1፥1, 2፤ 6፥64፤ 8፥25, 44፤ 15፥27፤ 16፥4፤ 1ዮሐ. 1፥1፤ 2፥7, 13, 14, 24፤ 3፥8 11፤ 2ዮሐ. 5, 6) መገኛ ወይም ምንጭ በሚለው ትርጉሙ በብዙ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ውስጥ ተተርጉሞአል (ሉቃ. 12፥11፤ ሮሜ 8፥38፤ 1ቆሮ. 15፥24፤ ኤፌ. 1፥21፤ 3፥10፤ 6፥12፤ ቆላ. 1፥16፤ 2፥10, 15፤ ቲቶ 3፥1) ። በራእይ መጽሐፍ ቃሉ እግዚአብሔርን ለማመልከት ገብቶአል ወይም ጥቅም ላይ ውሎአል (ራእ. 21፥6፤ 22፥13)። በነዚህ ክፍሎች ውስጥ ቃሉ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊነት ለማሳየት ከገባ የክርስቶስን ዘላለማዊነት የማያሳይበት ምንም ምክንያት የለም። ከአዲሲቱ ዓለም ትርጉም በስተቀር በየትኛውም የእንግሊዝኛም ሆነ የአማርኛ ትርጉሞች ላይ ቃሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጡር ነው አይልም። ነገር ግን የፍጥረት መገኛ ወይም መጀመሪያ ተብሎ ነው የተተረጎመው [የ1980 ዓ.ም. የአማርኛ ትርጉም ከ1954 ዓ.ም. ትርጉም ጋር ያወዳድሩ]።

ኢየሱስ ክርስቶስ አባቱን አምላኬ ብሎአል። ምክንያቱም ኢየሱስ የፍጡሩን ቦታ ለኛ ለኃጢአተኞች ሲል ስለወሰደ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ለአብ በሰማይ እንኳ ተገዝቶለት ነው ያለው። ነገር ግን ይህ ማለት ኢየሱስ ከአብ ያንሳል ማለት ግን በፍጹም አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ አሁን ድረስ ሰው ሆኖ ነው ያለው (የሐዋ. 17፥31፤ 1ጢሞ. 2፥5) ስለዚህ የክርስቶስ መገዛት በምድር በነበረበት ጊዜ ብቻ አይደለም።

17. F.F Bruce in Iнerrany, ed. Norman L. Geisler (Grand Rapids: Zondervan, 1979)
18. J.B Light foot, Paul's Epistles to the colossians and to philemon. (Grand Rapids: Zondervau, 1979), ገጽ. 147



ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ መልአክ ሚካኤል አይደለም። የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ኢየሱስ ሚካኤል ነው ለማለት የሚጠቅሰው ጥቅስ ዳን. 10፥13 ፍጹም የሚያስኬደው አይደለም። ምክንያቱም ሚካኤል "ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ" እንደሆነ እንጂ ኢየሱስ ሚካኤል ነው የሚል ዐረፍተ ነገርም ሆነ ቃል በክፍሉ ውስጥ አልተጠቀሰም። በራእ. 19፥16 ኢየሱስ "የነገሥታት ንጉሥና የጌታዎች ጌታ" ነው እንጂ ከብዙ አለቆች መካከል አንዱ አይደለም ከመላእክት አንድም እንኳ የእግዚአብሔር ልጅ ካልተባለ (ዕብ. 1፥5) ኢየሱስ ክርስቶስ መልአክት ሊሆን አይችልም የዕብራውያን ጸሐፊ ኢየሱስ ክርስቶስ ከነቢያት በላይ (1፥1–4)፥ ከመላእክት በላይ (1፥5–2፥8)፥ ከሙሴ በላይ (3፥1–6) እንደሆነ ያስተምረናል። ከተዘረዘሩትም በላይ መሆኑ የታየው የእግዚአብሔር የመጨረሻ መገለጥ (1፥1)፥ የዓለማት ፈጣሪና የዓለማት ደጋፊ መሆኑ (1፥3) እንዲሁም የእግዚአብሔር ባሕርይ (1፥3) ስላለው ነው። ይህ ብቻ አይደለም በዕብ. 1፥6 ላይ መላእክት ለኢየሱስ ይሰግዱለታል [በግሪክ ፕሮስኩኖ]። መልአክ ከሆነ እንዴት መላእክት ሰገዱለት? መላእክት ዓለማትን መግዛት ካልቻሉ (ዕብ. 2፥5) የዓለማት ገዥ ኢየሱስ በፍጹም መልአክ ሊሆን አይችልም (ዘፍ. 49፥10፤ 2ሳሙ. 17፥16፤ መዝ. 2፥6፤ ዳን. 7፥13–14፤ ሉቃ. 1፥32–33፤ ማቴ. 2፥1–2፤ 9፥35፤ ራእ. 19፥16)።

1ተሰ. 4፥16 "ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና" ክፍሉ ኢየሱስ በታላቅ አጀብ እንደሚመጣ የሚያስተምረን ክፍል እንጂ ኢየሱስ ራሱ በመልአክ ድምፅ ይናገራል አይልም።

መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና [personality] አለው። ብዙውን ጊዜ አካላዊ ህልውና ማለት መጨበጥ፥ መታየት ወዘተ ማለት የሚመስላቸው ሰዎች አሉ። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ህልውና አለው ሲባል የራሱ ማንነት ይኸውም ስሜት፥ እውቀትና ፈቃድ አለው ማለት ነው። ይዳስሳል፥ ይታያል ወዘተ ማለት አይደለም። የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና በሌላቸው ነገሮች መመሰሉ አካላዊ ህልውና እንደሌለው ያመለክታል የሚለው ትምህርት ፍጹም የተሳሳተ ነው። (ማር. 1፥10) መንፈስ ቅዱስ በርግብ መመሰሉ አካላዊ ህልውና የለውም እንድንል አያደርግም። አብ ራሱ በቁጥቋጦ እንደሚነድ እሳት ሆኖ ነው ሙሴን የተገናኘው (ዘጸ. 3፥2–4)። ይህ ማለት ግን እግዚአብሔር አብ ህልውና የለውም ማለት አይደለም።

በማቴ. 3፥11፤ ሉቃ. 3፥16 መንፈስ ቅዱስ በእሳት መመሰሉ አካላዊ ህልውና የለውም እንድንል አያደርገንም። መጽሐፍ ቅዱስ በተምሳሌታዊ አገላለጽ እግዚአብሔር እሳት ነው ይለናል (ዘዳ. 4፥24፤ 9፥3፤ ዕብ. 12፥29)።

ኤፌ. 5፥18 በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ የሚለው የመልእክት ክፍል በእግዚአብሔርም (3፥19) እንዲሁም በክርስቶስ (4፥10) ተሞሉ ይለናል። አብና ወልድ አካላዊ ህልውና እያላቸው የሚሞሉን ከሆነ መንፈስ ቅዱስ ቢሞላብን አካላዊ ህልውና የለውም የሚያስኘው ለምንድን ነው?

## መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሥላሴ ምን ይላል



የሥላሴ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ (ኢሳ. 43፥10፤ 44፥6–8፤ ኤር. 10፥10፤ ዮሐ. 17፥3፤ 1ጢሞ. 2፥5፤ ያዕ. 2፥19 1ዮሐ. 5፥20)። አብ እግዚአብሔር ነው (ዮሐ. 17፥3፤ 1ቆሮ. 8፥6)። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው (ኢሳ. 9፥6፤ ዮሐ. 1፥1፤ 20፥28፤ ሮሜ 9፥5፤ ቲቶ 2፥13፤ ዕብ. 1፥8፤ 2ጴጥ. 1፥1)። መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው (ዮሐ. 5፥3–4፤ 2ቆሮ. 3፥17)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ አምላክ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ወይም አምላክ ተብሎአል (ኢሳ. 9፥6፤ ዮሐ. 1፥1፤ 20፥28፤ ሮሜ 9፥5፤ ቲቶ 2፥13፤ ዕብ. 1፥8፤ 2ጴጥ. 1፥1)። ኢየሱስ ክርስቶስ ያህዌ ተብሎአል (ሮሜ 10፥9–13፤ ፊል. 2፥9–11፤ ዕብ. 1፥10–12፤ 1ጴጥ. 2፥3፤ 3፥15)። የእግዚአብሔር ባሕሪያት ሁሉ አሉት (ቆላ. 1፥15፤ 2፥9፤ ዕብ. 1፥3)። ይኸውም፦ አይለወጥም (ዕብ. 1፥11–12፤ 13፥8)። ዘላለማዊ ነው (ዮሐ. 1፥1–2፤ 8፥58፤ 17፥5፤ ቆላ. 1፥17፤ ዕብ. 1፥2 12)። የኃይል ሁሉ ባለቤት ነው (ማቴ. 28፥8፤ ኤፌ. 1፥21)። ሁሉን ያውቃል (ዮሐ. 16፥30)። በሁሉ ቦታ ይገኛል (ማቴ. 18፥20፤ 28፥30፤ ኤፌ. 1፥23፤ ኤፌ. 4፥10፤ ቆላ. 3፥11)። ከሰዎች ግምት በላይ ነው (ማቴ. 11፥27። ተፈርቶአል ኤፌ. 5፥21)። ከምንም ከማንም በላይ በፍጹምነት ተፈቅሮአል (ማቴ. 10፥37)። በፍጹም ልብ ታምኖአል [እግዚአብሔርን እንደምናምነው] (ዮሐ. 3፥16፤ 14፥1)። ስግደትን



ተቀብሎአል ወይም ተመልኮአል (ማቴ. 28፥17፤ ዕብ. 1፥6፤ ራእ 22፥3)። የሰበአውያንን ጸሎት ያዳምጣል (ዮሐ. 14፥14፤ ሮሜ 10፥12–13፤ 1ቆሮ. 1፥2)።

መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክ ነው። መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና አለው። የእግዚአብሔር መንፈስ ተብሎአል [እርኩሳን መናፍስት መንፈስ እንደተባሉት ማለት ነው] መንፈስ ቅዱስ ስም አለው (ማቴ 28፥19)። አጽናኝ ተብሎአል (ዮሐ. 14፥16) [ቃሉ በአዲስ ኪዳን ውስጥ (በግሪኩ ቅጂ ላይ) አካላዊ ህልውና ላለው አካል ብቻ የሚሰጥ ነው]። በኢየሱስ ክርስቶስ ተልኮአል፤ ይኸውም ለማስተማር፥ ለመስከር ወዘተ። ይህም ከራሱ ሳይሆን ከኢየሱስ ክርስቶስ ወስዶ ነው (ዮሐ. 14፥26፤ 15፥26–27፤ 16፥7 13–14)። ከእርኩሳን መናፍስት ጋር ተነጻጽሮአል (ማር. 3፥28–30፤ 1ጢሞ. 4፥1፤ 1ዮሐ. 3፥24–4፥6)። ለደቀ መዛሙርት ፈቃዱን ተናግሮአል፤ ወደ አገልግሎትም መርቶአቸዋል (የሐዋ. 8፥29፤ 10፥19–20፤ 16፥7)። ሰዎችን ወደ ልዩ ልዩ አገልግሎት ጠርቶአል (የሐዋ. 13፥2፤ 20፥28)። እርሱ ራሱ እንደፈቀደ ለክርስቲያኖች ስጦታን ይሰጣል (1ቆሮ. 12፥11)። ከእግዚአብሔር ቃል ይናገራል (የሐዋ. 1፥16፤ 28፥25፤ ዕብ. 3፥7)። ሊዋሽ ይችላል፤ ማለትም ሰዎች ሊዋሹት ይችላሉ [ነገር ግን አምላክ ስለሆነ ያውቃል] (የሐዋ. 5፥3)።

መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው። ያህዌ ተብሎአል (ዘጸ. 34፥34 ይህን ጥቅስ ከ2ቆሮ. 3፥17–18 ጋር ያነጻጽሩ)። እግዚአብሔር ተብሎአል (የሐዋ. 5፥3–4)። የእግዚአብሔር ባሕርያት አሉት። ዘላለማዊ ነው (ዕብ. 9፥14)። ሁሉን ያውቃል (1ቆሮ. 2፥10)። በሁሉ ቦታ ይገኛል (መዝ. 139፥7)።

## አስተምህሮተ ሥላሴን አስመልክቶ ጥያቄ ለይሖዋ ምስክሮች

1. ባቢሎናውያንም ሆኑ አሶራውያን መድበለ አማልክት [polytheism] አምላኪዎች ነበሩ። የሥላሴ አስተምህሮ ዳግም፦ "አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ [monotheism]፤ በአንዱ የእግዚአብሔር ግጻዌ መለኮት [Godhead] ውስጥ ሦስት አካላት [persons] አሉ" የሚል ነው። ታዲያ የሥላሴ አስተምህሮ የአረማውያን ፅንሰ ሐሳብ ነው የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርት ትክክል ነውን?

በማቴ. 3፥11፤ ሉቃ. 3፥16 መንፈስ ቅዱስ በእሳት መመስሉ አካላዊ ህልውና የለውም እንድንል አያደርገንም። መጽሐፍ ቅዱስ በተምሳሌታዊ አገላለጽ እግዚአብሔር እሳት ነው ይለናል (ዘዳ. 4፥24፤ 9፥3፤ ዕብ. 12፥29)።

ኤፌ. 5፥18 በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ የሚለው የመልእክት ክፍል በእግዚአብሔርም (3፥19) እንዲሁም በክርስቶስ (4፥10) ተሞሉ ይለናል። አብና ወልድ አካላዊ ህልውና እያላቸው የሚሞሉን ከሆነ መንፈስ ቅዱስ ቢሞላብን አካላዊ ህልውና የለውም የሚያሰኘው ለምንድን ነው?

## መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሥላሴ ምን ይላል



የሥላሴ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ (ኢሳ. 43፥10፤ 44፥6–8፤ ኤር. 10፥10፤ ዮሐ. 17፥3፤ 1ጢሞ. 2፥5፤ ያዕ. 2፥19 1ዮሐ. 5፥20)። አብ እግዚአብሔር ነው (ዮሐ. 17፥3፤ 1ቆሮ. 8፥6)። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው (ኢሳ. 9፥6፤ ዮሐ. 1፥1፤ 20፥28፤ ሮሜ 9፥5፤ ቲቶ 2፥13፤ ዕብ. 1፥8፤ 2ጴጥ. 1፥1)። መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው (ዮሐ. 5፥3–4፤ 2ቆሮ. 3፥17)።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ አምላክ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ወይም አምላክ ተብሎአል (ኢሳ. 9፥6፤ ዮሐ. 1፥1፤ 20፥28፤ ሮሜ 9፥5፤ ቲቶ 2፥13፤ ዕብ. 1፥8፤ 2ጴጥ. 1፥1)። ኢየሱስ ክርስቶስ ያህዌ ተብሎአል (ሮሜ 10፥9–13፤ ፊል. 2፥9–11፤ ዕብ. 1፥10–12፤ 1ጴጥ. 2፥3፤ 3፥15)። የእግዚአብሔር ባሕሪያት ሁሉ አሉት (ቆላ. 1፥15፤ 2፥9፤ ዕብ. 1፥3)። ይኸውም፦ አይለወጥም (ዕብ. 1፥11–12፤ 13፥8)። ዘላለማዊ ነው (ዮሐ. 1፥1–2፤ 8፥58፤ 17፥5፤ ቆላ. 1፥17፤ ዕብ. 1፥2 12)። የኃይል ሁሉ ባለቤት ነው (ማቴ. 28፥8፤ ኤፌ. 1፥21)። ሁሉን ያውቃል (ዮሐ. 16፥30)። በሁሉ ቦታ ይገኛል (ማቴ. 18፥20፤ 28፥30፤ ኤፌ. 1፥23፤ ኤፌ. 4፥10፤ ቆላ. 3፥11)። ከሰዎች ግምት በላይ ነው (ማቴ. 11፥27። ተፈርቶአል ኤፌ. 5፥21)። ከምንም ከማንም በላይ በፍጹምነት ተፈቅሮአል (ማቴ. 10፥37)። በፍጹም ልብ ታምኖአል [እግዚአብሔርን እንደምናምነው] (ዮሐ. 3፥16፤ 14፥1)። ስግደትን



ተቀብሎአል ወይም ተመልኮአል (ማቴ. 28፥17፤ ዕብ. 1፥6፤ ራእ. 22፥3)። የስበአውያንን ጸሎት ያዳምጣል (ዮሐ. 14፥14፤ ሮሜ 10፥12–13፤ 1ቆሮ. 1፥2)።

መንፈስ ቅዱስ ፍጹም አምላክ ነው። መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና አለው። የእግዚአብሔር መንፈስ ተብሎአል [እርኩሳን መናፍስት መንፈስ እንደተባሉት ማለት ነው] መንፈስ ቅዱስ ስም አለው (ማቴ. 28፥19)። አጽናኝ ተብሎአል (ዮሐ. 14፥16) [ቃሉ በአዲስ ኪዳን ውስጥ (በግሪኩ ቅጂ ላይ) አካላዊ ህልውና ላለው አካል ብቻ የሚሰጥ ነው]። በኢየሱስ ክርስቶስ ተልኮአል፤ ይኸውም ለማስተማር፥ ለመስከር ወዘተ። ይህም ከራሱ ሳይሆን ከኢየሱስ ክርስቶስ ወስዶ ነው (ዮሐ. 14፥26፤ 15፥26–27፤ 16፥7 13–14)። ከእርኩሳን መናፍስት ጋር ተነጻጽሮአል (ማር. 3፥28–30፤ 1ጢሞ. 4፥1፤ 1ዮሐ. 3፥24–4፥6)። ለደቀ መዛሙርት ፈቃዱን ተናግሮአል፤ ወደ አገልግሎትም መርቶአቸዋል (የሐዋ. 8፥29፤ 10፥19–20፤ 16፥7)። ሰዎችን ወደ ልዩ ልዩ አገልግሎት ጠርቶአል (የሐዋ. 13፥2፤ 20፥28)። እርሱ ራሱ እንደፈቀደ ለክርስቲያኖች ስጦታን ይሰጣል (1ቆሮ. 12፥11)። ከእግዚአብሔር ቃል ይናገራል (የሐዋ. 1፥16፤ 28፥25፤ ዕብ. 3፥7)። ሊዋሽ ይችላል፤ ማለትም ሰዎች ሊዋሹት ይችላሉ [ነገር ግን አምላክ ስለሆነ ያውቃል] (የሐዋ. 5፥3)።

መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ነው። ያህዌ ተብሎአል (ዘጸ. 34፥34 ይህን ጥቅስ ከ2ቆሮ. 3፥17–18 ጋር ያነጻጽሩ)። እግዚአብሔር ተብሎአል (የሐዋ. 5፥3–4)። የእግዚአብሔር ባሕርያት አሉት። ዘላለማዊ ነው (ዕብ. 9፥14)። ሁሉን ያውቃል (1ቆሮ. 2፥10)። በሁሉ ቦታ ይገኛል (መዝ. 139፥7)።

## አስተምህሮተ ሥላሴን አስመልክቶ ጥያቄ ለይሖዋ ምስክሮች

1. ባቢሎናውያንም ሆኑ አሶራውያን መድበለ አማልክት [polytheism] አምላኪዎች ነበሩ። የሥላሴ አስተምህሮ ዳግም፦ "አንድ እግዚአብሔር ብቻ አለ [monotheism]፤ በአንዱ የእግዚአብሔር ግጻዌ መለኮት [Godhead] ውስጥ ሦስት አካላት [persons] አሉ" የሚል ነው። ታዲያ የሥላሴ አስተምህሮ የአረማውያን ፅንሰ ሐሳብ ነው የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርት ትክክል ነውን?

2. "ሥላሴ" የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሌለ ብቻ ትምህርቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም ማለት ይቻላልን? [የይሖዋ ምስክሮች ድርጅታቸው በአምላክ የሚመራ ነው ስለሚሉ "ቴዎክራቲክ" ("በአምላክ የሚመራ") የሚለውን ቃል ይጠቀማሉ። ቃሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም። እንዲያውም ቃሉ የመጣው ከአረማውያን ነው፤ የሮም ቄሳሮችም ሆኑ የግብፅ ፈርዖኖች አምላክ ነን ይሉ ስለነበር አስተዳደራቸውን "ቴዎክራቲክ" ብለው ይጠሩታል። ቴዎክራቲክ የሚለው ቃል የመጣው ከአረማውያን ስለሆነ ቃሉን መጠቀም የለብንም ማለት አንችልም፤ ምክንያቱም ፅንሰ ሐሳቡ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሚገኝ]።
3. ሰበአውያን ሙሉ በሙሉ እግዚአብሔርን ሊረዱ አይችሉም (ኢሳ. 55፥8–9፤ ሮሜ 11፥33፤ 1ቆሮ. 13፥12)። "ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር" የሚባለው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት መጽሐፍ በገጽ 148 ላይ "አምላክ መጀመሪያ የለውም ማለት ምክንያታዊ ነውን? ይህን ጉዳይ አእምሮአችን ሙሉ በሙሉ ሊረዳው አይችልም። ለመረዳት አለመቻላችን ግን ይህን ሐቅ ላለመቀበል ምክንያት አይሆነንም" ይላል። የሥላሴን አስተምህሮ አእምሮአችን ሙሉ በሙሉ ስላልተረዳው አንቀበልም ማለት ምክንያታዊ ነውን?
4.

| ባሕሪ | አብ | ወልድ | መንፈስ ቅዱስ |
|---|---|---|---|
| በሁሉ ቦታ መገኘት | 1ነገ. 8፥27 | ማቴ. 28፥20 | መዝ. 139፥7 |
| ሁሉን ማወቅ | መዝ. 147፥5 | ዮሐ. 16፥30 | 1ቆሮ. 2፥10 |
| ሁሉን መቻል | መዝ. 135፥6 | ማቴ. 28፥18 | ሮሜ 15፥19 |
| ቅድስና | ራእ. 15፥4 | የሐዋ. 3፥14 | ሮሜ 1፥4 |
| ዘላለማዊነት | መዝ. 90፥2 | ሚኪ. 5፥2፤ ዮሐ. 1፥2፤ ራእ. 1፥8,17 | ዕብ. 9፥14 |

አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አንድ ዓይነት ባሕርይ ካላቸው በሥላሴ ማመን ያልተገባን ለምንድን ነው?

5. አልፋና ዖሜጋ እግዚአብሔር እንደሆነ ሁሉ (ኢሳ. 44፥6) ኢየሱስ ክርስቶስም አልፋና ዖሜጋ ነው (ራእ. 22፥12–13)። አልፋና ዖሜጋ የሆነው አብ ጅማሬ ከሌለው፤ አልፋና ዖሜጋ የሆነው ኢየሱስ እንዴት ጅማሬ ሊኖረው ይችላል?
6. በዳን. 10፥12 ኢየሱስ ክርስቶስ ሚካኤል ነው የሚል ግልጽ ዐረፍተ ነገር ወይም ቃል አለ?
7. ከመልአክት እግዚአብሔር ልጄ ያለው ከሌለ (ዕብ. 1፥5) ኢየሱስ ልጄ ካለው እንዴት ኢየሱስ መልአክ ሊሆን ይችላል?



8. ከመልአክት ዓለምን የሚመራ ከሌለ (ዕብ. 2፥5) ነገር ግን ኢየሱስ ዓለምን ከመራ (ሉቃ. 1፥32–33፤ ራእ. 19፥16) እንዴት መልአክት ነው ልንለው ቻልን?
9. ሊቀ መልአክ ሚካኤል ሰይጣንን "ጌታ ይገሥጽህ" (ይሁዳ 9) ካለው ኢየሱስ ግን በሥልጣኑ ሰይጣንን መገሠጹ (ማቴ. 4፥10፤ 16፥23፤ ማር. 8፥33) ምን ያስተምረናል?
10. መንፈስ ቅዱስ እውቀት (ሮሜ 8፥27፤ 1ቆሮ. 2፥10–11)፥ ስሜት (ኤፌ. 4፥30፤ 2ቆሮ. 2፥2, 5) እንዲሁም ፈቃድ (1ቆሮ. 12፥11፤ ያዕ. 1፥18) ካለው "ኃይል" ብቻ እንጂ አካላዊ ህልውና የለውም ከሚለው የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር ትምህርት ጋር እንዴት ይታረቃል? ኃይል ዕውቀት፥ ስሜት፥ ፈቃድ ሊኖረው ይችላል?
11. መንፈስ ቅዱስ የሚመሰክር (ዮሐ. 15፥26)፥ ትእዛዝ የሚሰጥ (የሐዋ. 8፥29፤ 13፥2) ከሆነ እንዴት የመጠበቂያ ግንብ ኃይል ብቻ ነው አለው? ኃይል አካላዊ ህልውና ያላቸው አካላት የሚሠሩትን እንዲህ ዓይነት ሥራ ሊሠራ ይችላልን?
12. ኃይል ሊያዝን፥ ሊሰደብ፥ ሊዋሽ፥ ሊታዘዙት እንዲሁም ሊላክ ይችላልን? [መንፈስ ቅዱስ ግን ሊያዝን (ኤፌ. 4፥30)፥ ሊሰደብ (ማቴ. 12፥32)፥ ሊዋሽ (የሐዋ. 5፥3–4)፥ ሊታዘዙት (የሐዋ. 13፥2) እንዲሁም ሊላክ (ዮሐ. 14፥26) ይችላል]።
13. መንፈስ ቅዱስን አስመልክቶ የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት አዘውትሮ በዋቢነት የሚጠቅሳቸው የግሪክ ቋንቋ ምሁራን መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ህልውና እንዳለው እንደሚያምኑ ያውቃሉ? [F.F Bruce, A.T Robertson, John N. Darby, R.C Trench, J.H Thayer, Marvin R. Vincent, W.E Vine, እንዲሁም R.Young[19]]
14. ኢየሱስ ክርስቶስ አካላዊ ህልውና እንዳለው እየታመነ ሰዎችን "የሚሞላ" ከሆነ (ኤፌ. 4፥10፤ 1፥23)፤ መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን መሙላቱ (ኤፌ. 5፥18) አካላዊ ህልውና የለውም ያሰኘዋል?

19. ለምሳሌ:– Richard Trench, Synonyms of the New Testament (Grand Rapids: Eerdman, 1953), ገጽ 357-361. A.T Robertson Word Pictures in the New Testament, Vol. 5 (Nashvill Broad-man Press, 1932, ገጽ. 253 W.E Vine, An Expository Dictionary of New Testament Words, Vol. 4 (old Tappan, N.J: Revell, 1966), ገጽ .64

## 3.4 የይሖዋ ምስክሮችና የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ

የይሖዋ ምስክሮችና የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር በመባል የሚታወቀው ድርጅታቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን የተነሣው መንፈሳዊ ፍጥረት ሆኖ ነው። የክርስቶስ ሰበአዊ አካል ከሙታን አልተነሣም። ነገር ግን የክርስቶስ ሰበአዊ አካል ወደ ጋዝነት ተለውጦአል ወይም ወደ አለመኖር ደረጃ ሄዶአል የሚል አስተምህሮት አለው። ይህን አስመልክቶ ከድርጅቱ እየታተሙ የሚወጡ ጽሑፎች እንዲህ ይላሉ፦

- "ንጉሥ ክርስቶስ ኢየሱስ በሥጋ ሞቶ የማይታይ ፍጥረት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል"[1]
- "በትንሣኤው ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ሰው አልሆነም ነገር ግን መንፈሳዊ ፍጥረት ሆኖ ተነሣ"[2]
  ይህ ብቻ አይደለም የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት የክርስቶስን ትንሣኤ በተመለከተ እንዲህም የሚል ግምት አለው፦
- የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ወደ ጋዝነት ተለውጦአል
- ወይም ለእግዚአብሔር ፍቅር ታላቅ መታሰቢያነት አንድ ሥፍራ ተጠብቆ ነው ያለው[3]

### መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች[4]

የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ በመንፈስ ነበር ለሚለው ትምህርታቸው የይሖዋ ምስክሮችና ድርጅታቸው የሚከተሉትን ጥቅሶች እንደ ቃለ እግዚአብሔር ማስረጃነት ይጠቀሙባቸዋል።

1. Let God Be True (1946) ገጽ. 22
2. The Kingdom is at Hand. ገጽ. 258 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም
3. Studies in the Scripture. ገጽ. 129 Vol 2
4. Reasoning from the Scriptures, ገጽ. 217,334-335 እና Insight on the Scriptures. ገጽ. 785-86



ክርስቶስ ኢየሱስ አካሉን ዳግም ካስነሣ ለኃጢአት የከፈለውን ክፍያ መልሶ ወስዶታል ማለት ነው (ማቴ. 20፥28)።

መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ሆኖ እንደተነሣ ይናገራል። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ. 15፥45 ኢየሱስ በትንሣኤው የመንፈስ ትንሣኤ እንዳደረገ ወይም መንፈስ ሆኖ እንደተነሣ መግለጽ ያስተምራል። በ1ጴጥ. 3፥18 ላይ "በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ" ማለት መንፈስ ሆኖ ተነሣ ማለት ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮት ቀመስ ባሕርይና ክብር ስላለው ከሙታን የተነሣው ከሰበአዊያን በላይ ሆኖ ነው። የኢየሱስ አምላክ ቀመስ ባሕሪው እግዚአብሔርን እንዲወክል አድርጎታል (ቆላ. 2፥9፤ ዕብ. 1፥3) ስለዚህም መንፈስ መሆን የግድ ያስፈልገዋል (ዮሐ. 4፥24)።

ኢየሱስ ሰው ሆኖ ለሰው ልጆች ስላደረገው በጎ ሥራ አምላክ መለኮታዊ መንፈስ ሸልሞታል ወይም ክብር ሰጥቶታል (ዮሐ. 17፥5)። መንፈስም ሆኖ ከሙታን በመነሣቱ ሥጋና ደም የማይወርሰውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ኢየሱስ ወርሶአል (1ቆሮ. 15፥50)። ይህም መለኮት የመሆን ሽልማት ኢየሱስን በተዘጋ ቤት ውስጥ መግባት አስችሎታል (ዮሐ. 20፥19)። ይህ ብቻም አይደለም በድንገት መታየትም ሆነ መሠወር ይችል ነበር (ሉቃ. 24፥30–36)።

ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ያለመታየቱ መንፈስ ሆኖ መነሣቱን ያረጋግጣል። ዓለም ኢየሱስን በፍጹም አያይም (ዮሐ. 14፥19)። ከሙታን የተነሣውን ኢየሱስ ማንም አላየውም፥ ሊያየውም አይችልም (1ጢሞ. 6፥16)።

ደቀ መዛሙርት ከትንሣኤው በኋላ ኢየሱስን ያወቁት በአካል ሳይሆን በምግባሩ ብቻ መሆኑ ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርት የታያቸው በተለየ አካል መሆኑን ያሳየናል። የኤማሁስ መንገደኞች ኢየሱስን ያወቁት ዳቦውን ቆርሶ፥ ባርኮ ሲሰጣቸው ነው (ሉቃ. 24፥13–31)። ማሪያም ኢየሱስን ያወቀችው ስሟን ከጠራ በኋላ ነው (ዮሐ. 20፥10–17)። ዮሐንስ ኢየሱስን ያወቀው ሌሎች ዓሣ እያጠመዱ ነው (ዮሐ. 21፥1–7)።

## የኢየሱስ ትንሣኤን በተመለከተ የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን

በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ለኃጢአታችን ክፍያ እንዳዋለ ያስተምረናል (ማቴ. 20፥28)። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ በአካል ሊነሣ አይችልም አላለም።

እርግጥ ነው (1ቆሮ. 15፥45) ኢየሱስን መንፈስ ነው ይለዋል፤ ነገር ግን ይህ ማለት ኢየሱስ መንፈስ ብቻ ነበር ማለት አይደለም። ይህን ክፍል ኢየሱስ መንፈስ ብቻ ነበር ብለን የምንተረጉመው ከሆነ አዳምም "ሕያው ነፍስ" ብቻ የሆነ፥ ቁሳዊ የሆነ አካል የሌለው ነበር ማለት ነው። ክፍሉ አዳምን ነፍስ፥ ኢየሱስን ደግሞ መንፈስ አድርጎ ማነጻጸሩ፥ አዳም ሰው ኢየሱስ መንፈስ ነው ለማለት ፈልጎ አይደለም። ነገር ግን ጳውሎስ የሚያነጻጽረው የአዳም ሕይወት ምድራዊና ተፈጥሮአዊ ነበር፤ የክርስቶስ የትንሣኤ ሕይወት ግን መንፈሳዊና ሰማያዊ ነበር። አዳም ሕይወት ያገኘው የሕይወት እስትንፋስ እፍ ሲባልበት ነው፤ ኢየሱስ ግን ሕይወት ሰጪ ነው፤ ስለዚህም የሕይወትን መንፈስ እፍ አለብን። ይህንን ነው ጳውሎስ በንጽጽር ሊያሳየን የፈለገው።

1ኛ ጴጥ. 3፥18 "በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ" ማለት የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት እንደሚለው መንፈስ ሆኖ ተነሣ ማለት አይደለም። ነገር ግን "በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ" ማለት በሥጋ ቢሞትም መንፈስ ቅዱስ ግን አስነሣው ለማለት ነው ["Made alive by the Spirit" NIV]። ስለዚህ ክፍሉ ኢየሱስ መንፈስ ሆኖ ተነሣ ሳይሆን የሚለው መንፈስ ቅዱስ ነው ያስነሣው ማለቱ ነው (ሮሜ 8፥11 ይመለከቷል)።

ስመ ጥር የግሪክ ቋንቋ ሊቃውንት ክፍሉ ኢየሱስ በሞተበት ዓርብና በትንሣኤ በተነሣበት እሑድ መካከል ስለነበረው የሽግግር ወቅት የሚተርክ እንጂ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የሚናገር አይደለም ባዮች ናቸው። ክፍሉ ስለ ትንሣኤ በፍጹም አያወራም። በሞቱና በትንሣኤው መካከል የነበረውን ወቅት የሚያሳይ ነው። ይህ ትንተና ከክፍሉ ዐውድ ጋር የሚስማማ ነው። ቀጣዩ ቁጥር (ቁጥር 19)



"በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው" ይህም በሞቱ ድል መንሣቱን ለማወጅ ነው። ድል የነሣውም እርኩሳን መናፍስትንና በኖኅ ዘመን የነበሩትን ኃጢአተኞች ነው (ቁጥር 20፤ ዘፍ. 6፥1–4፤ 2ጴጥ. 2፥4–5፤ ይሁ. 5–6፤ ቆላ. 2፥15) ይህ ትንተና ከዐውዱ ጋር መስማማቱ ብቻ ሳይሆን የክፍሉን የሐሳብ ፍሰት የተከተለ ነው። ቁጥር 18 ስለ ክርስቶስ ሞት፤ ቁጥር 19 እና 20 በሞቱና በትንሣኤው መካከል ስለነበረው ጊዜ፤ ቁጥር 21 ትንሣኤ፤ ቁጥር 22 ዕርገት።

በአጠቃላይ ከላይ እንደተመለከትነው የሥነ መለኮት ሊቃውንት ክፍሉን አስመልክቶ ሁለት የተለያየ አመለካከት አላቸው። "በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ" ማለት በሥጋው ሲሞት መንፈስ ቅዱስ አስነሣው የሚለው አንደኛው ትንታኔ ሲሆን፤ ክፍሉ ስለ ትንሣኤ ሳይሆን በሞቱና በትንሣኤው መካከል ስለነበረው ጊዜ የሚናገር ነው የሚለው ትንተና ሁለተኛው ነው። ነገር ግን በየትኛውም መንገድ ክፍሉ የይሖዋ ምስክሮች "ክርስቶስ መንፈሳዊ ፍጥረት ሆኖ ነው የተነሣው" ለሚለው ትምህርታቸው ድጋፍ ሊሆን በፍጹም አይችልም። ጴጥሮስ ክርስቶስ በሥጋዊ አካል እንደተነሣ አልካደም፤ ምክንያቱም በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ክርስቶስ በአካል እንደተነሣ ይመሰክራሉ።

የእግዚአብሔር ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው እንደሆነ ያስተምረናል። የይሖዋ ምስክሮች "ኢየሱስ መለኮት ቀመስ" ትምህርታቸው ምን ማለት ነው? ኢየሱስ አባቱን ድሮ በነበረኝ ክብር አክብረኝ (ዮሐ. 17፥5) ማለቱ ወደ ቀድሞ ክብሩ እንደሚመለስ እንጂ ሰዋዊነቱን ለመተው መፈለጉን አያሳይም። የኢየሱስ የትንሣኤ አካል እኛ ከለበስነው ሥጋና ደም የሚለየው የኢየሱስ የትንሣኤ አካል የማይሞት፥ የማይበሰብስ፥ እጅግ የከበረ፥ ወዘተ መሆኑ ብቻ ነው (1ቆሮ. 15፥50)።

ልክ ነው ኢየሱስ በተዘጋ ቤት ውስጥ ገብቶአል (ዮሐ. 20፥19፤ 26)። በእርግጥ ኢየሱስ ክርስቶስ በድንገት መታየትም ሆነ መሠወር ይችል ነበር (ሉቃ. 24፥30–36)። ነገር ግን ይህ ማለት ኢየሱስ ከሙታን የተነሣው መንፈስ ሆኖ ነው ማለት አይደለም። እግዚአብሔር በፊሊጶስ ተመሳሳይ ነገር አድርጓል (የሐዋ. 8፥36–40) ነገር ግን ፊሊጶስ መንፈስ አልነበረም። ኢየሱስ ከትንሣኤው በፊት በውሃ ላይ የሄደው (ማቴ. 14፥25–27፤ ማር. 6፥42–50፤ ዮሐ. 6፥6–20) በአካል መሆኑ ከታመነ ከትንሣኤው በኋላ በተዘጋ ቤት ውስጥ መግባቱም ሆነ መሠወሩ መንፈስ ነው እንዴት ያስኘዋል?


በእርግጥ ኢየሱስን ዓለም ዳግም አያየውም (ዮሐ. 14፥19)። ነገር ግን ይህ ማለት ኢየሱስ መንፈስ ሆኖ ነው የተነሣው ማለት አይደለም። ከትንሣኤው በፊት እንደሚያደርገው በሕዝብ ፊት አይመላለስም ለማለት ነበር እንጂ። እግዚአብሔር ኢየሱስን እንዲያዩ የፈቀደላቸው ደቀ መዛሙርቱና ሌሎች ሰዎች ኢየሱስን አይተውታል (የሐዋ. 10፥39–41)።

አንደኛ ጢሞ. 6፥16 ሰው ኢየሱስን በመለኮታዊ ክብሩ ፍጹም ማየት እንደማይችል ያስተምራል። ነገር ግን ጳውሎስና ሌሎች ጥቂት ሰዎች በክብሩም እንኳ ቢሆን አይተውታል። ክፍሉ ኢየሱስ በአካል ስላልተነሣ ማንም ሊያየው አይችልም አይልም። ሉቃ. 24፥13–31 ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን ያላወቁት "እንዳያውቁት ዓይናቸው ተይዞ ነበር" (ቁጥር 16) ይላል። እግዚአብሔር ዓይናቸውን ሲከፍትላቸው (ቁጥር 31) አወቁት። ስለዚህ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን ዘግይተው ማወቃቸው ኢየሱስ መንፈስ ስለሆነ ሳይሆን ዓይናቸው ስለተያዘ ነው።

ዮሐ. 20፥10–17 በዚህ ክፍል ላይ ማሪያም ኢየሱስን በመጀመሪያ ያላወቀችው *አንደኛ፥* ጨለማ ስለ ነበር (ቁጥር 1)። *ሁለተኛ፥* ብዙ አልቅሳ ስለ ነበር ዓይኗ በእንባ ስለተሞላ (ቁጥር 11፤ 13፤ 15)። *ሦስተኛ፥* ኢየሱስ እስኪጠራት ጊዜ ድረስ ወደ እርሱ ስላልዞረች ነበር (ቁጥር 16)። እንጂ ኢየሱስ መንፈስ ሆኖ ስለተነሣ አይደለም።

በዮሐ. 21፥1–7 ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን ያላወቁት:– *አንደኛ፥* ጊዜው "ንጋት" ላይ ስለ ነበር (ቁጥር 4)። *ሁለተኛ፥* ታንኳይቱ ኢየሱስ ከነበረበት *ሥፍራ* "ሁለት መቶ ክንድ" [(Hundred Yards) የእግር ኳስ መጫወቻ ሜዳን የሚያህል] (ቁጥር 8) ያህል ርቃ ስለነበር ነው እንጂ ኢየሱስ መንፈስ ሆኖ ከሙታን ስለተነሣ አልነበረም።

***መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ምን ይላል?***



የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የክርስትና እምነት ያረፈበት ታሪካዊ መሠረት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን አስተምህሮ አስመልክቶ እንዲህ ይላል:– "ክርስቶስም ካልተነሣ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው፤ እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት" በተጨማሪም ጳውሎስ



"ክርስቶስም ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ናት እስከ አሁን ድረስ በኃጢአታችሁ አላችሁ" (1ቆሮ. 15፥14፤ 17)። የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ አስመልክቶ ያለው እውነተኛ ትምህርት የአንድን ሰው ዘላለማዊ ሕይወት ጉዳይ ይወስናል "ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና" (ሮሜ 10፥9)።

## 1. ትንሣኤ የሚለው ቃል ቁሳዊ የሆነ አካልን ብቻ የሚያሳይ ነው

በመጽሐፍ ቅዱስ አነጋገር ትንሣኤ የሚለው ቃል ቁሳዊ አካልን ብቻ የሚያመለክት ነው። ዕብራውያን በተለይ በፈሪሳውያን ዘንድ የጻድቃን የወደፊት ሁኔታን አስመልክቶ የተለያየ አመለካከት ቢኖራቸውም፥ ሁሉም ግን ትንሣኤን ቁሳዊ አካል በጊዜያዊነትም ሆነ በቋሚነት ከመነሣት ጋር ብቻ ነበር የሚያያይዙት[5]።

ምንም እንኳ ኢየሱስ ክርስቶስ በፈሪሳውያን ግብዝነት ደስተኛ ባይሆንም፥ ሰዱቃውያን የሙታን ትንሣኤን ባለመቀበላቸው ቢነቅፋቸውም፥ ትንሣኤ በሚለው የቃል ፍቺ ላይ ግን ተመሳሳይ አቋም ነበራቸው (ማቴ. 22፥23–32)።

ጳውሎስ ቀድሞውኑ ፈሪሳዊ ስለነበር ስቃይ የደረሰብኝ በሙታን ትንሣኤ በማመኔ ነው ብሎ ነበር (የሐዋ. 23፥6–8)።

በአጠቃላይ ትንሣኤ የሚለው ቃል ያለው ትርጉም የሞተ ሰው አካል በቋሚነትም ሆነ በጊዜያዊነት ሕይወት ማግኘት ማለት ነው።

## 2. ኢየሱስ እስከ አሁን ድረስ ሰው ሆኖ ነው ያለው

በአብ ቀኝ የተቀመጠው የእግዚአብሔር ልጅ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ አሁን ድረስ ሰው ሆኖ ነው ያለው (የሐዋ. 17፥31፤ 1ቆሮ. 15፥47፤ 1ጢሞ. 2፥5)።

---

5. Norman L. Geisler, The Battle for the Resurrection (Nashville: Thomas Nelson, 1990), ገጽ. 179-181

በሐዋ. 17 ጳውሎስ ስለ ሙታን ትንሣኤ እያስተማረ (ቁጥር 32) ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን እንኳ ሰው ሆኖ እንዳለ ይናገር ነበር (ቁጥር 31)። በ1ኛ ቆሮ. 15፥47 ጳውሎስ ስለ ሁለት ሰዎች እየተናገረ ነው ያለው። የአንደኛው ሕይወት ሰማያዊ ነው፤ የሌላው ደግሞ ምድራዊ ነው። ይህ የሚያመለክተን አሁን እንኳ ኢየሱስ ሰው ሆኖ እንዳለ ነው እንጂ በአንድ ወቅት ሰው የነበረና አሁን ሰውነቱን የተወ ማለት አይደለም። 1ጢሞ. 2፥5 በዚህ ክፍል ኢየሱስ በአሁኑ ጊዜም እንኳ ሰው ባይሆን ኖሮ "ሰው" ማለት ባላስፈለገው ነበር። ኢየሱስን አማላጅ እንዲሆን ያደረገው የኛን ደምና ሥጋ መውሰዱ ነበር። ኢየሱስ የኛን ደምና ሥጋ ቀይሮ መንፈስ ሆኖ ካለ አማላጅነቱ እምኑ ላይ ነው?

## 3. ኢየሱስ ራሱ እኔ መንፈስ አይደለሁም ብሎአል

በሉቃ. 24፥39 ኢየሱስ መንፈስ እንዳልሆነ ለማስረገጥ የእጁንና የእግሩን ችንካር በማሳየት እኔው ራሴ ነኝ ብሎአል። የይሖዋ ምስክሮች እንደሚሉት ኢየሱስ ሥጋና ደም አለኝ ብሎ ለደቀ መዛሙርቱን ዳሱኝ ያለው የደቀ መዛሙርቱን እምነት ለማገዝ በመነሣቱ እንዲያምኑ ነበር የሚለው ትንተና ፍጹም ከእውነት የወጣ ነው። እንዴት ደቀ መዛሙርቱን እያታለለ እምነታቸውን ያጠናክራል?

## 4. ወንጌላት የኢየሱስ አካል ሕያው እንደሆነ ይናገራሉ

መላእክት የኢየሱስ አካል በመቃብሩ ሥፍራ ያለመገኘቱን ማብሠራቸው ኢየሱስ በአካል መነሣቱን ያሳያል (ማቴ. 28፥6፤ ማር. 16፥6)።

የኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ አካል በስቅላቱ ጊዜ በእጆቹ፥ በእግሮቹና በጎኑ የነበሩት ቁስሎች ወይም ጠባሳዎች ነበሩበት (ሉቃ. 24፥39–40፤ ዮሐ. 20፥20፤ 25፥27)።

ኢየሱስ ከትንሣኤው በኋላ ምግብ በልቶአል (ሉቃ. 24፥41–43፤ የሐዋ. 1፥4፤ ዮሐ. 21፥12–15)።

## 5. ኢየሱስ ሰበአዊ ሕይወቱን በትንሣኤ መልሶአል

ኢየሱስ አካላዊ ሕይወቱን የሰጠው (ያኖረው) ለዘላለም ሊተወው ሳይሆን በከበረ ሁኔታ ዳግም ሊያስነሣው ነው (ዮሐ. 10፥17–18)። "ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ አኖራለሁና" (ቁጥር 17) የሚለው ገለጻ



የሚያመለክተን ነፍሱን የሚያኖርበት ምክንያት ለማስነሣት ነው። (በዚህ ክፍል "ሒና" የሚለው የግሪክ ቃል ምክንያትን የሚያሳይ ነው)።

የሐዋ. 2፥24–32 "እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው፥ ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና" (ቁጥር 24) ይላል እንጂ እግዚአብሔር ኢየሱስን ከእንደገና መንፈስ አድርጎ ሠራው አይልም። "ሞት ይይዘው ዘንድ" ካልቻለ የይሖዋ ምስክሮች ለምን ሞቶ ቀረ ይሉናል?

ጴጥሮስ በመዝ. 16፥8–11 ያለውን ቃል ከክርስቶስ ጋር ያያይዘዋል (የሐዋ. 2፥25፤ 29–30) ". . . ደግሞ ሥጋዬ በተስፋ ያድራል፤ ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና . . ." (ቁጥር 26–27)። የሞተው የክርስቶስ አካል በሲኦል እንደማይቀር "ተስፋ" ያደርጋል። በዚህ ቦታ "ነፍስ" የሚለው ቃል ሰበአዊ የሆነውን ሕይወቱን የሚያሳይ ነው [እነዚህን ጥቅሶች ይመለከቷል (ማቴ. 20፥28፤ ማር. 10፥45፤ ዮሐ. 10፥17–18) በእነዚህ ክፍሎች ላይ ነፍስ (በግሪኩ ሱቼ) የሚለው ቃል የክርስቶስን ሥጋዊ ሕይወት የሚያሳይ ነው]።

## 6. የሞተው አካል ነው ከሙታን የተነሣው

ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሞተውን አካሉን ከሙታን እንደሚያስነሣ በዮሐ. 2፥19–22 ላይ ትንቢት ተናግሮ ነበር። ቁጥር 19 ላይ "ይህን" የሚለው አመልካች ቃል የሚያሳየው ኢየሱስ "ቤተ መቅደስ" ብሎ ስለሚጠራው አካሉ ነው። ይህም በሚናገርበት ጊዜ የነበረው። ኢየሱስ "አፍርሱት" (ቁጥር 19) ያለውን ነው ያስነሣው። የፈረሰው መንፈሳዊ አካል ወይም ቤተ ክርስቲያንን አይደለም። ነገር ግን አካሉን ነበር እንጂ [የይሖዋ ምስክሮች ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ስለሆነች አስነሣለሁ ያለው ቤተ ክርስቲያንን ነው የሚል አቋም አላቸው። ነገር ግን ኢየሱስ አስነሣለሁ ያለው የፈረሰውን፥ በሦስተኛውም ቀን የተነሣውን ነው]።

ኢየሱስ "በሦስት ቀን" ያስነሣው አካሉን ነበር እንጂ ቤተ ክርስቲያንን አልነበረም። "ቤተ መቅደስ" የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጥበት ምድራዊ ሕንፃ ነው።

## 7. በአንደኛ ቆሮንቶስ 15 ጳውሎስ ስለ አካል ትንሣኤ አስተምሮአል

1ኛ ቆሮ. ምዕራፍ 15 ስለ ክርስቶስም ሆነ ስለ አማኞች ያለውን የአካል ትንሣኤ በስፋት የሚያስተምር ስለሆነ ትኩረት ሰጥተን ልናጠናው ይገባል።

### ሀ. ". . . ከእናንተ አንዳንዶቹ፦ ትንሣኤ ሙታን የለም እንዴት ይላሉ?" (ቁጥር 12)

ጳውሎስ ይህን መልዕክት የጻፈው ከአቴና ትንሽ ኪሎ ሜትር ወረድ ብላ ለምትገኘው ቆሮንቶስ ነው። በዚያ የሞቱ ሰዎች ደግሞ ሕይወት ያገኛሉ የሚለው ትምህርት ተረት ነበር (የሐዋ. 17፥32)። አንድ ግሪካዊ ሰው ወደፊት ሕይወት በመንፈሳዊው ዓለም ውስጥ ይቀጥላል የሚለው ትምህርት የሚቀበለው እንጂ የሚሰናከልበት ጉዳይ አይደለም፤ ግሪካውያንን የሚያሰናክላቸው የአካል ትንሣኤ ወይም በዚሁ አካል ዳግም ሕይወት ያገኛል የሚለው ትምህርት ነው[6]።

### ለ. ". . .የምትዘራው የሚሆነውን አካል አይደለም. . ." (ቁጥር 37)

የዘር ፍሬ ከሚበቅለው ፍሬ እንደሚለይ የትንሣኤ አካል ከሚሞተው አካል የተለየ ነው። ነገር ግን በተዘራው (በሞተው) ዘር እና በበቀለው ዘር መካከል በክፍለ – ህዋስ ወይም በመሠረታዊው ተፈጥሮአቸውም ሆነ በታሪካቸው ልዩነት እንደሌላቸው ሁሉ የትንሣኤ አካል ከሞተው አካል ያለው አንድነት እንደዚሁ ነው።

### ሐ. "የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው። በመበስበስ ይዘራል፥ ባለመበስበስ ይነሣል፤ በውርደት ይዘራል፥ በክብር ይነሣል፤ በድካም ይዘራል፥ በኃይል ይነሣል፤ ፍጥረታዊ አካል ይዘራል፥ መንፈሳዊ አካል ይነሣል። ፍጥረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ።" (ቁጥር 42–44)

በክፍሉ ዐራት ጥንድ ነገሮች አብረው ተነጻጽረዋል። በመበስበስ፥ ባለመበስበስ፤ በውርደት፥ በክብር፤ በድካም፥ በኃይል፤ ፍጥረታዊ፥ መንፈሳዊ። በመጀመሪያዎቹ ሦስት ጥንዶች ስለሚሞተው አካል

6. F.F. Bruce The Acts of the Apostles. The Greek Text with Introduction and commentary 2d ed. (Grand Rapids: Eerdmans, 1952) ገጽ. 340 (on Acts 17፥32)



የተሰጡት አሉታዊ ገለጻዎች ናቸው። መበስበስ፥ ውርደት፥ ድካም ከመጀመሪያው አዳም የተወረሱ መጥፎ ነገሮች ናቸው። በመጀመሪያዎቹ ሦስት ጥንዶች ውስጥ ስለ ትንሣኤ አካል የቀረቡት ገለጻዎች የሚጠቁሙት አሉታዊ የሆኑት የውድቀት ውጤቶች እንደሚለወጡ ነው። በክፍሉ ላይ የቀረቡት የጳውሎስ ማስረጃዎች የሐሳብ ፍሰታቸው ወጥነት ያለው ነው። አራተኛው ጥንድ እንደ ላይኞቹ አብረው የተነጻጸሩ ናቸው። ይኸውም ለውድቀት መንስኤ ስለሆነው አካልና ከውድቀት ለመነሣት ምክንያት ስለሆነው አካል ነው። "ፍጥረታዊ አካል" የተባለው የኃጢአት አሉታዊ ውጤት የሆነው ነው። በኦሪት ዘፍጥረት መጽሐፍ ላይ እግዚአብሔር አምላክ አዳምን ከምድር አፈር እንዳበጀው፥ ይህንንም አካል "መልካም ነው" እንዳለ እንመለከታለን (ዘፍ. 1፥26–31)።

1ኛ ቆሮ. 2፥14–15 ስለ "መንፈሳዊ ሰው" ይናገራል። "መንፈሳዊ ሰው" ማለት ግን ቁስአዊ አካል የሌለው መንፈስ ብቻ የሆነ ማለት አይደለም። ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ያለ ማለት ነው።

በአጠቃላይ "ፍጥረታዊ አካል" በእግዚአብሔር ቢፈጠርም፥ እግዚአብሔር በመጀመሪያ "መልካም ነው" ቢለውም እንኳ በኃጢአት አማካኝነት ግን ይህ አካል ተበላሽቶአል።

### መ. "እንዲሁ ደግሞ፦ ፊተኛው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ ተብሎ ተጽፎአል፤ ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ።" (ቁጥር 45)

በዚህ ክፍል ላይ የተነጻጸሩት ነፍስ (በግሪክ፦ ሱቺ) እና መንፈስ (በግሪክ፦ ኒውማ) መፈታት ያለባቸው ከቁጥር 44 አንጻር ነው። ስለዚህ በቁጥር 44 ላይ ያለው ንጽጽር በሚሞተው አካል [ለኃጢአትና ለውጤቱ ስለባ (ተጠቂ) የሆነው] እና በትንሣኤ አካል [ከኃጢአት ተጽዕኖ ውጪ የሆነው] መካከል ነው በቁጥር 45 ላይም የምናገኘው ንጽጽር ይህንኑ ነው። አዳም በሚፈጠርበት ጊዜ ኃጢአተኛ ስላልነበር የኃጢአትም ጥቃት አልደረሰበትም። ነገር ግን በኃጢአት በመውደቁ ተበላሸ፥ ረከሰ፥ ደከመ፥ ሟች ሆነ።

### ሠ. "የፊተኛው ሰው ከመሬት መሬታዊ ነው፤ ሁለተኛው ሰው ከሰማይ ነው።" (ቁጥር 47)

ይህ ክፍል ኢየሱስን ሰው ይለዋል። ለኃጢአት ክፍያ ኢየሱስ ሰብአዊነቱን ትቶአል ከሚለው የይሖዋ ምስክሮች ትምህርት ጋር ቀጥታ ይጋጫል።

የትንሣኤ አካል አፈር ብቻ አይደለም ነገር ግን ለሕይወት ብቁ እንዲሆን የተለወጠ ነው (ቁጥር 48)

### ረ. "*. . . ሥጋና ደም የእግዚአብሔር መንግሥት ሊወርሱ አይችሉም፥ የሚበሰብሰውም የማይበሰብሰውን አይወርስም።*" (ቁጥር 50)

የይሖዋ ምስክሮች አብዛኛውን ጊዜ የመጀመሪያውን ዐረፍተ ነገር መጥቀስ ይወዳሉ። ነገር ግን ተከታዩ ዐረፍተ ነገር ግልጽ ያደርገዋል። የሚሞተው አካላችን ችግሩ ቁሳዊ አካል መሆኑ ሳይሆን ስለተበላሸ፥ በሰባሽ ስለሆነ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ "ሥጋና ደም" የሚለውን አገላለጽ በምድር ብቻ የተወሰነ መሆንን፥ ድካምን የሚገልጽ ስዕላዊ ቋንቋ ነው (ማቴ. 16፥17፤ ገላ. 1፥16፤ ኤፌ. 6፥12፤ ዕብ. 2፥14)።

"የእግዚአብሔርን *መንግሥት*" *ያለመውረሳችን* ምክንያት ከሥነ-ምግባራዊ ውድቀት የተነሣ ነው (1ቆሮ. 6፥9–10፤ ገላ. 5፥21)። ስለዚህ የእግዚአብሔርን *መንግሥት* ለመውረስ ቁሳዊ አካልን መተው ሳይሆን (1ቆሮ. 15፥50) የተበላሸውን ሁኔታችንን የሚያድስና የሚያስተካክል የመንፈስ ቅዱስ ሰማያዊ ሕይወት ማግኘት ነው (1ጴጥ. 1፥4)።

### ሰ. "*. . . ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ እኛም እንለወጣለን።* ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋል።" (ቁጥር 52–53)

ጳውሎስ በዚህ ክፍል እያጠናከረ ያለው ትምህርት ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርስ መለወጥ የግድ እንደሚያስፈልገው ነው። እሱን በማጥፋት መንፈሳዊ በሆነው አካል (ኢቁሳዊ አካል) በመቀየር አስፈላጊ አይደለም። ይህ የተበላሸው፥ ሟች የሆነው ሰብአዊነት የማይሞተውንና የማይበሰብሰውን መልበስ ያስፈልገዋል።



አሁን ያለን ይህ አካላችን ቀጣይነት ይኖረዋል፤ ነገር ግን የሚበሰብሰው ክፍል ሊለወጥ ይገባዋል።

### ሸ. "*. . . በዚያን ጊዜ፦ ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸማል።*" (ቁጥር 54)

ትንሣኤ ሞትን ድል የሚያደርገው የሚሞተው በሕይወት ሲታደስ ነው።

## በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ላይ ጥያቄ ለይሖዋ ምስክሮች

1. አሁን በአብ ቀኝ ተቀምጦ ያለው የእግዚአብሔር ልጅ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ እስከ አሁን ድረስ ሰው ሆኖ እንዳለ እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይናገራሉ (የሐዋ. 17፥31፤ 1ቆሮ. 15፥47፤ 1ጢሞ. 2፥5)። ኢየሱስ አሁን እንኳ ሰው ሆኖ ካለ የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር ኢየሱስ በመንፈስ ነው የተነሣው ለምን ይላል?
2. ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ሆኖ ከሙታን ከተነሣ፥ ጌታ ወደ ሰማይ ካረገ፥ ከ30 ዓመት በኋላ ጳውሎስ ኢየሱስ በአካል ይኖራል ለምን አለ (ቆላ. 2፥9)?
3. ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ሆኖ ከሙታን ከተነሣ አካሉ የት ሄደ? (ግምት ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ ይስጡን)
4. ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ሆኖ ከተነሣ ለምን ደቀ መዛሙርቱን "እኔ ራሴ እንደ ሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ፤ በእኔ እንደምታዩት፥ መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ አላቸው" (ሉቃ. 24፥16፤ 31)?
5. ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ሆኖ ከተነሣ የኤማሁስ መንገደኞች "ተይዞ" የነበረው ዓይናቸው ሲከፈት እንዴት ሊያውቁት ቻሉ (ሉቃ. 24፥61፤ 31)?
6. መላእክት የኢየሱስ አካል በመቃብሩ ሥፍራ ያለመገኘቱን ማብሠራቸው (ማቴ. 28፥6፤ ማር. 16፥6) ኢየሱስ በአካል መነሣቱን እንዴት አያሳይም? [ደብቀውት ነበር በውሸት ተነሥቶአል ያሉት?]
7. የኢየሱስ ክርስቶስ የትንሣኤ አካል በስቅላቱ ጊዜ በእጆቹ፥ በእግሮቹና በጎኑ የነበሩት ቁስሎች ወይም ችንካሮች በመስቀል ላይ የነበረው አካል መነሣቱን እንዴት አያመለክትም (ሉቃ. 24፥39–40፤ ዮሐ. 20፥20፤ 25፤ 27)?

8. ዮሐ. 2፥19–22 "ይህን" የሚለው ቃል የሚያሳየው ኢየሱስ "ቤተ መቅደስ" ብሎ ስለሚጠራው አካሉ አልነበረምን? (አዎ ሊሉ ይገባል) ኢየሱስ ከሙታን ያስነሣው "አፍርሱት" (ቁጥር 19) ያለውን ከሆነ፤ የፈረሰው ኢየሱስ ከሦስት ቀን በኋላ ያስነሣው አካሉን አልነበረምን? እውነቱ ይህ ከሆነ የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ኢየሱስ መንፈስ ሆኖ ነው የተነሣው ለምን ይላል?
9. ዮሐ. 2፥18–22 ኢየሱስ የሥልጣኑን ምልክት አካሉን ማስነሣቱ እንደሆነ ከተናገረ የይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ በአካል አልተነሣም ለምን ይሉናል?
10. ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ነው ከሙታን የተነሣው ለሚለው እምነታቸው የይሖዋ ምስክሮች ከቃለ እግዚአብሔር አንድ ጥቅስ ሊጠቅሱልን ይችላሉ?

### ማጠቃለያ

ዛሬ የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በስህተት የመጠበቂያ ግንብ ድርጅትን በመከተል ላይ ላሉ እውነት ፈላጊ የይሖዋ ምስክሮች የራሱን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል ትደግማለች፦ ". . . ስለምን ትደነግጣላችሁ? ስለምንስ አሳብ በልባችሁ ይነሣል? እኔ ራሴ እንደ ሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ በእኔ እንደምታዩት፥ መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ. . ." (ሉቃ. 24፥38–39)።

## 3.5 ደኅንነት በይሖዋ ምስክሮች መንገድ

የይሖዋ ምስክሮች ደኅንነት የሚገኘው በሥራ እንደሆነ ያምናሉ። ደኅንነት በጸጋና ክርስቶስ በማመን ይገኛል ለሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት የሚሰጡት የክንፈር አገልግሎት ብቻ ነው። ደኅንነት ለይሖዋ ምስክሮች፦ ለመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ሙሉ በሙሉ መገዛትና በሚያወጣቸውም ፕሮግራሞች ተካፋይ ከመሆን ውጪ የሚታሰብ አይደለም። መሠረታዊ የሆነውን የመጠበቂያ ግንብ አስተምህሮ ከድርጅቱ እየታተሙ የሚወጡት ጽሑፎች እንዲህ ይገልጹታል፦



- "ደኅንነት ለማግኘት ወደ ይሖዋ ድርጅት [የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር] ይምጡ"[1]
- "እግዚአብሔር የግንኙነት ድልድይ አድርጎ ከሚጠቀምበት [የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት] ጋር ግንኙነት ከሌለን የቱንም ያህል መጽሐፍ ቅዱስን ብናነብ በሕይወት ጎዳና ልናድግ አንችልም"[2]
- "በምድረ ገነት ዘላለማዊ ሕይወት ለማግኘት ያንን ድርጅት [የመጠበቂያ ግንብ ማኅበር] በመለየት የእርሱ አካል ሆኖ እግዚአብሔርን ማገልገል ነው"[3]
- "የዘላለምን ሕይወት ለመቸለም ጠንክረን መሥራት አለብን"[4]
- "አንድ ሰው በሕይወት መጽሐፍት ላይ ስሙ እንዲጻፍለት በሥራው ሊደገፍ ይገባዋል"[5]

እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ የመጠበቂያ ግንብ ጽሑፎች በማንበብ የይሖዋ ምስክሮች እንዴት የእግዚአብሔርን ጸጋ ሊረዱ ይችላሉ? እንደ መጠበቂያ ግንብ ጽሑፎች ጸጋ ማለት ደኅንነትን ለመሥራት የሥራ ዕድል ማግኘት ማለት እንጂ፤ ጸጋ የደኅንነት ነፃ ስጦታ ነው ማለት በፍጹም አይደለም።

የይሖዋ ምስክሮች ለመዳን የጸጋን አስፈላጊነትና በክርስቶስ የማመንን አንገብጋቢነት ይናገራሉ። ደኅንነትም "ነፃ ስጦታ" ነው ባዮች ናቸው። ነገር ግን እንደ መጠበቂያ ግንብ ጽሑፎች ጸጋና እምነት በራሳቸው በቂ አይደሉም። ደኅንነትም በእምነት ብቻ የሚገኝ ነፃ ስጦታ አይደለም።

እንደ መጠበቂያ ግንብ ትምህርት የይሖዋ ምስክሮች በዚህ ሕይወት ደኅንነት ይኑራቸው አይኑራቸው በፍጹም እርግጠኞች አይደሉም[6]።

አንድ የይሖዋ ምስክር ከኃጢአት ሊርቅና እግዚአብሔርን ፈጽሞ ሊታዘዝ ይገባዋል። በሺው ዓመትም ጊዜ የሚገጥመውን ፈተና ካላለፈ ወደ አለመኖር ደረጃ ይሄዳል። በሺው ዓመት ጊዜ እግዚአብሔርን በታማኝነት ያገለገለ የዘላለም ሕይወት ይለገሠዋል።

1. The watchtower, 15 November 1981, ገጽ. 21 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።
2. The watchtower, 1 December 1981, ገጽ. 27 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።
3. The watchtower, 15 February 1983, ገጽ 12-13 በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።
4. The watchtower, 15 August 1972, ገጽ. 491
5. The watchtower, 1 April 1947, ገጽ. 204
6. Life Everlasting – In Freedom of the sons of God. ገጽ. 398.

የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና የትራክት ማኅበር የደኅንነት አስተምህሮ ክርስቲያኖችን በሁለት ጎራ ይከፍላቸዋል። ይኸውም፡– “ቅቡዓን” እና “ታላቁ መንጋ” በማለት ነው። “ቅቡዓን” የእግዚአብሔር የመንፈስ ልጅ ሆነው ወደ ሰማይ ይሄዳሉ። እነዚህም ሰዎች በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩና ከ1935 ዓ.ም. በፊት ድርጅቱን የተቀላቀሉ ናቸው። የ“ታላቁ መንጋ” አባላት ትንሣኤን ካገኙ በኋላ በምድር ላይ ለዘላለም ይኖራሉ 1935። ይህ “ታላቅ መንጋ” ሰማይ ከሞላ በኋላ የመጣ ሲሆን [ሰማይ ሞላ የተባለው በ1935 ዓ.ም. ላይ ነው] እስከ አሁን ድረስ በምድር ላይ እየኖሩ ያሉት ናቸው። “ቅቡዓን” ሆነው ዛሬ በምድር ላይ ያሉት “ቅሬታዎች” በመባል ይታወቃሉ። ደኅንነት የሚገኘው በክርስቶስ በማመንና ተግቶ በመሥራት ነው። እንደመጠበቂያ ግንብ ትምህርት ደኅንነት የሚገኘው ሕይወትን በመቀየር ለአምላክ መንግሥት ብቁ መሆንን በማረጋገጥ ነው።

አንድ መቶ አርባ አራት ሺዎቹ [144 ሺ ናቸው የሚባሉት “ቅቡዓን” ናቸው] ብቻ ናቸው ዳግም የተወለዱት። “ቅቡዓን” ደግሞ የሚወለዱት በሰማይ መንፈስ ሆኖ ለመኖር የሚያስችል ቅድመ ሁኔታ ብቻ እንጂ ለደኅንነት አንገብጋቢ ስለሆነ አይደለም።

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ከላይ የተመለከትነውን የደኅንነት ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ለማለት ከቃለ እግዚአብሔር የሚጠቅሳቸው ጥቅሶች የሚከተሉት ናቸው።

ክርስቲያኖች በሁለት ጎራ (ቡድን) ይከፈላሉ[7]። በራእ. 7፥2–8 “ቅቡዓን” ወይም 144ሺዎቹ አንደኛው ጎራ ሲሆኑ፤ በራእ. 7፥9–17 ደግሞ “ታላቁ መንጋ” ወይም “በግ” የሚባሉት ያሉበት ሁለተኛው ጎራ ነው[8]። 144ሺዎቹ ከሰማያዊ ተስፋ ጋር መንፈሳዊ እስራኤሎች ናቸው። የሚኖሩትም በጽዮን ተራራ ላይ ነው (ራእ. 14፥1)። ይህም የሰማይ ምሳሌ ነው (ዕብ. 12፥22)። “ቅቡዓን” ከምድር ነው ወደ ሰማይ



የሚወስዱት (ራእ. 14፥3)። “ቅቡዓን” ሆኖ በምድር ላይ ወደፊት የሚኖር የለም። 144ሺዎቹ ሁሉ በሥጋ የእስራኤል ወገን መሆን የለባቸውም። አዲሱንም ዝማሬ የሚዘምሩት የእስራኤል ወገን ክርስቲያኖች ብቻ የሚሆኑበት ምንም ምክንያት የለም። ነገር ግን የአሕዛብ ክርስቲያኖችም ጭምር ናቸው። ስለዚህ 144ሺዎቹ መንፈሳዊ እስራኤል ናቸው።

“ታላቁ መንጋ” የሚባሉት እንደ “ቅቡዓን” ሰማያዊውን አካል ሳይሆን ምድርን ተስፋ የሚያደርጉት ናቸው። ታላቁ መንጋ ተስፋ የሚያደርገው በረከት (ራእ. 7፥15–17) ምድርን መውረስ ነው (ራእ. 21፥2–4)። ታላቁ መንጋ “በዙፋኑና በበጉ ፊት” ይቆማሉ (ራእ. 7፥9) ይህ ማለት ግን የታላቁ መንጋ ሰፍራ ሰማይ ነው ማለት ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነትና ሞገስ የሚያሳይ አገላለጽ ነው። ይህም አገላለጽ ኃጢአተኞች በእግዚአብሔር ፊት እንደማይቆሙ ለማነጻጸር ነው (ራእ. 6፥15–17)።

ሁለት ዓይነት ክርስቲያኖች እንዳሉ የሚያሳየው ሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል[9] (ራእ. 1፥6፤ 5፥10፤ 20፥6) ነው። ነገሥታትና ካህናት የሚሆኑት ሰዎች ከሚመሩትና በእግዚአብሔር ፊት ከሚወክሉት ሰዎች የተለዩ ናቸው። ሉቃ. 12፥32፤ ዮሐ. 10፥16 ክርስቶስ መንግሥቱን የሚሰጠው “ትንሽ መንጋ” አለው፤ ይህም መንጋ ከ“ሌሎች በጎች” የተለየ ነው [“ትንሹ መንጋ” የሚባሉት “ቅቡዓን” ናቸው። “ትልቁ መንጋ”፥ “ሌሎች በጎች” የሚባሉት ከመቶ አርባ አራት ሺው ውጪ ያሉት ናቸው]።

በእምነት ጸድቀናል ነገር ግን ጽድቃችን ጊዜያዊ ነው፤ ዘላቂነት የለውም። “ታላቁ መንጋ” በምድር ላይ ለዘላለም ይኖራል። የእግዚአብሔርን ጓደኛ ለመሆን ጸድቋአል (ያዕ. 2፥23)። ለ“ታላቁ መንጋ” እንከን አልባ የመሆን ሥልጣን ወይም ደረጃ ተሰጥቶታል። ነገር ግን በሺ ዓመቱ ጊዜ የመፈተኑ ጉዳይ በእንጥልጥል ላይ ያለ፥ ውሳኔ ያላገኘ ጉዳይ ነው። አብርሃምም ሆነ ከክርስቶስ በፊት ለነበሩ ቅዱሳን በእግዚአብሔር ተስፋ በማመናቸው በእግዚአብሔር ፊት እንከን አልባ ናችሁ ለመባል መሠረቱ ነበር (ሮሜ 4፥20–22)። “ታላቁ መንጋ”

7. በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ፤ ገጽ 120–126
8. “Great Crowd”, in In sight on the scriptures, 1: ገጽ. 995-997

9. ዝኒ ከማሁ። ገጽ 997። ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር፤ ገጽ 165–168።
10. በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ፤ ገጽ 127–133 250–255
11. “Declare Righteous,” in In sight on the Scriptures, 1: 604-606

ተብለው የተቆጠሩት ክርስቲያኖች በክርስቶስ በማመናቸው የክርስቶስ የማዳን ሥራ እግዚአብሔር እነርሱን እንደ “ጻድቃን” እንዲመለከታቸው አድርጎታል (ማቴ. 25፥34-46)። ነገር ግን እምነታቸው ጽድቅ ሆኖ የሚቆጠርላቸው ለመልካም ሥራ ያላቸው ጥረትና ለእግዚአብሔር ፈቃድ ከመታዘዛቸው ጋር ተያይዞ ነው (ያዕ. 2፥17-26)። የ“ታላቁ መንጋ” አባላት ጻድቅ መሆናቸው ገና አልተረጋገጠም። ጻድቅ መሆናቸው የሚረጋገጠው እስከ ሺ ዓመት መጨረሻ ድረስ በእምነት ለመታዘዝ የቀጠሉ እንደሆነ ብቻ ነው።

የክርስቲያናዊ ማኅበር አባላት (“ቅቡዓን”) የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን ጸድቀዋል (ዮሐ. 1፥12-13) ከኃጢአት ውጪ እንዲሆኑ የተሰጣቸው ጊዜያዊ ሥልጣን በእምነት እስካሉ ጊዜ ድረስ ቋሚ ነው። እንደ “ታላቁ መንጋ” “ቅቡዓንም” ለደኅንነታቸው መልካም ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል። “ቅቡዓን” የእግዚአብሔር የማደጎ ልጅ የሆኑት ለጊዜው ነው (ሮሜ 8፥15-16)። ነገር ግን ትክክለኛ ልጆች መሆናቸው የሚረጋገጠው በትንሣኤ መንፈስ ሆነው ከሙታን ሲነሡ ነው።

መልካም ሥራ ደኅንነትን ያመጣል። መልካም ሥራ የሚባሉት ከዚህ የሚከተሉት አራቱ ነጥቦች ናቸው[12]፡-

1. በመጠበቂያ ግንብ መሪነት መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት የእግዚአብሔርንና የክርስቶስን ነገር “ማወቅ” (ዮሐ. 17፥3)
2. ለእግዚአብሔር ሕግጋት መታዘዝ [እነዚህ ሕግጋት በመጠበቂያ ግንብ ድርጅት በኩል የተደነገጉት ናቸው። ከነዚህም ውስጥ ደምን መቀበልም ሆነ መስጠት (blood transfusions)፥ የልደት በዓላትን፥ የዓመት በዓላትን ወዘተ ማክበርን ፈጽሞ የሚከለክለው ነው]።
3. የእግዚአብሔር ድልድይ (channel) ከሆነው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ጋር ኅብረት ማድረግ።
4. በይሖዋ ምስክሮች የስብከት ሥራ ላይ ተካፋይ መሆን።

“ዳግም ልደት” ለ144ሺዎቹ ብቻ ነው[13]። “ቅቡዓን” ለእግዚአብሔር መንፈስ የሚሆኑ ልጆች ናቸው። መንፈስ እንደመሆናቸውም በሰማይ ሆነው ምድራዊ የእግዚአብሔር መንግሥትን ያስተዳድራሉ (1ቆሮ. 15፥50)። ዳግም ልደት ለእነርሱ ያስፈለገበትም ዓላማ በሰማይ

12. The watchtower, February 15, 1983, ገጽ. 12-13.
13. ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር፤ ገጽ 75-78



ስለሚጠብቃቸው ሕይወት ወደ መንፈስነት ስለሚለውጣቸው ነው (ዮሐ. 3፥4-5፤ ሮሜ 8፥16-17፤ 1ጴጥ. 1፥3-4)። “ቅቡዓን” ዳግም መወለዳቸው የእግዚአብሔርን መንፈስ እንዲቀበሉ ያደርጋቸዋል። ይህም መንፈስ ሰማያዊ ጥሪያቸውን ይገልጽላቸዋል እንዲሁም “ልባምና ታማኝ ባሪያ” የመሆን ኀላፊነታቸውን እንዲወጡ ያበረታቸዋል።

ዳግም ልደት ክርስቶስን ላመኑ ሰዎች ሁሉ አይደለም። ነገር ግን በክርስቶስ ዘመን እስራኤላዊ ሆነው ክርስቶስን የተቀበሉት ዳግም ተወልደዋል።



## የይሖዋ ምስክሮች
## የደኅንነት ትምህርት
## በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን



ሁለት ዓይነት ክርስቲያኖች አሉ የሚለው የይሖዋ ምስክሮች ትምህርት ሙሉ ለሙሉ የተመሠረተው ከአዲስ ኪዳን መጻሕፍት መካከል በጣም አከራካሪና ለመረዳትም እጅግ አስቸጋሪ በሆነው በራእይ መጽሐፍ ነው (ራእ. 7 እና 14፥1-5)። 144ሺዎቹና በራእ. 7 ላይ ያለው ታላቁ መንጋ የተለያዩ ክፍሎች ናቸው የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት ፍጹም ትክክል አይደለም። እንደ ድርጅቱ ትምህርት 144ሺዎቹ በቀጥታ ተተርጉሞ እስራኤላዊ ክርስቲያኖች ናቸው ሲባል፤ ታላቁ መንጋ ደግሞ ከተለያየ ነገድ ያመኑ ክርስቲያኖች ናቸው። ነገር ግን የክፍሉ መጻሕፍ ቅዱሳዊ ትምህርት 144ሺዎቹም ሆኑ ታላቁ መንጋ ሕዝበ ክርስቲያንን የሚወክሉ ናቸው። ይኸውም ቤተ ክርስቲያን ማለት ነው። 144ሺዎቹ በምድር ላይ በሚመጣው ቁጣ በእግዚአብሔር ማኅተም የተጠበቁ (ራእ. 7፥1-8) እንዲሁም ቁጣው እስከ ሚያልፍ በድል የቆሙ ናቸው (ራእ. 14፥1-5)። ታላቁም መንጋ የሚወክለው ቤተ ክርስቲያንን ነው፤ ይኸውም ከታላቁ መከራ በኋላ ባለማቋረጥ ለእግዚአብሔር የሚሰጠውን አምልኮ በማሳየት (ራእ. 7፥9-17)።

አንድ መቶ አርባ አራት ሺዎቹ ያሉት በሰማይ ሳይሆን በምድር ነው (ራእ. 7፥1-8)። አራቱ መላእክት ምድርንና ባሕርን ከመጉዳታቸው በፊት በእግዚአብሔር እንዲጠበቁ የታተሙ ናቸው። በተጨማሪም

144ሺው በጽዮን ተራራ ላይ ቆመው ሳለ (ራእ. 14፥1) በላይ በሰማይ መዘምራን ይዘምሩ ነበር (ቁ. 2–3)። በእርግጥ የጽዮን ተራራ ሰማያዊዋን ከተማ ሊወክል ይችላል (ዕብ. 12፥22)፤ ነገር ግን ሰማያዊዋ ከተማ ከሰማይ ወደ ምድር ወርዳለች (ራእ. 21፥2)። በመንፈሳዊው አነጋገር ክርስቲያኖች አሁን በምድር እያሉ ወደ ጽዮን ተራራ መጥተዋል (ዕብ. 12፥22)። ይህ ለ144ሺዎቹ ሰማያዊውን ዝማሬ ለመማር ከሰው ዘር ውስጥ ብቸኞቹ ናቸው (ቁ. 3)። "ከምድርም ከተዋጁት" (ቁ. 3) የሚለው አገላለጽ የሚያመለክተው 144ሺዎቹን ነው። ነገር ግን 144ሺዎቹ በሰማይ ለዘላለም ይኖራሉ ማለት ግን አይደለም። ነገር ግን በምድር ላይ ሊመጣ ካለው ቁጣ እንዲያመልጡ ወደ ሰማይ ከተወሰዱ በኋላ ተመልሰው ወደ ምድር መመለሳቸውን ነው የሚያሳየው። አዲሲቷ እየሩሳሌም ብለን በምንጠራት "አዲስ" ምድር ላይ ይኖራሉ (ራእ. 21፥1–2)።

የተባረከው ተስፋ ለታላቁ መንጋ ነው የሚለው የይሖዋ ምስክሮች አባባል ትክክል ነው (ራእ. 7፥15–17)። በአዲሲቱ ምድርም ለመኖር ተስፋ ከተሰጣቸውም ጋር አንድ ናቸው (ራእ. 21፥2–4)። የበረከታቸውም መሠረት እግዚአብሔር በእነርሱ መካከል መኖሩ ነው። እነርሱም በእግዚአብሔር ና በበጉ ዙፋን ፊት ይቆማሉ (ራእ. 7፥9)። ምክንያቱም ከመጨረሻው ፍርድ በኋላ የእግዚአብሔር ዙፋን በአዲሲቱ ምድር ስለሆነ (ራእ. 21፥3)።

የይሖዋ ምስክሮች ሁለት ዓይነት ክርስቲያኖች አሉ ለሚለው ትምህርታቸው ማስደገፊያ ከላይ ካየናቸው ጥቅሶች በተጨማሪ የሚጠቅሱት (ራእ. 1፥6፤ 5፥10፤ 20፥6) ነው። ነገር ግን በክፍሉ መንግሥትና ካህናት የሚሉት ቃላት አሁን በከፊል ወደፊት በሙላት ቅዱሳን በእግዚአብሔር በረከት የሚደሰቱትን ደስታ የሚያሳይ አገላለጽ ነው። እንደ "መንግሥት" ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን የልጅነት ግንኙነት ያመለክታል (ራእ. 21፥7)። እንዲሁም በአዲሲቷ ምድር ላይ የሚያሳዩትን ፍትሐዊ አገዛዝ ያሳያል (ዘፍ. 1፥26–30፤ መዝ. 8፥3–8)። "ካህናት" መሆናቸውም ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ መገናኘት እንደሚችሉ የሚያመለክት ነው።

ሉቃ. 12፥32፤ ዮሐ. 10፥16 ክርስቶስ መንግሥትን እሰጣችኋለው ካለው "ትንሹ" መንጋ "ከሌሎች በጎች" ጋር ፍጹም ልዩነት የለውም። ከላይ ያየናቸው የሉቃስና የዮሐንስ ወንጌላት ዐውዳቸው አብሮ የሚሄድ አይደለም። እነዚህም ክፍሎች "ታላቁ መንጋ" እና "ታናሹ መንጋ" ልዩነት አላቸው፥ ትንሹ መንጋ ትልቁን መንጋ ይመራል አይልም።



"ትንሹ መንጋ" የተባለበት ምክንያት በዚያን ጊዜ ይህ ኅብረት የክርስቶስ ትንሽ ኅብረት ስለሆነ ነው። ሁሉም ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን መንግሥት እስከፈለጉ ድረስ (ሉቃ. 12፥32) ለሁሉም ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር መንግሥት ይሰጣቸዋል (ቁ. 32)። የሚፈልግም ሁሉ ያገኛልና (ማቴ. 7፥7–8)።

ዮሐ. 10፥16 ከመጠበቂያ ግንብ ትምህርት ጋር ይጋጫል። ይኸውም ወደፊት በጎች ሁሉ "አንድ መንጋ" ስለሚሆኑ ነው። "ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ" የዚህ አባባል ታሪካዊ ዳራ የሚጠቁመን ከዚህ በረት ያልሆኑ ሌሎች አሕዛብ ማለትም ከእስራኤል ነገድ ውጪ የነበሩት በክርስቶስ "አንድ መንጋ" መሆናቸውን የሚያስተምር ነው።

የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ስለ ቅቡዓን የሚያስተምረው ትምህርት ያለው ችግር ወደ ስድስት ሚሊዮን የሚደርሱትን ምድር ናፋቂ የይሖዋ ምስክሮች ያለመሪ ሊያስቀራቸው ነው። እንደ ድርጅቱ ትምህርት ወደ "ቅቡዓን" የመቀላቀል ቁጥር (144ሺ) የሞላው በ1935 ዓ.ም. ነው። አሁን በምድር ላይ ያሉት የዚህ የ"ቅቡዓን" ክፍል አባላት [በሕይወት ያሉ "ቅቡዓን" "ቅሬታዎች" በመባል ይታወቃሉ] ቁጥር ከ8ሺ የሚያንስ ሲሆን ዕድሜያቸውም ከ70 ዓመት በላይ ነው። በቅርቡ እነዚህ "የቅቡዓን" "ቅሬታዎች" ሞተው ያልቃሉ፤ ድርጅቱም ያለመሪ ይቀራል።

ደኅንነት እምነትን ብቻ ሳይሆን ሥራንም ይጨምራል የሚለው የይሖዋ ምስክሮች ትምህርት ከቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ጋር የሚጋጭ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እምነት አስፈላጊ ነው ያለው ያለ እምነት እግዚአብሔርን ማስደሰት ስለማይቻል ነው (ዕብ. 11፥6)። እውነተኛ እምነት ደግሞ መልካምን ሥራ ፍሬው ያደረገ ነው (ያዕ. 2፥14–26)። እግዚአብሔር ደኅንነትን ያዘጋጀው ለሚያምኑ ነው እንጂ "እምነታቸውን በተግባር ላዋሉ" አይደለም። "እምነትን በተግባር ማዋል" የሚለው ቃል "ፒስቲአ" ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ነው። የቃሉም ትርጉም በአንድ ሰው ወይም ነገር መመካት ወይም ማመን ማለት ነው (ለምሳሌ፡– ዮሐ. 3፥16 18)። ትክክለኛ እምነት በሥራውና በፍሬው ይታወቃል፤ ስለዚህ እምነት እንጂ "እምነትን በተግባር በማዋል" አይደለም ለደኅንነት ቅድመ ሁኔታ (ለምሳሌ፡– ዮሐ. 3፥16, 18፤ የሐዋ. 16፥31፤ ሮሜ 1፥16–17፤ 3፥21–28፤ 2ተሰ. 1፥8–10)። መልካም ሥራ እጅግ አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ለደኅንነት ቅድመ ሁኔታ አይደለም። የመልካም ሥራ መኀደል ክርስቲያን

ክርስቲያናዊ ሥነ-ምግባር እንዳያሳይ ያደርገዋል፤ በመጽሐፍ ቅዱስ አጠራር ሥጋዊ ክርስቲያን ያስብለዋል (1ቆሮ. 3፥1-4)። ነገር ግን እምነት ብቻ የደኅንነት ዋስትና ነው (ቲቶ 1፥16፤ 1ጴጥ. 1፥5-10፤ 1ዮሐ. 2፥3-4፤ 3፥9-10, 14-15፤ 5፥2-3)።

በእምነት የጸደቅነው ለጊዜው ሳይሆን ለዘለቄታው (ለዘላለም) ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ጓደኛ ለመሆን በጸደቁት (ያዕ. 2፥23) በ"ታላቁ መንጋ" እና የእግዚአብሔር ልጅ (ዮሐ. 1፥12-13) ለመሆን በጸደቁት "ቅቡዓን" መካከል ምንም ልዩነት የለም። ሁሉም በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው (ሮሜ 8፥13-14)። መጽሐፍ ቅዱስ ለሁለት ነገር መጽደቅንም ሆነ [ግምሹ፥ ለልጅነት፥ ግማሹ ጓደኛ ለመሆን] ሁለት ዓይነት ጽድቅ አለ አይልም።

እግዚአብሔር አማኞችን ጸድቀዋል ያለው ለጊዜው ወይም ወደፊት የሚጠብቃቸውን ፈተና የሚያልፉትን አይደለም። ነገር ግን ለአንዴና ለዘላለም ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የጸደቅነው ላሁኑ ጊዜ ብቻ ነው፥ እንዲሁም ሺ ዓመት የፈተና ጊዜ ነው አይልም (ዕብ. 9፥27)። አብርሃምና ሌሎች ቅዱሳን ደኅንነታቸው የተረጋገጠው ወደፊት እምነታቸው ስለሚፈተን አይደለም። ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን በማመናቸው ብቻ ነበር። አሁንም ሰው መንግሥተ ሰማይን የሚያገኘው ልክ እንደ እነርሱ ነው (ማቴ. 8፥11፤ ሉቃ. 13፥28፤ ገላ. 3፥9)። በዚህ መልኩ የጸደቀው የአብርሃም እምነት ፍጹም ነበር (ያዕ. 2፥22)። ኖኅ "በእምነትም የሚገኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ" (ዕብ. 11፥7)። ሁሉም ክርስቲያኖች በክርስቶስ ኢየሱስ ሞት በማመናቸው ብቻ ጽድቃቸውን አውጀዋል፤ ደኅንነታቸውም የተጠበቀ ነው።

ደኅንነት የተከናወነ እውነት ነው (ሮሜ 5፥1-9) በዚህም መሠረት ነው መጽሐፍ ቅዱስ በእርሱ ከቁጣው እንድናለን (ሮሜ 5፥9) የሚለው። እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል የሰጠን ነፃ ስጦታ መጽደቅ (ሮሜ 3፥22-24፤ 5፥15-16) እንዲሁም የዘላለም ሕይወት (ሮሜ 6፥23) ነው። ሁለቱም እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚሄዱ ናቸው (ሮሜ 5፥17-18)። የጸደቁም ጻድቃን ናቸው የሚከብሩት (ሮሜ 8፥20)። አማኞች ወደፊት የመከበራቸው ጉዳይ የተረጋገጠው በተከናወነው መሠረት ላይ [ይኸውም፦ በመጽደቃቸው] ነው።

የእግዚአብሔር የማደጎ ልጅ መሆናችን (ሮሜ 8፥15-16) ወደፊት በፈተና የሚገኝ ሳይሆን የአሁን ጊዜ እውነታ ነው። ሮሜ 8፥23 የማደጎ ልጅ መሆናችን የወደፊት ጊዜን የሚያሳይ ነው። ነገር ግን ይህ ማለት



አሁን የእግዚአብሔር የማደጎ ልጅ አልሆንም ማለት ሳይሆን የአሁኑ ልጅነታችን የሚገለጠው ወደፊት ነው ማለት ብቻ ነው (ቁ. 18-119፤ 1ዮሐ. 3፥1-2)። የማደጎ ልጅነታችንንም መገለጥ እየተጠባበቅን እንጂ ለማደጎ ልጅነታችን እየሠራን አይደለም (ቁ. 23-24)።

መልካም ሥራ ለደኅንነታችን ቅድመ ሁኔታ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ የእምነት ትምህርቶች የሚቀዱበት፥ ደኅንነትም ሆነ መልካም ሥራ የሚገነቡበት፥ የእግዚአብሔር ሥልጣናዊ ቃል ነው (2ጢሞ. 3፥15-17)። የዘላለም ሕይወት የሚገኘው "ዕውቀትን በመገብየት" ሳይሆን እግዚአብሔርንና ክርስቶስ በ"ማወቅ" ነው (ዮሐ. 17፥3)። ከአብና ከወልድም ጋር ግንኙነት የሚመሠረተው በእምነት ነው። ለደኅንነት የመጠበቂያ ግንብ ጽሑፎችን ማንበብ አለብህ የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርት ከቃለ እግዚአብሔር ጋር ይጋጫል። ከዚህም በተጨማሪ የእግዚአብሔርን የጽድቅ ሥራ ከንቱ ያደርጋል (ሮሜ 3፥21-26)።

እውነተኛ ክርስቲያን ባሕርይውን፥ ምግባሩንም ሆነ አስተሳሰቡን በእግዚአብሔር ቃል መቅረፅ አለበት። ነገር ግን መልካም ሥነ-ምግባር የደኅንነት መሠረት ሳይሆን የደኅንነት ፍሬ ነው። ዛሬ በመጠበቂያ ግንብ በኩል እየተላለፉ ያሉት ሕግጋት [ለምሳሌ፦ ደም መስጠትና ደም መቀበል [blood transfusion]፥ የልደት በዓላት፥ የሕዝብ በዓላት ወዘተ] በመጽሐፍ ቅዱስ የተሰጠ ትምህርት አይደለም። እነዚህም ነገሮች የደኅንነትም ሆነ የቅድስና መሠረት አይደሉም።

መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ የሃይማኖት ድርጅት ጥላ ሥር መጠለል ወይም ከድርጅቱ ጋር መተባበር ለደኅንነት መሠረት ነው አይልም። እውነተኛ ክርስቲያኖች መሰሎቻቸውን መውደድ፥ ከእነርሱም ጋር ኅብረት ማድረግ እንዳለባቸው ያስተምራል (1ዮሐ. 3፥14፤ 4፥20፤ 5፥1)።

ደኅንነት ከእምነት በስተቀር በምንም ነገር ላይ የተመሠረተ ስላልሆነ በስብከትም ሆነ በማስተማር ሥራ ላይ ተካፋይ መሆን ለደኅንነት አንገብጋቢ ጉዳይ ተደርጎ የሚሠራጨው የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጋጭ ነው። ክርስቶስ አሥራ ሁለቱን ለወንጌል ሥራ ማሰማራቱም ሆነ (ማቴ. 10፥5-42፤ ሉቃ. 9፥1-6) 72ቱን መላኩ (ሉቃ. 10፥1-16) ለኛ እንደ ምሳሌ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ክርስቲያናዊ ሕግ ልናደርገው በፍጹም አንችልም።

ክርስቲያኖችን ሰማይ ወራሽ እና ምድር ወራሽ ብሎ ለሁለት መክፈል መጽሐፍ ቅዱሳዊ እስካልሆነ ድረስ የመጠበቂያ ግንብ ስለ ዳግም ልደት የሚሰጠው ትምህርት ትክክል ሊሆን አይችልም። ክርስቲያኖች መንፈስ ሳይሆን የከበሩ ሰዎች ነው የሚሆኑት (1ቆሮ. 15፥47–57)። የትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ዳግም ልደት አንድ ሰውን መንፈስ ወደ መሆን ሕይወት የሚያሸጋግረው ነው አይልም (ለምሳሌ 3፥3–5፤ ሮሜ 8፥16–17፤ 1ጴጥ. 1፥3–4)። ስለዚህ "ዳግም ልደት" እንደ መጠበቂያ ግንብ ትምህርት ለጥቂት ሰዎች ብቻ የሚሆን፥ ጥቂት ክርስቲያኖችን ሰማያዊ ጥሪ እንዳላቸው የሚጠቁም፥ ወይም በሌሎች ክርስቲያኖች ላይ መሪና አለቃ እንዲሆኑ ኃይል የሚሰጥ አይደለም።

ዮሐ. 1፥12–13 "ለተቀበሉት" የሚለው ግሥ ኀላፊ ጊዜን ቢያሳይም እንኳን በአሁኑ ጊዜ ሰዎች ዳግም አይወለዱም ማለት አይደለም። የይሖዋ ምስክሮች ራሳቸው ብዙ ሰዎች ከእኛ መካከል ዳግም ልደትን አግኝተዋል ይላሉ። በሐዋርያው ዮሐንስ የቃል አጠቃቀም መሠረት ሁለት ዓይነት ሰዎች አሉ። እነርሱም፦ የእግዚአብሔር ልጆችና የሰይጣን ልጆች ናቸው (1ዮሐ. 3፥10)። ዮሐንስ ከእግዚአብሔር የተወለዱ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው ካለ (ዮሐ. 1፥13) እንዲሁም ከእግዚአብሔር ያልተወለዱ የሰይጣን ልጆች ከሆኑ፤ አማኞች ሁሉ ዳግም ተወልደዋል ማለት ነው።

## መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ደኅንነት ምን ይላል?



ሁሉም ክርስቲያኖች እኩል የሆነ ሥልጣን አሁንም ሆነ ወደፊት አላቸው። ሁሉም ክርስቲያኖች በአዲሲቱ ምድር ይኖራሉ (ራእ. 21፥1–4)። አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ ምድር ከወረደች የቅዱሳን መኖሪያ ምድር ነው ማለት ነው። ይህም ለእግዚአብሔር ሕዝቦች መኖሪያ ምድር ነው ማለት ነው። ይህም ለእግዚአብሔር ሕዝቦች መኖሪያ ተምሳሌታዊ (ሥዕላዊ) ገለጻ ነው። ይኸውም ሕይወት ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሚመጣ፤ ወደፊት የከበረም አዲስ ሕይወት በምድር እንደሚሆን ነው። ዮሐንስ በመቀጠል እንዲህ ይላል፦ "እነሆ፥ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል" (ቁ. 3)። ክፍሉ ጥቂት የተመረጡ ሰዎች



ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር ወደ ሰማይ ይሄዳሉ አይልም። ነገር ግን እግዚአብሔር ራሱ ከሰዎች ጋር ለመኖር ይመጣል፥ እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል ነው የሚለው። አሁን ክርስቲያኖች ወደ ሰማይ የሚሄዱት የትንሣኤን ቀን ለመጠበቅ ነው። ነገር ግን እኛ ወደ መንግሥተ ሰማይ ሳይሆን የምንሄደው መንግሥተ ሰማይ ወደ እኛ ትመጣለች።

ራእ. 5፥10 ክርስቲያኖች "በምድርም ላይ ይነግሣሉ" የሚለው ዐረፍተ ነገር በአዲሲቱ ዓለም ትርጉም [NWT] "ከምድርም በላይ ይነግሣሉ" [over the earth] ይለዋል። ነገር ግን ይህ ትርጉም በመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ተቀባይነት የለውም። በአዲስ ኪዳን ግሪክ "ኢፒ" የሚለው የግሪክ ቃል 63 ጊዜ "ምድር" ከሚለው ቃል ጋር ተያይዞ ተጠቅሶአል። ነገር ግን አንድም ቦታ ላይ ከምድር በላይ ተብሎ አልተተረጎመም። ቃሉ በራእ. 5፥10 13 ላይ የተተረጎመው በዚህ መልኩ ነው።

ክርስቲያኖች ሁሉ ትንሣኤ አግኝተው ዘላለማዊ ሕይወትን በአዲሲቱ ምድር ላይ ለዘላለም መኖር ከመጀመራቸው በፊት በሰማይ ከክርስቶስ ጋር ይቆያሉ። በራእ. 7፥9–17 ላይ ያለው "ብዙ ሕዝብ" እና በሰማይ ያለው ብዙ ሕዝብ መካከል ብዙ ትይዩ እውነታዎች አሉአቸው። ይኸውም፦ በሁለቱም ክፍሎች ላይ "ብዙ ሕዝብ" የሚለው ቃል አለ (ራእ. 7፥9፤ 19፥1, 6)። በእነዚህም ክፍሎች ላይ ብቻ ነው "ብዙ ሕዝብ" የሚለው አገላለጽ በራእይ መጽሐፍ ላይ ያለው። በሁሉቱም ክፍል ላይ ያሉት "ብዙ ሕዝብ" "በታላቅ ድምፅ" ይጮኻሉ (ራእ. 7፥10፤ 19፥1) የጩኸታቸውም አጀማመር አንድ ዓይነት ነው "በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው" (7፥10)፥ "ማዳንና ክብር፥ ኃይልም የአምላካችን ነው" (19፥1)። በእነዚህም ሁለት ክፍሎች ላይ ብቻ ነው "ማዳን የአምላካችን ነው" የሚለው ዐረፍተ ነገር የሚገኘው። ከዚህም በኋላ ሽማግሌዎቹና አራቱ ፍጥረታት "ወድቀው" ለእግዚአብሔር ይሰግዳሉ፤ የመጀመሪያ ቃላቸውም "አሜን" (7፥11–12፤ 19፥4) የሚለው ነው።

ሉቃ. 23፥43 እንደ መጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርት ንስሐ የገባው ወንበዴ ለሰማያዊ ሕይወት ብቁ አይደለም። ምክንያቱም የክርስቲያናዊ ጉባዔ ተጠማቂ አባል ስላልሆነ። ነገር ግን ኢየሱስ ከእርሱ ጋር *አሁን በገነት* እንደሚሆን ቃል ገብቶለታል። ይህ የሚያሳየን አማኝ ሁሉ በሚሞትበት ጊዜ ነፍሱ ወይም መንፈሱ ንቁ ስለሆነ ከጌታ ጋር ለመሆን ወደ ሰማይ እንደሚሄድ ነው።

ሁሉም ክርስቲያኖች የዘላለምን ሕይወት እኩል ይወርሳሉ። (ማቴ. 5፥3-12) የተራራው ስብከት የሚናገረው ስለ አንድ ሕዝብ እንጂ ስለተለያዩ ሁለት ክፍሎች አይደለም [የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑት "ብፁዓን" ናቸው ምድርን የሚወርሱት]። ኤፌ. 4፥4 ክርስቲያን ሁሉ አንድ ተስፋ ካለው መጠበቅ ያለበት ተመሳሳይ ተስፋ ነው።

ጳውሎስ እንደሚለው ሁሉም ክርስቲያኖች "የክርስቶስ አካል" ናቸው (ኤፌ. 4፥3-4)። ክርስቲያኖች ሁሉ "አንድ አካል" ከሆኑ የዚህ አካል፥ ክፍል ያልሆነ ክርስቲያን አይደለም ማለት ነው። 1ቆሮ. 12፥12-27 ላይ ጳውሎስ የአንድ አካል ብልቶች አንዱ ከሌላው እንደሚሻል ወይም የበለጠ እንደሆነ አድርጎ ራሱን መቁጠር እንደሌለበት ያስተምራል [እንደ መጠበቂያ ግንብ ትምህርት አብዛኛው የይሖዋ ምስክር ("ታላቁ መንጋ") ጭራሹኑ የዚህ አካል ክፍል አይደለም]። ሮሜ 12፥4-8 ሌሎችን የሚያገለግሉ፥ የሚያበረታቱ፥ ምሕረትን የሚያሳዩ ወዘተ ክርስቲያኖች የክርስቶስ አካል እንደሆኑ ሁሉ የሚያስተምሩ፥ የሚመሩና የሚተነቢዩም የክርስቶስ አካል ናቸው።

በጸጋ በእምነት በኩል የተገኘ ደኅንነት መልካም የሥራ ፍሬ ያፈራል። በእምነት ብቻ የዳኑን ሰዎች ብንሆንም እንኳ የሚያድን እምነት መልካምን ሥራ ፍሬው ያደረገ ስለሆነ አማኝ የመንፈስ ፍሬ የሆነው መልካም ሥራ ይታይበታል። እምነት ብቻ ነው ደኅንነት የሚያገኙትንና የማያገኙትን የሚለየው። ለዚህም ነው ቃለ እግዚአብሔር የእምነትን አንገብጋቢነት በስፋት የሚያስተምረው (ለምሳሌ፡- ዘፍ. 15፥6፤ ዕብ. 2፥4፤ ዮሐ. 3፥14-18፤ 20፥30-31፤ የሐዋ. 16፥31፤ ሮሜ 1፥16-17፤ 3፥22-28፤ 4፥3-5፤ 5፥1-2፤ 10፥9-11፤ ኤፌ. 2፥8፤ ቲቶ 3፥8፤ ዕብ. 4፥2-3፤ 1ጴጥ. 1፥5፤ 1ዮሐ. 3፥23-24፤ 5፥10, 13)።

እውነተኛ እምነት ታዛዥነትን የሚያፈራ፥ መልካም ሥራን የሚሠራ፥ ፍቅርን የሚያሳይ ነው (ሮሜ 1፥15፤ 16፥25-26፤ ገላ. 5፥6፤ ያዕ. 2፥14-26)። ለእግዚአብሔር ትዕዛዝ ተገዥ ያልሆኑ ሰዎች በትክክል ያላመኑ ናቸው፤ በትክክል ያላመኑም ደኅንነት የላቸውም (1ቆሮ. 6፥9-11፤ ገላ. 5፥19-21፤ ኤፌ. 5፥5-6፤ 1ዮሐ. 1፥6፤ 2፥3-6, 9-11፤ 3፥6-15፤ ራእ. 21፥8)።

ሐዋርያት ክርስቲያን ኃጢአትን መሥራት ማቆም እንደሚገባው፥ ቅድስናን ማጎልበት እንዳለበት ማስተማራቸው እውነተኛ ክርስቲያን ከኃጢአት ጋር ዕለት በዕለት እንደሚታገል፤ ታግሎም ወደ ብስለትና



ወደ ግብረገባዊ እድገት እንደሚመጣ ያሳያል። ክርስቲያን ከኃጢአቱ ጋር መታገሉ ደኅንነቱንም ሆነ በእግዚአብሔር ላይ ያለው እምነት በጥያቄ ውስጥ እንዲወድቅ ሊያደርግ አይገባውም (ገላ. 5፥16-26፤ ኤፌ. 4፥25-32፤ 1ተሰ. 4፥1፤ ዮሐ. 3፥17-18)።

አንድ ኃጢአት ብቻ ሰዎችን ከዘላለም ሕይወት ያጎድላቸዋል። ይኸውም፡- እውነትን እያወቁ ለማያምኑ፥ በክርስቶስም የሚያምነውን ሰው ከክርስቶስ የሚርቁ ናቸው (ዕብ. 2፥1-3፤ 6፥4-6፤ 10፥26-29፤ 2ጴጥ. 2፥20-22፤ 1ዮሐ. 5፥16)።

ደኅንነት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፤ እኛ ልንሠራው የምንችለው ነገር ቢኖር በእምነት መቀበል ብቻ ነው። በእግዚአብሔር ላይ ያለን ትክክለኛ አቋም፥ እምነታችን፥ በቅድስና ማደጋችን፥ እስከ መጨረሻው በእምነት ጸንተን መቆማችን በእግዚአብሔር ጸጋና ኃይል ነው (ዮሐ. 3፥16-17፤ የሐዋ. 18፥27፤ 20፥24፤ ሮሜ 3፥23-24፤ 5፥15-21፤ ኤፌ. 1፥18-19፤ 2፥4-10፤ ፊል. 1፥6፤ ቲቶ 3፥7፤ ዕብ. 4፥16፤ 1ጴጥ. 1፥5) ። ጸጋን ለማግኘት የምንሠራ ከሆነ ጸጋ ምኑን ጸጋ ሆነ? [ጸጋ ማለት የእግዚአብሔር ነፃ ስጦታ ማለት ነው (ሮሜ 4፥2-4፤ 11፥6፤ ገላ. 2፥21)]።

ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው (ዮሐ. 3፥3-5)። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ማለት በሚመጣው አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ላይ መኖር ከበረከቱም ተካፋይ መሆን ማለት ነው (ማቴ. 5፥19-20፤ 7፥21፤ 18፥3፤ 19፥23-25፤ 21፥31፤ ማር. 9፥47፤ 10፥23-26)። ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ያልተወለደ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት አይችልም ካለ ክርስቲያን ሁሉ ዳግም ሊወለድ ያስፈልገዋል ማለት ነው (ዮሐ. 3፥3-5)።

ሮሜ 8፥14-16 በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና (ቁ. 14) ክርስቲያኖች ሁሉ በመንፈስ መመራት ካለባቸው፥ በመንፈስ የሚመሩ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆኑ ክርስቲያን ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ማለት ነው። የባርነትን መንፈስ ካልተቀበልን የተቀበልነው የልጅነት መንፈስ ነው ማለት ነው (ቁ. 15)። የልጅነት መንፈሱን የተቀበለና እግዚአብሔርን አባ የሚለው ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ሁሉም ክርስቲያን እግዚአብሔርን አባት ካለው ለሁሉም ክርስቲያን እግዚአብሔር አባት ነው ማለት ነው። የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆንን ያ መንፈስ የሚነግረን ከሆነ (ቁ. 16) አንድም የሃይማኖት ድርጅት የእግዚአብሔር ልጆች አይደላችሁም ሊለን አይችልም።

ገላ. 3፥23–4፥7 አሁን ክርስቶስን የሚያምን ሁሉ ከሞግዚት በታች (ቁ. 23–25) አይደለም። በእምነት በኩል ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች ነን (ቁ. 26)። ከክርስቶስ ጋር የተጠመቀ ወይም እንደ ክርስቲያንነቱ ጥምቀትን የወሰደ ሁሉ ክርስቶስን ለብሶታል (ቁ. 27)። ክርስቶስንም የለበሰ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ ነው (ቁ. 26–27)። ክርስቶስ ከመምጣቱ በፊት ለባርነት ከቀንበር ሥር ነበርን። አሁን ክርስቶስ መጥቶአል፤ የእግዚአብሔርም ልጆች እንድንሆን ተዋጅተናል (4፥1–5፥7)። ይህ የሚያመለክተን በክርስቶስ የተዋጀ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ እግዚአብሔርን አባ እንድንለው ያስተምረናል። ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆንን ልናውቅ ይገባል (4፥6፤ ሮሜ 8፥15–16)።

1ጴጥ. 1፥3 12–23 ዳግም በመወለዳችን ሕያው ተስፋ አለን (ቁ. 3)። ይህ የሚያመለክተን ሕያው ተስፋ ያለው ሁሉ ዳግም እንደተወለደ ነው። መንፈሳዊ ፍሬ ማፍራት የቻልነው [ለምሳሌ፦ ፍቅር፥ ቅድስና] ዳግም ስለተወለድን ነው (ቁ. 22–23)።

1ዮሐ. 3፥9–10፤ 5፥1–2 18–19 ክርስቶስ ነው ብሎ በእግዚአብሔር የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዶአል (5፥1)። በዮሐንስ አነጋገር "ከእግዚአብሔር መወለድ" ማለት የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ማለት ነው (5፥1፤ 3፥9–10፤ 5፥18–19፤ ዮሐ. 1፥12–13)። ዳግም መወለድ ማለት ከእግዚአብሔር መወለድ ማለት ነው (ዮሐ. 3፥3–5)። ዳግም ልደት የክርስቲያንን ሕይወት ስለሚቀይር ክርስቲያን ኃጢአትን አያደርግም (1ዮሐ. 3፥9–10፤ 5፥18፤ 2ቆሮ. 5፥17) ይህም ነው ዳግም መወለድ ለክርስቲያን አንገብጋቢ ጉዳይ የሚያደርገው።

## ደኅንነትን አስመልክቶ ጥያቄ ለይሖዋ ምስክሮች

1. እንደ መጠበቂያ ግንብ አስተምህሮ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መንፈሳዊ በረከቶች ለቅቡዓን ማለትም ለ144ሺዎቹ ብቻ ነው[14]።
   - ዳግም መወለድ (ዮሐ. 3፥3–8፤ ቲቶ 3፥5፤ 1ጴጥ. 1፥3፤ 1ዮሐ. 5፥1)።
   - የእግዚአብሔር የማደጎ ልጆች መሆን (ዮሐ. 1፥12–13፤ ሮሜ 8፥14–17፤ ገላ. 4፥6–7፤ ኤፌ. 1፥5)።
   - የክርስቶስ ወንድም መሆን (ሮሜ 8፥29፤ ዕብ. 2፥11–17፤ 3፥1)።

14. Robert M. Bowman, "Only for the 144,000" Fact Sheet, Christian Research Institute.



- የክርስቶስን መልክ መምሰል (ሮሜ 8፥29፤ 2ቆሮ. 3፥18)።
- ከክርስቶስ ጋር ኅብረት ማድረግ (2ቆሮ. 5፥17፤ ኤፌ. 1፥3)።
- ከክርስቶስ ጋር መወረስ (ሮሜ 8፥17)።
- የአዲሱ ኪዳን አባላት መሆን (ሉቃ. 22፥20፤ ዕብ. 12፥20–29)።
- ከክርስቶስ ሞት ጋር መጠመቅ (ሮሜ 6፥3–8፤ ፊል. 3፥10–11፤ ቆላ. 2፥12, 20፤ 2ጢሞ. 2፥11–12)።
- የጌታን እራት መውሰድ (ሉቃ. 22፥15–20፤ 1ቆሮ. 11፥20–29)።
- በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ (1ቆሮ. 12፥13)።
- የቤተ ክርስቲያን አባል መሆን (ሮሜ 12፥5፤ 1ቆሮ. 12፥13፤ ኤፌ. 4፥4)።
- የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አባል መሆን (1ቆሮ. 3፥16፤ ኤፌ. 2፥20–22፤ 1ጴጥ. 2፥5)።
- የአብርሃም ዘር አባል መሆን (ገላ 3፥26–29፤ 6፥15–16)።
- የንጉሥ ካህን መሆን (1ጴጥ. 2፥4–9፤ ራእ. 1፥6፤ 5፥10)።
- በእምነት መጽደቅ (ሮሜ 3፥22–28፤ 5፥1፤ ቲቶ 3፥7)።
- መቀደስ (1ቆሮ. 1፥2፤ 6፥11፤ ኤፌ. 1፥4፤ 1ቆሮ. 15፥50፤ 1ጴጥ. 1፥4)።
- ከክርስቶስ ጋር መምራት (1ቆሮ. 6፥2፤ 2ጢሞ. 2፥12፤ ራእ. 20፥6)።
- ክርስቶስንና እግዚአብሔርን የማየት ዕድል ማግኘት (ማቴ. 5፥8፤ 1ዮሐ. 3፥2)።

"ሌሎች በጎች" ዳግም ሳይወለዱ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዴት ሊወርሱ ይችላሉ (ዮሐ. 3፥3–8)? በአዲሱ ኪዳን ውስጥ ከሌሉ በአሮጌው ወይም በሌላ ኪዳን ውስጥ ናቸው ማለት ነው (ሉቃ. 22፥20፤ ዕብ. 12፥20–22)? የጌታን እራት ካልወሰዱ እንዴት የዘላለም ሕይወት ይኖራቸዋል? እንዴት ኢየሱስ ክርስቶስ በመጨረሻው ቀን ያስነሣቸዋል (ዮሐ. 6፥52–56)? ከክርስቶስ ሞት ጋር ካልተባበሩስ እንዴት በትንሣኤ ቀን ይነሣሉ (ሮሜ 6፥3–8)? በመንፈስ ቅዱስ ሳይጠመቁ እንዴት የእርሱ ወገን ይሆናሉ (ሮሜ 8፥9፤ 1ቆሮ. 12፥13)? የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ አባል ካልሆኑስ እንዴት፥ እንዴትስ በዋጋ [በክርስቶስ ደም] የተገዙ ሊሆኑ ይችላሉ (1ቆሮ. 3፥16፤ 6፥19፤ ኤፌ. 2፥20–22፤ 1ጴጥ. 2፥5)?

2. ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን እንደ እረኛ ደቀ መዛሙርቱን እንደ በግ መስሎአቸው ነበር (ለምሳሌ፡- ማቴ. 10፥16)። የእርሱም ስቅላት ደቀ መዛሙርቱን እንደሚበታትናቸው እንዲህ ሲል ትንቢት ተናግሮ ነበር፡- “ሁላችሁ በእኔ ትሰናከላላችሁ፤ እረኛውን እመታለሁ የምንጋውም በጎች ይበተናሉ” (ማቴ. 26፥31)። ጌታ በዚህ ስፍራ ደቀ መዛሙርቱን “በግ” ያለው በቀላሉ ስለሚደነግጡ፥ በጣም ጥቂት ስለሆኑ ወዘተ ብቻ ነው። ጌታ በሉቃ. 12፥32 ላይም የሚናገረው ለነዚሁ ደቀ መዛሙርት ነው። ስለዚህ “ታናሹ መንጋ” በተባለውና “በግ” በተባለው መካከል ልዩነት አለ የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርት ከቃለ እግዚአብሔር የተቀዳ ነውን?

3. ሉቃ. 12፥22–34 አንድ ዐውደ ንባብ ነው። ክፍሉም “ለደቀ መዛሙርቱም እንዲህ አለ፡-” በሚለው ዐረፍተ ነገር በመጀመር እስከ ቁጥር 34 ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ያለውን ነገር ይተርካል። ይኸውም ደቀ መዛሙርት በሚባሉት፥ በሚለብሱትና በሌላም ነገር መጨነቅ እንደሌለባቸው፤ ጭንቀት የሚፈይደው ነገር እንደሌለ (ቁ. 25–26)፤ እንደውም መጨነቅ የእምነት ማጣት ችግር መሆኑን (ቁ. 29)። ነገር ግን እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ነገር እንደሚያውቅ (ቁ. 30)፤ የሚያስፈልጋቸውን ነገር እንደሚሰጣቸው (ቁ. 32) ነው። ስለዚህ ይህ ዐውደ ንባብ ከራእይ 7 እና 14 ጋር በማያያዝ ስለ 144ሺው ነው የሚናገረው ማለት እንዴት ይቻላል?

4. የ144ሺው ቁጥር በ1935 ዓ.ም. ሞላ የሚለውስ የድርጅቱ ትምህርት ከየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተወሰደ ነው? [በ1935 ዓ.ም. ሰማይ እንደ ሞላ “መገለጥ” አገኘ የሚባለው የድርጅቱ ሁለተኛ ፕሬዚዴንት ሮዘርፎርድ ነው። ድርጅቱ መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል የሚከተል በምድር ላይ የሚገኝ ብቸኛ ድርጅት እኔ ነኝ እስከ አለ ድረስ ለዚህ “መገለጥ”መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ሊያቀርብ ይገባዋል]።

5. እግዚአብሔር ሰማያዊ ዜግነትን ለ144ሺው ብቻ ነው የሰጠው የሚለው ክፍል የትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላይ ነው የሚገኘው? [ራእይ 7 እና 14 ላይ ሰማያዊው ዜግነት ለ144ሺው ብቻ ነው አይልም። ስለዚህ የይሖዋ ምስክሮች ሰማያዊ ዜግነት ለ144ሺው ብቻ ነው የሚለውን ትምህርት ከየት እንዳመጡት አጥብቀን ልንጠይቃቸው ይገባል]።

6. 1ዮሐ. 5፥1 “ክርስቶስ ነው ብሎ በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ በእግዚአብሔር ተወልዶአል” ይላል። በዮሐንስ አነጋገር “ከእግዚአብሔር መውለድ” ማለት “ዳግም መወለድ” ማለት ነው (ዮሐ. 3፥3–5)። በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ከተወለደ ዳግም ልደት ለ144ሺው ብቻ ነው የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት ከየት የመጣ ነው?



7. በዮሐንስ አነጋገር “ከእግዚአብሔር መውለድ” ማለት “የእግዚአብሔር ልጅ”መሆን ማለት ከሆነ (1ዮሐ. 3፥9–10፤ 5፥1–2 18–19፤ ዮሐ. 1፥12–13፤ 3፥5) ከ144ሺው ውጪ ናቸው የተባሉት፥ ከ6 ሚሊዮን የማያንሱ የይሖዋ ምስክሮች ዳግም መወለድ አያስፈልጋቸውም የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት ከቃለ እግዚአብሔር የተገኘ ነውን?

8. አብርሃም፥ ይስሐቅና ያዕቆብን ጨምሮ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን በምድር ነው የሚኖሩት የሚለው የይሖዋ ምስክሮች ትምህርት አብርሃም፥ ይስሐቅንና ያዕቆብን ጨምሮ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን በመንግሥተ ሰማይ ነው የሚኖሩት ከሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል [ለምሳሌ፡- ማቴ. 8፥11 እና ሉቃ. 13፥18] ጋር አይጋጭም?

9. “ቅቡዓን” የሚባሉት የይሖዋ ምስክሮች በሰማይ ይኖራሉ የ“ሌሎች በጎች” ክፍል የሆኑት የይሖዋ ምስክሮች ዳግም በምድር ይኖራሉ የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርት “አንድ መንጋ” “እረኛውም አንድ” ከሚለው ከዮሐ. 10፥16 ትምህርት ጋር አይቃረንም?

10. “ቅቡዓን” የሚባሉት የይሖዋ ምስክሮች ተስፋቸው ሰማይ ከሆነና “ሌሎች በጎች” የሚባሉት ደግሞ ተስፋቸው ምድር ከሆነ ሁላችንም የተጠራነው ለአንድ ተስፋ ነው የሚለውን የኤፌ. 4፥4 ትምህርት ድርጅቱ እንዴት ይመለከተዋል?

11. በራእይ መጽሐፍ “ፊት” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ነው። 144ሺው በእግዚአብሔር ዙፋን “ፊት” እንዳሉ (14፥3)፥ መላእክትም በእግዚአብሔር ዙፋን “ፊት” እንዳሉ (7፥11)፥ 24ቱ ሽማግሌዎች በእግዚአብሔር ዙፋን “ፊት” እንዳሉ ሁሉ (5፥8)፥ “እጅግ ብዙ ሕዝብ” የተባሉትም በእግዚአብሔር ዙፋን “ፊት” እንዳሉ (7፥9) ይናገራል። ቃል እግዚአብሔርን አተርጓጎማችን ወጥነት ያለው ከሆነ “እጅግ ብዙ ሕዝብ” በሰማይ ነው ያለው ወይስ በምድር? ታናሹ መንጋ በሰማይ “እጅግ ብዙ ሕዝብ” በምድር የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርት እንዴት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሊሆን ይችላል?
“እጅግ ብዙ ሕዝብ” እግዚአብሔርን በመቅደሱ ቀንና ሌሊት የሚያገለግሉት ከሆነና (ራእ. 7፥15) የእግዚአብሔር መቅደስም በሰማይ ከሆነ (ራእ. 11፥19፤ 14፥17) እጅግ ብዙ ሕዝብ የሚባሉት የሚኖሩት በምድር ላይ ነው የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ድርጅት ትምህርት ከየት የመጣ ነው?

12. “ሌሎች በጎች” ወይም “እጅግ ብዙ ሕዝብ” የሚባሉት የይሖዋ ምስክሮች ለዘላለም የሚኖሩት በምድር ነው፤ ለሚለው የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት እንደ ቃለ እግዚአብሔር ማስረጃ የሚወስደው

ማቴ. 6፥10 ነው። "ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር" የሚባለው የድርጅቱ መጽሐፍ በገጽ 165 ላይ አምላክ ለምድር ያለው ፈቃድ ሰዎች በምድር እንዲኖሩና እንዲገዙ ለመሆኑ ከዘፍ. 1፥28 እና ከኢሳይያስ 45፥18ን ከማቴ. 6፥9–10 ጋር አያይዞ ያቀርባል። ነገር ግን የማቴ. 6፥10 ዐውደ ንባብ ከዘፍ. 1፥28 እና ከኢሳ. 45፥18 ጋር ምን ያገናኘዋል? [ክፍሉ የእግዚአብሔር ፈቃድ በሰማይ እንደሆነ እንዲሁ በምድር እንዲሆን ነው እንጂ የሰዎች በምድር የመኖርና የመባዛት ጉዳይ አይደለም። ንጽጽሩ የተካሄደው በሰማይ የሆነው በምድር እንዲሆን ነው። ይኸውም ያለ ኃጢአት የሆነው የእግዚአብሔር አገዛዝ በሰማይ እንደሆነ በምድር እንዲሆን]።

13. ምድር ገነት ትሆናለች ለሚለው የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት በይሖዋ ምስክሮች የሚጠቀሰው ሌላው ጥቅስ መዝ. 37፥9, 11, 29 ነው። ነገር ግን የምዕራፉ ዐውድ በአጠቃላይ የሚያመለክተን ዘማሪው ኃጢአተኞች ከጠፉ በኋላ ጻድቃን ስለሚኖሩበት የወደፊቷ ምድር እየተናገረ ሳይሆን ስለ ራሱ ዘመን ነው። በዕብራይስጡ መሬት የሚለው ቃል እግዚአብሔር ለእስራኤ ልጆች የሰጠውን የተስፋይቱን ምድር የሚያሳይ ነበር (ዘሌ. 25፥33 ጀምሮ፤ ሆሴ. 9፥13፤ ዘዳ. 4፥38፤ 11፥13–15፤ 8፥7–9፤ ኤር. 2፥7)። ስለዚህ ምድር የሚለው ቃል እግዚአብሔር ለእስራኤል የሰጠውን የቃል ኪዳን ምድር እንጂ አጠቃላይ ምድርን የሚያመለክት አይደለም። ምድሪቱንም የሚወርሱ ሰዎች (ቁ. 9, 11, 22, 29) ያበድራሉ (ቁ. 21)፥ በመንገዳቸውም የቀና ነው (ቁ. 7)። የክፍሉ ትምህርት ይህ ከሆነ የመጠበቂያ ግንብ ትምህርቱን ለማጽናት እንዲህ ያሉ ጥቅሶችን ለምን ይጠቅሳል?

14. እግዚአብሔር ለሰው ልጆች መኖሪያ እንድትሆን የሰጠው ምድርን ከሆነ (መዝ. 115፥16) "ቅቡዓን" ለምን በሰማይ ይኖራሉ?

15. ጌታን የሚያገለግሉት ጌታ በሚኖርበት ስፍራ የሚኖሩ ከሆነ (ዮሐ. 12፥26) "ሌሎች በጎች" ከኢየሱስ ተለይተው ለዘላለም በምድር ይኖራሉ የሚለው የመጠበቂያ ግንብ ትምህርት ከክፍሉ ጋር አይጋጭምን?

16. ክርስቲያኖች ሁሉ በእግዚአብሔር መንፈስ መመራት ካለባቸውና (ሮሜ 8፥14–16) በእግዚአብሔርም መንፈስ የሚመሩ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆኑ (ቁ. 14)፥ የተቀበሉትም የባርነት ሳይሆን የልጅነት መንፈስ ከሆነ (ቁ. 17) ታላቁ መንጋ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለህም፥ እግዚአብሔርንም አባት ብለህ መጥራት አትችልም ለምን ተባለ?



## 3.6 የይሖዋ ምስክሮች አስተምህሮ በሞት፥ በነፍስና በሲኦል ላይ

የይሖዋ ምስክሮች የሰው ነፍስ ወይም መንፈስ ቁሳዊ ከሆነው የሰው አካል የተለየ መሆኑን አያምኑም። ሰው ማለት የአካልና የ"እስትንፋስ" ጥምር (ውሁድ) ነው፤ እነዚህም ሁለቱ "ሕያው ነፍስ"ን አስገኙ። ስለዚህ አንድ ሰው በአካል ሞተ ማለት በነፍስ ወይም በመንፈስ መኖር አቆመ ማለት ነው። ሰው ሲሞት በሰማያዊም ሆነ በምድራዊ ሕይወት መኖር ያቆማል።

ለይሖዋ ምስክሮች ኢቁሳዊ የሆነ ነፍስ ወይም መንፈስ የለም። ነፍስ ማለት "ሰውዬው ራሱ ወይም አንድ እንስሳ ያለው ሕይወት ማለት ነው"[1]። መንፈስ የሚባለው ደግሞ የሚያመለክተው "የሕይወታችን[ን] ኃይል ነው"[2]። "ይህ የሕይወት ኃይል በእያንዳንዱ የሰዎችና የእንስሳት የአካል ሴሎች ውስጥ ይገኛል"[3]። ነፍስና መንፈስ አንድ አይደሉም። ነፍስ ማለት "ሕይወት" ማለት ነው። መንፈስ ማለት ደግሞ የመኖርን እውነታ እውን የሚያደርግ ኃይል ወይም ጉልበት ነው። መሞት ማለት በሥጋም ሆነ በነፍስ ወይም በመንፈስ መኖር ማቆም ማለት ነው። በሰው ተፈጥሮ ውስጥ የማይሞት ነፍስም ሆነ መንፈስ የለም። ሙታን በነፍስና በመንፈስ ንቁ ሆነው በሥጋ ለመኖር ትንሣኤን የሚጠብቁበት "የሽግግር ወቅት" የሚባል ነገር የለም።

ኃጢአተኞች ንቁ ሆነው ለዘላለም አይሰቃዩም። ሲኦል ማለት የመቃብር ስፍራ ወይም የኃጢአተኞች ለመጨረሻ ጊዜ ፈጽሞ መጥፋት ነው። ኃጢአተኞች በመከራ አይቀጡም ነገር ግን ፈጽሞ ወደ አለመኖር ደረጃ ይሄዳሉ።

1. ከቅዱሳን ጽሑፎች እየጠቀሱ ማመራመር (1994) ገጽ 374
2. በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ (1991) ገጽ 79. በቅንፍ ያለውን አይጨምርም።
3. ዝኒ ከማሁ